ያረፈዱትን ልጆች ከቅጣት ምክር ስለሚቀድም "ጌታን ትወዳላችሁ ተቀበሉት እሱ ይወዳችኋል ጥሩና ታላቅ ሰው ያደርጋችኋል" ይላቸዋል፡፡ በመጨረሻም ተመክረዋል ብሎ ያሳልፋቸውና ወደክፍላቸው ይገባሉ፡፡ በየቀኑ ምክሩን (ወንጌልን) ከሱ ለመስማት ሆን ብለው የሚያረፍዱም ነበሩ፡፡

የሦስት አመቱ የደገም ቆይታው ዘበኛ ይባል እንጂ እንደገና ወደ አገልግሎት የተመለሰበት ጊዜ ነበር፡፡ ሌሊት እየዞረ ያገለግላል ቅዳሜና እሁድ ርቆ በመሄድ ያገለግላል፡፡ ባዶውን ክፍል ልክ በሰው እንደተሞላ አዳራሽ በመቁጠር ይሰብካል፡፡ ከዚያም ባለፈ ለታመሙ ተማሪዎች ወላጆችና ያካባቢ ነዋሪዎች ሀመም ይፀልያል፡፡ የተጨነቁ ሰዎች ያለበት ድረስ በሽተኞችን ተሸክመው ያመጡ ነበር፡፡ ጌታም ይፈውሳቸው ነበር፡፡





# ሌላ ትልቅ ስራ

በ1982 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ በአንድ ሌሊት ገርቦሌና አዳነች ተመሳሳይ ህልም አይተው አደሩ፡፡ ህልሙም ሦስት ነጭ የለበሱ ሰዎች ወደቤታቸው መጥተው "አሁን ይበቃል የዚህ ቦታ ቆይታህ አልቋልና ከዚህ በኋላ ሌላ ትልቅ ሥራ ስለተዘጋጀ ወደዚያ ትሄዳለህ" የሚል ነበር፡፡ ባልና ሚስት ስለ ህልማቸው እየተገረሙ ሳለ የአዳነች ወንድም ገመቹ ቶሌራ ከነቀምት ሙሉ ወንጌል ቤተክርስቲያን ተልኮ ነበርና መልዕክት ይዞ መጣ፡፡ በዚያን ጊዜ የነቀምት ሙሉ ወንጌል ቤተክርስቲያን መሪዎች የነበሩት እነ ፓስተር ተስፋዬ ራዕይ ያለውና ጌታ የጠራው አገልጋይ ይፈልጉ ኖሯል፡፡ በዚህ መሀል አንድ እግዚአብሔር የጠራው ነገር ግን የተጣለና አሁን ዘበኛ ሆኖ የሚኖር ሰው ደገም ላይ እንዳለ ይሰማሉ፡፡ ይኼኔ ነው ያመልዕክተኛ ገርቦሌን ወደነቀምት ሙሉ ወንጌል ቤተክርስቲያን እንዲጠራ ተልኮ የመጣው፡፡ የገርቦሌን መሳፈሪያ ፓ/ር ተስፋዬ ኃይሌ ከራሳቸው ኪስ ሲልኩ ገመቹ ቶሌራ ደግሞ ሠራተኛ ስለነበር የራሱን መሳፈሪያ ችሎ ወደ ጊዳ ተጓዘ፡፡

ይህ የተረጋገጠ የእግዚአብሔር ፈቃድ በመሆኑ ከደገም ነቅሎ ወደ በካቀጬ ለመጓዝ ጊዜ አልፈጀበትም፡፡ ቀጬ በደርግ ዘመን በገበሬዎች መንደር ምሥረታ የተቋቋመች መንደር ስትሆን ቀስ በቀስ ገበሬዎቹ ከመንደር ምስረታው ሰፈር እየተንሸራተቱ ወደ ቀድሞው ቆዬና ኮሲ ጓሮ በመመለሳቸው ብዙ ባዶ ጎጆዎች በቀጬ ነበሩ፡፡ እነ ገርቦሌም ወደ አንዱ ባዶ የሳር ክዳን ቤት ገብተው

መኖር ጀመሩ:: ቤተሰቡን በዚህ ሁኔታ ትቶ ጥሪ ወዳቀረበችለት የነቀምት ቤተክርስቲያን ሄደ:: በዚያም በፍቅር ተቀብለውት እንደአገልጋይም ፀለዩለትና አቅም የፈቀደውን አስይዘውት ወደ ቀዬው ተመለሰ ::

ይህ የመንደር ምስረታ ሰፈር ኑሮ ለአዳነች በጣም ከባድ ጊዜ ነበር:: "አራተኛ ልጄን ማርታን የወለድኩት እዚህ ነው ለጎኔ ማረፊያ አልጋ እንኳ አልነበረንም:: በዚያ ላይ ቤቱ በመንግስት ትዕዛዝ ባስቸኳይ የተሰራ በመሆኑ ሰሪዎቹም ከካድሬዎች ከሚደርስ ማንገላታት ለመዳን እንደነገሩ የሠሩት በመሆኑ ያፈሳል:: ያለውን ጨርቅ ሁሉ ልጆች ላይ ደርበን እኔና ገርቢሴ የመጋረጃ ጨርቅ አውርደን እምንለብስበት ጊዜ ነበር:: መውለጃዬ ሲደርስ ገርቢሴ ሻምቡ ኮንፈረንስ ላይ አገልግሎት ስለነበረበት መሄዱ ግድ ነበር:: ልቅር እንኳ ቢል እኔ አላስቀረውም ነበር:: ስለዚህ የነበረው ዕድል እርሱ እስከሚመለስ ሳልወልድ እንድቆየው ፀልዮ መሄድ ነበርና ሄዶ ወር ቆይቶ መጣ:: አስር ወር ሆኖኝ ልጄን በሆዴ ይዤ ጠበቅሁት::

ሀሙስ ዕለት ገባ:: አርብ ዕለት የቆሸሸ ልብሱን አጣጠብኩለት:: ስለ ደከመው ተኛ:: ቅዳሜ ጧት ቡና ጠጥተን ሦስት ሰዓት ላይ ማርታ ተወለደች:: የሚለበስ የሚበላ አልነበረም:: ውዬ አድሬ እሁድ ቀን ላይ እናቴ ገንፎ ይዛልኝ መጣችና በላሁ:: በዚያ ችግር ውስጥ ፊቴ የበላና የተመቸው ይመስላል:: ልጆቼም ጠግበው እየደረሱ በድሎት የተያዙ ይመስሉ ነበር:: አንድም ቀን ልጅ ታሞብኝ ተጨንቄ አላውቅም:: ቤተሰቤም ሁሉ ሰላምና ጤና ነበር::





ሁሉም ሲወለዱ ከኔ ጋር የሚገኘው አማማዬ ገርቢሴ ብቻ ነው:: እሱ ቆሞ ይፀልያል እኔ አምጬ እወልዳለሁ:: ምጤ አፍታ ሳይቆይ እገላገልና ልጄን አቅፋለሁ::

በአገልጋይነቱ ወደ መታወቅ የመጣው ገርቢሴ ሰው ጠልቶ የተወው ሰፈራ ጣቢያ ውስጥ መቀመጥ አላስፈላጊ ነው አለና ጊዳ ከተማ መግቢያው ላይ በወር ሃያ አምስት ብር የምትከራይ ቤት አግኝቶ ገቡ:: አልጋ በአራት ብር ለወር ተከራዩ:: ገርቢሴ የተከራዩት ቤት ብዙም ሳይቆይ አዳነችን ከአራት ልጆቿ ጋር ትቶ ወደተጠራበት አገልግሎቱ ሄደ:: ልጆች ይዛ ብቻዋን በመሆኗ የከበደው ታናሽ ወንድሟ ጌታሁን መጥቶ ከነሱ ጋር መኖር ጀመረ:: አከራዩ ሁሌ የቤት ኪራይ ይጠይቃታል:: "ቆይ ባለቤቴ አልመጣም" እያለች አራት ወር አለፈ:: "ባልሽ ከጠፋ ገንዘቤ ይቀራል ወይ ክፈይ ወይም ከቤቴ ውጪ ካልወጣሽ በላይሽ ላይ እቃዬን አስገባለሁ" ሲል ቁርጡን ተናገረ:: በዛቻ ብቻ አላቆመም ለቤት መግቢያ የሚሆን ጠላ ለመጥመቅ መጥተው አሻሮ ይቆሉ ጀመር:: የቀንና የሊሊት ልብስ ሆና የምታገለግላት የአዳነች ሽርጥ በአሻሮ እሳት ተያይዛ ተቃጠለችባት:: ስለዚህ ከዚህ በላይ እዚያ ቤት መቆየት እንደማትችል ሲገባት ልጆቿን ሰብስባ ወጣችና ሌላ ትንሽ ቤት ተከራይታ ገባች::

ገርቢሴ መጋቢት የወጣ በስድስት ወሩ መስከረም ሲመለስ በአዲስ አበባ ዞሮ መጣ:: ቀድሞ የተከራዩት ቤት ሰተት ብሎ ገባ ቤቱ በባለቤቶቹ እየተኖረበት ሲያገኝ "ቤተሰቤን እዚህ ትቼ ነበር የሄድኩት የትሄዱ" ብሎ ጠየቀ:: "ቤተሰብህ የት እንዳለ አንተ እወቅ

እንጂ ጭራሽ እኛን ትጠይቃለህ" በማለት ሲያንጓጥጡት ትቶ ፍለጋ ጀመረ፡፡ ያሉበትንም አጠያይቆ ቤት አገኘው፡፡

አጻነች ሆድ ብሷታል ስታየው አንገቱ ላይ ተጠምጥማ አለቀሰች አብረውም ተላቀሱ፡፡ ለቅሶው ቋንቋ አለው ችግርና መከራ ከብዷቸዋል፡፡ ልጆቿ ጦም ያድራሉ፡፡ አንድ ጊዜ በተከታታይ ሁለት ቀን የምትሰጣቸው አጥታ ጦም አደሩ፡፡ ሦስተኛም ሊደገሙ ሆነ፡፡ በዚህ ጊዜ የእናት ሆድ አልቻለም፡፡ "ጌታ ሆይ እነዚህ ልጆች ሦስተኛ ቀን ይችላሉ? እባክህ በቤቴ አለፍ" ብላ ፀልያ የምታደርገውን አጥታ ወዲያ ወዲህ ስትል አንድ ሰው ከውጭ ተጣራ፡፡ ያ ሰው በቆሎ በአህያ ጭኖ ሲያልፍ ማዳበሪያው ከመጠን በላይ ሞልቶ ስለነበረ እየፈሰሰ አስቸገረውና "እባክሽ እየፈሰሰ ስላስቸገረኝ ዕቃ ስጭኝ ልቀንሰው" አለና ጭነቱን አራገፈ፡፡

ወደ አስር ኪሎ የሚጠጋ በቆሎ ቀንሶ ይህንን ለልጆችሽ ቁይላቸው ብሎ አመስግኖ ሄደ፡፡ እሷም የቅርቡን ጌታ አመስግና ይዛ ገባች፡፡ ያቺ በቆሎ እየተበላች ገርቦሌ እስከሚመጣ ድረስ ሳታልቅ በተዐምር ቀለበቻቸው፡፡ ገርቦሌም ቢሆን ባለበት ቦታ ሆኖ ስለቤተሰቡ መጨነቁ አይቀርም፡፡ አዲስ አበባ በነበረ ጊዜ ቀጣና ሁለት ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተክርስቲያን ለመካፈል ሄዶ በነበረ ቀን ቤተሰቡ ከመቼውም ይልቅ ፊቱ ድቅን አሉበት አልቻለም፡፡ አብረዋቸው ከነበሩት ሰዎች ተለይቶ ወደ ሸንት ቤት ገባ፡፡ ሸንት ቤት የገባው ሸንት ቤት የሚያስገባ ጉዳይ ኖሮት አይደለም፡፡ በጌታ ፊት ሊያዝን ነው፡፡ "ጌታ ሆይ ሸንት እንኳ ይህንን የመሰለ ቤት ተሰርቶለት እኔ





ቤተሰቤን የትም በትኜ እዚህ አለሁና እባክህ ቤት ስጠኝ" ብሎ ወጣ፡፡

በማግስቱ አንድ የእግዚአብሔር ሰው ጠራውና ብር አንድ ሺህ አመስት መቶ ሰጠው፡፡ እንግዲህ ይዞት የማያውቀውን ይህን ብዙ ገንዘብ ይዞ ነው አሁን ከቤተሰቡ የተገናኘው፡፡ ቤት ስጠኝ ብሎ ፀልዮ ስላገኘው እንደቀድሞው ለተቸገሩ ለመስጠት ልቡ አልተከፈለም፡፡ በአጀንዳ የተገኘ ብር ስለሆነ፡፡ አጻነች ተከራይታ የቆየችው ቤት ይሸጣል ሲባል ስለሰማ ዋጋ ጠየቀ፡፡ "አንድ ሺህ አምስት መቶ" አሉት ገዛው፡፡ የቤቱ ዋጋ የተቆረጠው አዲስ አበባ ሲሆን ትዕዛዙ የወጣው ሸንት ቤት ውስጥ በቃተተ ጊዜ ነበርና ሳያንስ ሳይተረፍ በተሰጠው ብር የተከራዩውን ቤት ገዛ፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ የራሳቸው ቤት ባለቤት ሆኑ፡፡

ይህች የመጀመሪያ ቤታቸው መንገድ ዳር በመሆኗ የገጠሩ ሰው ወደገበያ የሚሄደውም የሚመለሰውም በዚያ ጎዳና በደጃቸው ላይ ነው፡፡ የመንገድ ዳር ቤት እንደመሆኗ በባህሉ መሰረት የሚጠበቅባት ህብረተሰባዊ አገልግሎት ብቅ ብቅ ይሉ ጀመር፡፡ የመሸበት አሳድሩኝ፡፡ ውሃ የጠማው አጠጡኝ፣ የታመመ አሳርፉኝ ይላል፡፡ አልሸጥ ያሉ እንስሳት እስከሚቀጥለው የገበያ ቀን እዚህ ይቆዩልን ብለው አጥር ላይ አስረው የሚሄዱም ነበሩ፡፡

የመሸበት ሰው አሳድሩኝ ብሎ በማንኛውም ሰው ደጅ ቆሞ ሲጠይቅ "እንግዳ የሚያድርበት እዚያ ነው" በማለት ወደነ ገርቦሌ ቤት ያመለክቷቸዋል፡፡ "እነሱ እንግዳ ይወዳሉ" ይባላል ባገሩ፡፡

እናም የመሸበት “ስለ እግዚአብሔር ብላችሁ አሳድሩኝ” ይላል በደጅ ቆሞ ከእርሱ የቀደሙም በቤት ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ትልቁ ችግር መኝታ መቀመጫና ምግብ ነው፡፡ ለመቀመጫነት የሚያገለግል ትልቅ ጉራጅ ጉቶ የነበረ ሲሆን ጢት ያወጡታል ማታ ለእንግዳ ያስገቡታል፡፡ ምግብን በተመለከተ ምንም ከሌለ ፀልየው ውሃ ይሰጧቸዋል፡፡ “የኛ ምግብ ይህ ስለሆነ ጠጡ” ይባላሉ፡፡ እንደዚያ ጠጥተው በህልማቸው ጌታ ተገናኝቷቸውና ጢት ወንጌልን አምነው ወደ ቤታቸው የተመለሱም አሉ፡፡ ከዚህ አንፃር የእንግዳውን አለማቋረጥ ካየነው የመዳንን መንገድ እንዲያውቁ ነው ብለን ልናስብ እንችላለን፡፡

ጊዳ በገቡበት የመጀመሪያዎቹ አመታት አካባቢ ከጨሊያ አገልግሎ ሲመለስ በመንገድ ራበው፡፡ በመንገዱ ዳር ዳስ ነገር ከልላ ሻይና ዳቦ የምትሸጥ ከሚላ የምትባል ሴት ነበረችና ከጥላው አረፍ አለ፡፡ ሻይና ዳቦ ፈላጊ የመጣ መስሏት ቀዳች ዳቦም አቀረበችለት፡፡ በኪሱ ምንም ስላልነበረው “እኔ መንገደኛ ነኝ ገንዘብ የለኝም ወይስ በነፃ ትሰጪኛለሽ” ሲል ጠየቃት፡፡ “አንተ ለማኝ ነህ” ስትል ጠየቀችው “አይደለሁም” አላት “ለማኝ ነኝ በልና ትበላለህ” አለችው፡፡ በርሀብ ጊዜ የሚቀርብ ምግብ ኤሳውን እንዳዋረደ ትዝ አለው፡፡

“ኤሳው ደክሞ ከበረሀ ገባ ኤሳውም ያዕቆብን ከዚህ ከቀዩ ሎጥ አብላኝ እኔ እጅግ ደክሜአለሁና አለው፡፡.... ያዕቆብም በመጀመሪያ ብኩርናህን ሽጥልኝ አለው፡፡ ኤሳውም እነሆ እኔ ልሞት ነኝ ይህች ብኩርና ለምኔ ናት አለ፡፡ ያዕቆብም እስኪ መጀመሪያ ማልልኝ አለው፡፡ ማለለትም ብኩርናውንም ለያዕቆብ ሸጠ” /ዘፍጥረት 25:34/ ስለዚህ “ለማኝ ነኝ” ብሎ ከመብላት ይልቅ ጌታ በተራበ ጊዜ የመለሰውን መልስ መረጠ፡፡ ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም፡፡...” ስለ እንጀራ የማንነት ለውጥ ለሚፈትናቸው ሁሉ ትምህርት እንዲሆን እሱ ወንጌላዊ ነው እንጂ ለማኝ አይደለምና ከነክብሩ መንገዱን ሄደ፡፡

ከፊት ተራራ መውጣት ይጠበቅበት ስለነበረ “ጌታ ሆይ ለማኝ አይደለሁም ብዬ የሚበላውን ትቼ መጥቻለሁና እባክህ የምበላው ነገር ስጠኝ፡፡” ብሎ ለመነ ከፊት ለፊት መንገደኞች ጥንቅሽ እየበሉ መጡ ከእነርሱም አንደኛው እንዲህ አለው፡፡ “አንተ መንገደኛ የራበህ ትመስላለህ እንካ አፍህን እርጥብበት” ብሎ ሰጠው ጥንቅሹን እየመጠጠ ተጓዘ፡፡

ገቢያ ወጥቶ ውሃ የማይጠማው የለምና ውኃ ለሚጠይቀው ተጠሚ ሁሉ አዳነች በጀርባዋ ከወንዝ የምትቀዳው ውሃ ነበር የሚቀርበው፡፡ የከተማው ሴት ውሃ የሚቀዳው በየግቢው ከሚገኙ የውሃ ጉድጓዶች ሲሆን አዳነች ከጉድጓድ ውሃ መሳብ ልትለምድበት አልቻለችምና ከመጓተቱ ትልና እንስራዋን አንስታ ወደ ወንዝ ትወርዳለች፡፡ ከሁሉ የሚፈትነው የልጆቿ መጓጓት ነበር፡፡ ገቢየተኞች ሙዝ ለገቢያ ተሸክመው ይመጡና ውሃ ይጠጣሉ ሙዛቸውን ያሳርፋሉ ያሳድራሉ፡፡ ተስተናግደው ሲሄዱ ግን አንዲት ሙዝ ወይም ሸንኮራ ወይም ጥንቅሽ ከያዙት ልጅ አንጊ ከሆነው ምርታቸው አይናቸው ለሚንከራተተው የቤቱ ልጆች እጃቸው

አይፈታም ነበርና አዲና ገርባሌ ይህን ቤት አልወደዱትም፡፡ ባንድ ድምፅ ጌታ ሆይ ይህ ቤት መንገድ ዳር በመሆኑ ማስተናገዱ ቸግሮናል በዚያ ላይ እንግዳው እየተረፈ በደጅ እስከሚያድር ደርሷል እባክህ ሰፊ ቤት ስጠን" ብለው ለመኑ፡፡

ሌሊት እየዘነበ በተኙበት አንድ ድምፅ ሰሙ፡፡ ቤቱ እስከሚነቃነቅ የሆነ ነገር ሆኗል፡፡ "መብረቅ ይሆን" አለ ገርባሌ ለአዲ ቀስ ብሎ በጨለማው ውስጥ ለማንኛውም ብሎ ባትሪ ይዞ ደጅ ለመውጣት በሩን ቢፈልገው አጣው፡፡ የቤቱ አቀማመጥ ቀድሞ እንደነበረው ሳይሆን ተለዋውጧል፡፡ በሩ ከጠፋ ቀዳዳ መፈለግ ነበረበትና በጓሮ በኩል አንድ ከቤት የሚያስወጣ ቀዳዳ አገኘና ሾልኮ ወጣ፡፡ በዚያው ባትሪ የቤቱን ዙሪያ ገባ ሲመለከት በግቢ ውስጥ የነበረው ረጅም ባህር ዛፍ ቤታቸው ላይ ከስሩ ተገንድሶ ተጋድሟል፡፡ ግንዱና ቅርንጫፎቹ ቤቱን እንዳለ ደምስሰው ጣሪያውን ከመሬቱ ጋር አጣብቀውታል፡፡ በቁሟ እንደዋሻ ተሸርፋ የቆመችው የቤቱ አካል ቤተሰቡ የተኙበትን የሚከልለው ሸራፊ ብቻ ነው፡፡ በፀሎት የገዙት ቤት በፀሎት ፈርሶ አደረ፡፡የወደቀው ዛፍ ባለቤት ግምቱን ልክፈላችሁ ቢላቸውም እምቢ አሉ፡፡

"ቤቱን የሸጡልን ሰዎች የገዛንበትን ዋጋ ሊመልሱልን ስለጠየቁን ተስማምተን አንድ ሺ አምስት መቶ ብራችንን ይዘን ወጣን፡፡ ቤታቸው ሁልጊዜ እንግዳ ስለማያጣው አዲስ የሚሠራው ሰፋ ብሎ ሦስት ክፍል ያለው መሆን እንዳለበት ተስማሙ፡፡ ለዚህም የእምነት ፀሎታቸውን በጌታ ፊት በዚህ መልክ አቀረቡ፡፡ የአንድ





ብር ምስማር፣ ሦስት እንጨቶችና ሦስት ብር በመሬት ላይ አስቀምጠው "ለዚህ ቤት የሚያስፈልገውን ቆርቆሮና ሚስማር ብረት የሆነው ሚስማሩ ይፈልግ፡፡ እንጨቱን እንጨቱ ይፈልግ፡፡ ብሩን ብሩ ይፈልግ ተፈላልገው ቤት ይሁኑ" በማለት ፀለዩ፡፡ አመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ እንደተባለው ሁሉም ቁሳቁሶች ተጠራርተው ቤት ሆኑ ባለሦስት ክፍል ቤት፡፡

1983 ዓ.ም የመንፈስ ቅዱስ ጉብኝት ውጤት ሆኖ በርካታ ሰው ወደጌታ ይጎርፍ የነበረ ሲሆን በዚያው መጠን ማፈን የማይቻለውን ሰማያዊ እሳት ለማፈን ጠላት ለመጨረሻ ጊዜ ባለ በሌለ ኃይሉ የሚፍጨረጨርበት ወቅት ነበር፡፡ እግዚአብሔር ከፊታቸው እንደወጣ የገባቸው አስተዋይ አገልጋዮች በበካ ላይ ታላቅ ኮንፈረንስ አዘጋጁ፡፡ ኮንፈረንሱ የተዘጋጀው የወ/ዊ ገመቹ ቶሌራ ሠርግ ነው በሚል በሰርግ ስም ሲሆን ለነገሩ እርሱ ካገባ ቆይቶ ነበርና እንደ አዲስ ድራማዊ ሠርግ ተብሎ በውስጥ ኮንፈረንስ ታቀደ፡፡ የሁለትና የሦስት ቀን መንገድ ቅዱሳን ወገኖችና አገልጋዮች ከየገሩ ስንቃቸውን ተሸክመው ወደ በካ ተጉዘው ደረሱ፡፡ ያ ወቅት የደርግ የመጨረሻ አመት ስለነበር ስንቅ ይዞ መጓዝ ለመንግስት ተቋማት ምን ማለት እንደሆነ ግልፅ ነበርና ወደ ኮንፈረንሱ የሚተመው ሕዝብ በየቦታው ይታሰራል ይፈታል፡፡ ፓ/ር ኢያሱ ከበሎ ተነስቶ በካ እስከሚገባ ድረስ በሁለት ቀን ጉዞው ሁለቴ ተይዞ ተገርፎ ተመርምሮ ነው የደረሰው፡፡ ሌሎችም በያቅጣጫቸው እንዲሁ መሰናክሎቻቸውን እያለፉ ታላቅ

የእግዚአብሔር ክብር ወደ ተገለጠበት በካ ደረሱ፡፡ መዘምራን ከነቀምት መጥተው ነበር፡፡ ሰባኪያኑም ወ/ሮ አርጋውንዳ ወ/ሮ ታደሰ አወቀና ወ/ሮ ጌታቸው ኃይሌ ነበሩ፡፡ ሕዝቡ ያየዘው ስንቅ ሲያልቅ ሦስት በሬ ታረደ፡፡ ታላቅ ሪቫይቫል ነበር ከኮንፈረንሱም በኋላ ይህ የበካ ሪቫይቫል አልቆመም ቤተክርስቲያን መሥርቶ አልፏል በቦታው፡፡ ጌሴም ሙሉ ወንጌል የምትባል፡፡





## የእምነት ሥራዎች

"እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ነፋስ አታዩም ዝናብም አታዩም ይህ ሸለቆ ግን ውሀ ይሞላል" (2ነገ 3፡17)

ከጊዳ የተነሳው ይህ የእግዚአብሔር ባሪያ በነቀምቴ በኩል አልፎ ዴዴሳ ሸለቆ ማንጎ ሜካ ውስጥ ካለው ኤፍሬም ሆቴል ቁርስ ነገር ቀማምሶ ወደ ጊምቢ የአባሴናን ላይ ዳገት የምጡን እየቧጠጠ በሚንፏቀቀው ቼንቶ እያዘገመ ተጓዘ፡፡ ከጊንቢ ጀምሮ እዚህና እዚያ ጌታ ወደ ሚመራው አብያተክርስቲያናትና ግለሰቦች ጎራ እያለ የደንቢ ዶሎን መንገድ ወደ ግራ ትቶ መቀነጆላይ ወደ ቀኝ የሚታጠፈውን ተከትሎ በነጆ በመንዲ አድርጎ እንደ ባህር ተንጣሎ መልካውን ሞልቶ አባይን ለመገናኘት የሚያዘግመውን የዳቡስን ወንዝ በተግጣጣሚ የብረት ድልድይ ተሻግሮ ቤንሻንጉልና ጉሙዝ ክልል ባምባሲ ገባ፡፡ ባምባሲ የሚገኙትን ቅዱሳን ካገለገለ በኋላ ጌታ ወደ ቤጊ መራው፡፡

ከባንባሲ ቤጊ የሰድሳ ኪሎ ሜትር ርቀት ሲሆን መንገዱ ማሊያን ሲገባ የቀደደው ሆኖ ለብዙ ዓመታት ሳይሰራ ወጣ ገባ ድንጋያማና ጭቃማም ሆኖ ሲኬድበት ኖሯል፡፡ አልፎ አልፎ ራሺያ ሥሪት የሆኑና ጎማቸው ከመሬት ከፍ ያሉ መኪኖች እንደ ህዝብ ማመላለሻነት የሚያገለግሉ ሲሆን የሚያስከፍሉት ዋጋ የትም የሌለ ነው፡፡ አይቀመስም እኔ ራሴ እንኳ በዚህ አስቸጋሪ መንገድ ያውም በደላላ በተገኘ ኢንትሬ መኪና ከዕቃ ጋር ተጭኜ መጓዜን

አስታውሳለሁ፡፡ ለጊዜው የተባልነውን ከፍለን ተሳፈርን እንጂ ያንን ሁለንተናው ወደል ብረት የሆነ የጣሊያን መኪና በገመድ እየጎተትን ከወንዝና ከጭቃ ስናወጣ ውለን ቤጊ ያገባነው እኛ ነን፡፡

እንዳሁኑ መንገድ በየቅጣጫው ሳይሰራ በፊት በዚያ አገር የነበረው ጉዞ በጣም ከባድ ነው፡፡ ባሁኑ ጊዜ ከባንባሲ ወደ ቶንጎ ከባንባሲ ቤጊ ከቤጊ በጊዳሚ በጅማ ሆሮ አድርጎ ጫንቃ መግባት ቀላል ነው፡፡ ቀድሞ ግን ከቤጊ ጊዳሚ ሃምሳ ስድስት ኪሎ ሜትር ለማይሞላ መንገድ አምስት መቶ ብር ከፍለን ተጉዘናል፡፡ ያውም መደበኛ የትራንስፖርት ተሽከርካሪ ኖሮ ሳይሆን ባጋጣሚ በዚያ አገር የማዕድን አሰሳ ሥራ ይካሄድ ስለነበረ አንድ የማዕድን ሚኒስቴር ፒክአፕ ሾፌር ከመደበኛ ሥራው በተደራቢ የተጨነቁ ባለጉዳዮችን እንዲህ ያጓጉዝ ነበር፡፡ ሌላ ጊዜ ከአዲስ አበባ ቤጊ በትንሿ አይሮፕላን ከቤጊ የጊዳሚ ቤተክርስቲያን በላከችልኝ በቅሎ መጓዜን አስታውሳለሁ፡፡ በቅሎዋ ደክማብን መሄድ ስላቆመች ላዩዋ ላይ ቁጭ ብዬ ከማድር በማለት ይዟት የመጣው ዲያቆን የወገኖችን ቤት ፊልጎ አድረን በማግስቱ ረፋድ ላይ ጊዳሚ ደረስን፡፡ እንግዲህ እኔ አንዴ በኤንትሬ ሌላ ጊዜ በማዕድን ሚኒስትር መኪና ሌላ ጊዜ በበቅሎ የተጓዝኩትን ያን ፍዳ አስጨራሽ መንገድ ገርቦሌ በእግር ተያየዘው፡፡

አንድ እግረኛ በሰዓት በአማካይ ሰባት ኪሎ ሜትር ያህል ይጓዛል፡፡ ከባንባሲ ቤጊ ያለው መንገድ በዚሁ አይነት አንድ ቀን ተኩል ፈጅቶበታል፡፡ የባንባሲ ወገኖች ከከተማዋ ወጣ እስከሚል





ሸኙትና ተመለሱ፡፡ በቀኝና በግራ የበቆሎና የማሽላ ሰብል እየተመለከተ ሜዳማውን አገር አልፎ ወደ ሞቃቱ የቀርቀሀ ደን ገባ፡፡ የቀሽማንዶን የፀሐይ ንዳድ መቋቋም አልቻለም፡፡ ጫማው ከሙቀቱ የተነሳ ስላቃጠለው አውልቆ በባዶ እግሩ እያዘገመ ሰኞ ገበያን እንዳለፈ ጌታ አንድ ነገር አለው ሲያገለግል ሊለብስ በቦርሳ የያዘውን ሙሉ ልብስ ቤጊ ለሚያገኛቸው ሁለት አገልጋዮች እንዲሰጥ ኮቱን ሊቀበለው ለሚመጣው ሱሪውን ማታ እግሩን ለሚያጥበው፡፡ አድካሚ ጉዞ በመንገድ የተላጠ እግር ረሃብና ጥማት ደረስኩ ሲል ደግሞ የለበሰውን ለሌላ መስጠት ለሌላ ሰው ይከብዳል፡፡ እግዚአብሔርን ለሚታዘዘውና እግዚአብሔርም ራሱ ለገራው ለዚህ ለተገራ ባሪያ መታዘዝ ደስታ ነውና እንደተባለው ለሚገባቸው ሱሪና ኮቱን አሳልፎ ሰጠ፡፡

ይህ ዕሑፍ ሲዘጋጅ ኮት የደረሰው በዝማሬ እያገለገለ ሲሆን ሱሪ የደረሰው እግር አጣቢ ደግሞ አዲስ አበባ አገልጋይ ሆኗል፡፡ ለሁለት ሳምንት በቄለምና በበጊ አገልግሎ ስለ መልስ ጉዞ ሲያስብ በመጣበት ሁኔታ መመለሱ ከበደው፡፡ ስለዚህ ከቤጊ አዲስ አበባ በአይሮፕላን ለመብረር አሰበና ወደ አየር መንገድ ቢሮ ሄደ፡፡

ቤጊ ካለችው የአየር መንገድ ቢሮ ቀጥተኛ አገልግሎት ማግኘት የማይታሰብ ነው፡፡ ቡናቸውን በትሬንታ ኳትሮ ወደ አዲስ አበባ የላኩ ነጋዴዎች በአየር ቀድመው አዲስ አበባ ለመድረስ እዚያች ቢሮ መሄዳቸው ግድ ነው፡፡ ታመው ለህክምና የሚመጡም እንዲሁ፡፡ ሌላም ባለጉዳይ ይደመርና የአገልግሎት ጠያቂው ብዛት

ከትንሿ አይሮፕላን አሥራ ሰባት መቀመጫ በላይ ይሆናል፡፡ እንግዲህ በምድር መንገድ በሌለበት አገር በሰማይም ዕድሉ ሲጣበብ የአየር መንገድ ተወካዩ ተገልጋዮቹን እንዴት ሊመርጥ እንደሚችል በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ልምድ በመጠቀም መገመት ይቻላል፡፡ ትሬንታ ኳትሮ ሙሉ ቡና በምድር የላከውም ሆነ ነፍሱ ልትወጣ የደረሰውና ሀኪም የራበው በሽተኛ ማንኛውንም ሕጋዊውንም ሕገወጡንም መስዋዕትነት ከፍለው ለመብረር ወደ ኋላ አይሉም፡፡

የቤጊን የኢትዮጵያ አየር መንገድ ቢሮ ለጊዜውም ቢሆን ወደ ጎን እንተወውና ገርቦሌ በአይሮፕላን አዲስ አበባ ድረስ መጥቶ ከዚያም በአውቶብስ ነቀምት ዘልቆ ቤቱ ከቀድሞው ባነሰ ድካም ለመግባት ወደ አየር መንገዱ ቢሮ አመራ "አዲስ አበባ መሄድ ፈልጌ ነበር ትኬት ስጡኝ" አለ አገልጋዩ፡፡

"አይሮፕላኗ ከመጣች ሰነበተች በረራ የለም" ሲል መለሰ ቀብራራውና ብቸኛው የአየር መንገዱ ሠራተኛ ሙት ወቃሽ አያርገኝና፡፡ እንደ ገርቦሌ ሁሉ ስለ በረራ ለመጠየቅ የመጡና የለም ቢባሉም ተስፋ መቁረጥ አቅቷቸው እዚያው የቆሙ ሰዎች ነበሩ፡፡ ገርቦሌ "በረራ የለም" ሲባል ወደ መጣበት አልተመለሰም፡፡ ጥቂት አሰበና የተሰበሰቡት ሰዎችና ከእርሱ ጋር የነበሩት ቅዱሳን እያዩት ሁለት እስኪቢርቶዎች ከኪሱ አወጣና እያፋጨ እንደ ሞባይል ይዞ "ሀሎ አዲስ አበባ ሀሎ ጅማ ይሰማል ሀሎ አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ የአየር መንገድ ቢሮ ነው አይደል በአስቸኳይ አይሮፕላን ላኩ ብዙ ሰው ነን ተቸግረን እየጠበቅናችሁ ነው" ብሎ ካበቃ በኋላ "አይሮፕላኗ





ዛሬ ትመጣለችና ጠብቁ" አላቸው አብረውት ያሉትን መንገደኞች፡፡ የአየር መንገዱ ቢሮ ሠራተኛ ለማረጋገጥ ቴሌግራሙን ቢሞክር አይሰራም፡፡ ማንም ገርቦሌን አላመነውም "ተዉ አይሮፕላኗ ትመጣለች ወደ አየር ማረፊያው እንሂድ" አለ ዳግመኛ፡፡ "አንተ ከቢሮ ሠራተኛው የበለጠ ታውቃለህ?" ሲል አንደኛው መንገደኛ አንጓጠጠው፡፡ ከችግራቸው የተነሳ የማይታመነውን ለማመን የዳዳቸው አንዳንዶች "እስቲ ቴሌግራሙን ደጋግመህ ሞክረው" አሉት ከብዙ ሙከራ በኋላ ከአዲስ አበባ በቴሌ ግራሙ ውስጥ ድምፅ መጣ ከአዲስ አበባ ቤጊ በረራ እንዳለ የሚናገር ድምፅ፡፡ ሊላ ሰው ሊሸኝ በመጣ መኪና ተሳፍሮ ገርቦሌም ወደ አየር ማረፊያው ከዚያም ወደ አዲስ አበባ በረረ፡፡

# የምሪት አገልግሎት

"ደጆቹ ተዘግተው ሳሉ ኢየሱስ መጣ" /ዮሐንስ 20፡26/ ቾምቤ በሚኖርበት የነጆ ከተማ ሕዝብ አድሞበታል፡፡ መተዳደሪያው የሆቴል ንግድ ስለሆነ "የጴንጤ ሆቴል አትግቡ" ተብሎ ከሊቅ እስከ ደቂቅ አድመውበታል፡፡ ነቢዩ በዚያ እንደሚያልፍ የሰማው ቾንቤ አገሩ እንዳመፀበትና ሆቴሉ እንደተዘጋ ጌታ ባልቃ እንዲገባ እንዲፀልይለት ለመነው፡፡ "ጌታ ስመለስ ቃል ይሰጠኛል አሁን ምንም የምልህ ነገር የለኝም" ይለውና ይለያያሉ፡፡

አገልግሎቱን ጨርሶ ሲመለስ ቲኬት የቆረጠው በዘላቂ መኪና ቢሆንም ቾምቤ ከተማ ሲደርስ "ጌታ ሆይ ልለፍ ወይስ ልውረድ" ብሎ ጠየቀ፡፡ "ውረድና መልስ ስጠው" ነበር የጌታም ምላሽ፡፡ ወረደና የተዘጋውን ሆቴል ፈለገ፡፡ መቼም በማታውቁት ከተማ ውስጥ ጥሩ መረጃ ማግኘት ከፈለጋችሁ ማግኘት ከምትችሉባቸው ምንጮች ውስጥ ሊስትሮዎችም ይገኛሉ፡፡ እናም ጫማውን እያስጠረገ "የቾምቤን ሆቴል ታውቀዋለህ?" ሲል ልጁን ጠየቀው፡፡ የተጠየቀው ልጅ መልስ ለመስጠት ጊዜ አልወሰደበትም፡፡ "የመቼህን የቾምቤ ሆቴል ተዘግቷል እኮ" ሲል መለሰለት "ለምን ተዘጋ ከስሮ ነው" ሲል ደግሞ ጠየቀ፡፡ "ጴንጤ ስለሆነ እሱ ሆቴል የገባ የተወገዘ ነው" ስለተባለ ማንም ዝር አይልም ስለዚህ ገቢያ አጣና ብቻውን ሲቀር ዘጋው" በማለት ዝርዝሩን አስረዳው፡፡ "አሁን ልታሳየኝ ትችላለህ" በማለት ጫማ አጠረገበት ሂሳብ ላይ ጨመር አድርጎ ሰጠው፡፡ ልጁም እያሳበረ ቾምቤ ሆቴል አደረሰው፡፡





ሲደርስ እውነትም እንደተባለው ዝግ ነው፡፡ ቾምቤና ባለቤቱ መኖሪያ ክፍላቸው ውስጥ በፀሎት በእግዚአብሔር ፊት እያለቀሱ ነበረ፡፡ "እኔ ጌታ ነው የላከኝ" ሲል አመጣጡን አስረዳ፡፡ በመቀጠልም "ጌታ ወደዚህ የተዘጋ ቤት ይግባ ርግማን ይውጣ ሰላም ለቤታችሁ ለኑሯችሁና ለሥራችሁ ይሁን" በማለት የጌታ መንፈስ ያመጣለትን ተናገረ፡፡ እያፅናናቸውና እያጫወታቸው እዚያው የተዘጋው ሆቴል አደረና ጧት "አሁን ጌታ ወደተዘጋው ቤታችሁ መጥቷልና ተነስታችሁ አፀዱ ከፍታችሁ ሥራችሁን ቀጥሉ ባላቸው መሰረት ሆቴሉ ተከፍቶ ሥራ ተጀመረ፡፡ ቀድሞ ሰይጣን አትሂዱ ያላቸውን ሰዎች ኢየሱስ ሂዱ ስላላቸው መጉረፍ ጀመሩ፡፡ ከበፊቱ የበለጠ ሆነ ሥራቸው ተቃና ያ ሆቴል አሁን በከተማው ውስጥ አለ የሚባል ሆቴል ሆኗል፡፡ የሚጠፋው መስተንግዶ እንጂ ገቢያ አይደለም፡፡

"የዳዊት መክፈቻ ያለው የሚከፍት የሚዘጋም የሌለ የሚዘጋ የሚከፍትም የሌለ..." (ራዕይ 3፡7)

እንደልማዱ ከቤቱ ከጊዳ ተነስቶ ነቀምት ያድርና ወደ ሚቀጥለው ያገልግሎት ጉዞው በማለዳው አውቶብስ ለመጓዝ የሚያድርበትን ካመቻቸ በኋላ ፀጉሩ አድጎ ስለነበረ ለመስተካከል ወደ ደንበኛው ፀጉር ቤት ጎራ አለ፡፡ ፀጉሩን እየተስተካከለ ከእግዚአብሔር ዘንድ መልዕክት መጣለት፡፡ ወደ አንድ የሚያውቀው ቤተሰብ በፍጥነት መሄድ አለበት፡፡ ቤቱን ስለማያውቀው የፀጉር ደንበኛውን ቢጠይቀው የተባሉትን ሰዎች እንደሚያውቃቸው ስለነገረው ሊወስደው ተስማሙና ይዞት ሄደ፡፡ ሲደርስ ቤቱ ዝግ ነው

ወደበሩ ጠጋ ብሎ ግድግዳው ሥር ተቀመጠ፡፡ "ተነስ እንጂ እንሂድ ሰው የለም እኮ" አለው ያመጣው ሰው "ቤቱ መዘጋቱን እያወቀ ሂድ ያለኝ ጌታ ስለሆነ እዚሁ እቆያለሁ አንተ ሂድ" አለውና ፀጉር አስተካካዩ ወደሱቁ ፈጠነ፡፡

የልጁ አባት ሀኪም መኮንን እንደሚሉት "እኛ በቤታችን ጌታን ስለምናመልክ ያካባቢው ሰዎች አይወዱንም ነበር፡፡ ስለሆነም እኛ ባልጠረጠርንበት ሁኔታ ህፃኑን ለማይገቡ ሰዎች ትተን ወደ ሥራ በሄድንበት ወቅት በጡጦው ውስጥ መርዝ አድርገው ስለሰጡት የሚመገበው አልረጋ እያለ ያስመልሰዋል በመርዙም አለመሞቱ ገርሞኛል፡፡ ቢሆንም መዳን አልቻለም፡፡ በጣም ተቸገርን አለም የለምም የማይባል ልጅ ሆነብን፡፡ በዚህ መሀል ነበር ነብይ ገርቦሌ ስለሁኔታው እግዚአብሔር ነግሯቸው ቤታችንን ፈልገው የመጡት፡፡" የሞተ ያህል ምንም የማይሰማና የማይለማውን ሕፃን ታቅፈው ተዘግቶ ወደነበረው ቤታቸው አገቡት፡፡ ቤተሰቡ እያለቀሰ እያለ የተላከው የእግዚአብሔር ባሪያ ልጁን ተቀብሎ ታቀፈና ወዲያ ወዲህ እያለ በልሳን መፀለይ ጀመረ፡፡ የሕፃኑ ነፍስ ተመለሰች መንቀሳቀስ ጀመረ፡፡ ዳነ፡፡ አይኑን ገልጦ መጫወት ጀመረ፡፡ "የሞት መንፈስ ከቤታችሁ ሄዷል ጌታን አመስግኑ ደህና እደሩ ብሎ ተነሳና ልጁን ለወላጆቹ ሰጣቸው፡፡ "እባክህ እደር ብላ ጠጣ ቢሉትም ግብዣውን በሙሉ አልተቀበለም፡፡ "የመጣሁት ለዚህ ብቻ ነው እንጂ ብላ ጠጣ እደር አልተባልኩም፡፡" ብሎ ተሰናብቶ ወጣ፡፡ ያ ልጅ አሁን የአምስተኛ ክፍል ተማሪ ነው፡፡





በአሦሳ የሚኖሩት መምህር ነገሰ ኦሊቃና ባለቤቱ ወ/ሮ ባፌች አኩማ ከተጋቡ አምስት አመት ያለፈ ቢሆንም እንኳ በባህሉም ሆነ በጋብቻ አለም ቀጥሎ የሚሆነው ነገር አልሆነላቸውም፡፡ ልጅ አላገኙም፡፡ ቀስ በቀስ የፍቅር መቀዝቀዝና መጋጨት መከሰቱ አልበቃ ብሎ አንድ ሌሊት እሷ ከፉኛ ታመመች፡፡ ያለማቋረጥ ደም እየፈሰሳት መኝታውና ልብሱ ሁሉ በደም ተጥለቀለቀ፡፡ ባለቤቷ ብቻውን የሚቻለውን ሁሉ በማድረግ እንዲሁ በጭንቀት እያሉ ሊነጋጋ ሲል በራቸው ተንኳኳ፡፡ በዚያ ሰዓት የሰው በር ማንኳኳት የነበረባቸው በችግር ያሉት እነሱ ናቸው፡፡ ችግርና ስቃያቸውን በቤታቸው ችለው አደሩ እንጂ፡፡ አሁን ያንኳኳው ጌታ ነው ባሪያውን ልኮ፡፡ "ክፈትልኝ እኔ ገርቦሌ ነኝ ጌታ ልኮኝ ነው የመጣሁት" አለው፡፡ መምህሩ በሩን ሲከፍት መጋቢ ከሊፋ ኤሊያስና ገርቦሌ በበሩ ላይ ቆመዋል፡፡ ወደ ውስጥ ገቡ ገርቦሌ ወደ አልጋው ሲያመራ በደም የተጨማለቀውን ልብስና ፍራሽ እንዳያይበት ተሳቅቆ እንዲቀመጡ ለማድረግ ቢግደረደርም በቀጥታ ወደ ባፌች ተጠግቶ "እኔ እግዚአብሔር ልኮኝ ነው የመጣሁት ጌታ ኢየሱስ እንደሚፈውስ ታምናላችሁ? ትንሽ ዘይት አምጡልኝ" አለ፡፡ ዘይቱን ሰጡት ፀለየና ቀባት፡፡ ከዚህ በኋላ የሚፈስ ደም አታይም የዛሬ አመት ደግሞ ልጅ ወልደሽ ትታቀፊያለሽ" ብሏት ወጥተው ሄዱ፡፡ እንደተባለው ደም መፍሰሱ የአገልጋዮቹ እግር እንደወጣ ቆመ፡፡ በአመቱ በፀሎት ነገሥ ተወለደች፡፡ በፀሎት በ2003 ዓ.ም የዘጠነኛ ክፍል ተማሪና በቤተክርስቲያን ውስጥ በዝማሬ የምታገለግል ወጣት ናት፡፡

እዚያው ቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ ታህሳስ 1999 ዓ.ም በሄደ ጊዜ መጋቢ ዮሐንስን "ልጅ መውለድ እየፈለጉ ያላገኙና መካን የሆኑ አማኞችን ጥራልኝ ጌታ ሊጎበኛቸው ይፈልጋል" አለው፡፡ መጋቢውም በስልክም በመልዕክትም የሚያውቃቸውን መካኖች አገልጋዩ ወዳረፈበት ወደ ራሱ ቤት ጠራ፡፡ ተፀለየላቸውም፡፡ በአመቱ ልጅ ከታቀፉት ውስጥ አስፋው ማሞና ራህማ ተማም የተባሉት ባለትዳሮች ይገኙበታል፡፡ የተወለደውን ልጅ በረከት አሉት፡፡

አሶሳ ደርሰን የመጋቢ መኮንን ምስክርነት ሳንሰማ መመለስ አይገባንም እንስማው፡-

"ከነብዩ ገርበሊ ጋር ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ አብረን ባገለገልንበት በርካታ ድንቅና ተዓምራት የተፈፀሙ ቢሆንም ያን ሁሉ ለመተንተን ሁኔታው አይፈቅድም፡፡ ለየት ካሉት ውስጥ ጥቂቶቹን ለእግዚአብሔር ክብርና ለአገልጋዩም ትክክለኛ የእግዚአብሔር ባሪያነት ማስረጃ እንዲሆኑ እጠቅሳቸዋለሁ፡፡ አንድ ምሽት እኛ ወዳረፍንበት ቤት መጥታ "ባሌ አያምንም አጋንንት አምላኪ ነው፡፡ ለክፉ መናፍስት የሚሆን መስዋዕት እንዳዘጋጅ ስለሚያስገድደኝ በዚህ ነፍሴ በጣም ተጨንቃለች እባካችሁ ባለቤቴ እንዲያምን ፀልዩልኝ" አለች፡፡ የእግዚአብሔር ሰው በአጠገባችን የነበረውን ዲያቆን "ያንን የማገዶ እንጨት አምጣው" አለውና የማገዶውን እንጨት ጠረጴዛ ላይ አጋደመው፡፡ ሴትዮዋን የባሏን ስም ጠየቃትና ነገረችው፡፡ "ይህ እንጨት በዚህ የሌለው የባልሽ ምሳሌ ነውና ባሌነው ብለሽ እመኚ" ሲላት "እሺ አምናለሁ" አለች





ወደኛ ዞር ብሎ "እናንተስ ታምናላችሁ" ብሎ እኔንና ዲያቆኑን ጠየቀ፡፡ ዲያቆኑ ወደ እንጨቱ እየተመለከተ በንቀት ሳቀ፡፡ ነቢዩም "ጌታ ኢየሱስ የሞተችውን ልጅ ለማስነሳት ወደ ቤት በገባ ጊዜ ያሾፉትን እንዳስወጣቸው አንተም ባለማመን ስቀሀልና ውጣ" ብሎ አስወጣው፡፡

እኔና ነብዩ ሴትየዋ ሦስታችን ሆነን ጠረጴዛ ላይ በተጋደመው ማገዶ ላይ እጃችንን ጭነን ፀለይንና እንጨቱን ወደ አንድ ጥግ አስቀመጥኩት ከሁለት ቀን በኋላ ያ አስቸጋሪ ሰው እኛ ወዳረፍንበት ቤት ቁርስ ልንበላ ተዘጋጅተን ሳለ መጣ፡፡ ስለወንጌል ነገርነው፡፡ ጥያቄ የሆኑበትን ነገሮች እያነሳ ከተነጋገርን በኋላ እውነቱ ገባውና ጌታን ለመቀበል ተስማማ፡፡ የቤቱ ሰዎች እንጂ እኛ የሰውየውን ማንነት እስከዚህ ሰዓት ድረስ አላወቅንም ነበር፡፡ "ይህ ሰው እኮ የማገዶ እንጨት አጋድማችሁ በስሙ የፀለያችሁለት ነው" ሲሉን በመገረም ጌታን አመሰገንን፡፡ ሴትዮዋም በማግስቱ መጥታ ሌሊት ዘጠኝ ሰዓት ተነስቶ "እንፀልይ መዝሙርም ዘምሪልኝ" አለኝ ብላ ነገረችን፡፡ ያም ሁኔታ ለብዙዎች እምነትና ለማያምኑም መዳን ምክንያት ሆነ፡፡

በሌላ ጊዜ እኔ በብዙ የጠላት ውጊያ ውስጥ በነበርኩበት ወቅት ብዙ ነገሮች ተመሰቃቅለው ነበር፡፡ ነብዩ ወደ አሶሳ ለአገልግሎት በመጣ ጊዜ "እንድፀልይልህ እግዚአብሔር ልኮኛል" ብሎ ወደ ቤቱ መጣ፡፡ ከፀለይልን በኋላ እግዚአብሔር የጠላትን ሥራ አፍርሷል ለምልክት እንዲሆንህና እንድታምን ኑ ወደ ውጪ እንውጣ በደጅ እባብ እናገኛለን ትገድለዋለህ፡፡ አለኝና ከባለቤቴ ጋር ሆነን

ሦስታችን ወደ ደጅ ስንወጣ እባብ መጣ "በሉ ግደሉት" አለን ቀጥቅጠን ገደልነው፡፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እንደ እግዚአብሔር ሰው ቃል ብዙ ውስብስብ የሆነ የጠላት አሠራር እየፈረሰ የተበላሹ ነገሮች እየተስተካከሉና እየተቃኑ መጡ፡፡

በደርግ ዘመን አንዲት ሕፃን ታማ እንድንፀልይ ተላከብንና ሄድን፡፡ እናትየዋ ቀድማ በጌታ የነበረችና ደከማ የደርግ ባለስልጣን ያገባች ሴት ነበረች፡፡ ሕፃኗ በህክምና አልድን ስላለች ነበር በመጨረሻ ቀድሞ የምታውቀውን ጌታን ለመሞከር የመጨረሻው ተሞክሮ ሀኪም እንዲሆን የኢሰፓ አባል የሆነው ባሏ የፈቀደላት፡፡ ነብዩ ቃል እየሰበከ በመሀል አቋረጠና "እግዚአብሔር እንዲህ ይልሀል ሕፃኗስ አትሞትም ነገር ግን አንተ ዛሬ አሁን ራስህን ለጌታ ካልሰጠህ በቅርብ ቀን ትሞታለህ፡፡" ሲለው ሰውየው ውሃ ሆነ "አሁን እኔ ላንተ ብፀልይና ንስሀ ብትገባ ልጅቷም ትድናለች በአንተም ላይ መጥቶ በደጅ የቆመው ሞት አፍሮ ባዶ እጁን ከቤታችሁ ይመለሳል እያለው ሳለ ሰውየው አልቅሶ ንስሀ ገባ ልጅቷም ዳነች እናቷም ከኩብለላዋ ተመለሰች፡፡

አንድ ጊዜ ለአገልግሎት ወደ ደምቢደሎ ሄደን በዚያ እያለን ከምሽቱ አራት ሰዓት አካባቢ ስልክ ተደወለ፡፡ የተደወለው ከጌዶ ሲሆን ቀደም ሲል በጌታ የነበረና ኋላ የደከመ የፖሊስ ባልደረባ በጠና ታሞ ፖሊስ ሆስፒታል በህክምና ሲረዳ ከቆየ በኋላ እንደማይድን ይልቅስ አስከሬን ከማጓጓዝ ከነነፍሱ በፍጥነት ወደ ቤቱ እንዲወሰድ ስለተመከሩ ዘመዶቹ ወደ ቤት አምጥተውት ካሁን





አሁን አረፈ እያሉ በመጠባበቅ ላይ እያሉ ነበር የፀሎት እርዳታ ፈልገው ለነብዩ የደወሉት፡፡ የእግዚአብሔር ሰው ትንሽ ከፀለየለት በኋላ "ስልኩን ስጡት" አላቸው፡፡ ሰዎቹም ምንም መንቀሳቀስ አይችልም ያለው በጣር ነው ምግብ ከቀመሰም እንኳ አሥራ ሁለት ቀን ነው፡፡ የሰነበተው በግሉኮስ ሲሆን አሁን እሱም ተነቅሏል ማናገርም አይችልም፡፡" ሲሉ ታማሚው ያለበትን ሁኔታ ለማስረዳት ሞከሩ፡፡ ነብዩም "ስልኩን ጆሮው ላይ ያዙለት ብሎ ጆሮው ላይ እንደያዙለት ብዙ መልዕክት ነገረው እንዴትም ከጌታ ቤት እንደኮበለለ ጭምር ሲነግረው የማይለማና የማይሰማ የነበረው ሰው ስቅስቅ እያለ ያለቅስ ጀመር፡፡ መደማመጥ በጀመሩበት በዚህ ሁኔታ ላይ እያሉ "በጌታ በኢየሱስ ስም ተነስና ተመላለስ" ሲል አዘዘው፡፡ እንደተባለውም ተነስቶ ባስታማሚዎቹ መሀል መንጎራደድ ጀመረ፡፡

ከቅርብና ከሩቅ የመጡ ዘመድ አዝማድ ሆስፒታል አቅቶት ተመለሰ ሲባል ወሬውን ለማየት የመጡ የአካባቢ ሰዎች በሁኔታው ተደንቀው የሚያምኑት ጌታን እያመሰገኑ ሲዘሉ ሌላው በመገረም አይናቸውን አንዴ ወደተኛበት ቦታ አንዴ ወደቆመው ሰው እያደረጉ ተደነቁ፡፡ ተነስቶ የቆመው ህመምተኛ አሁንም ስልኩን ጆሮው ላይ እንደያዘ ነው "አሁን ምግብ ብላ ለሰላሳ ጠማና ከሠላሳ ደቂቃ በኋላ ደውልልኝ" ተባለ፡፡ ከሠላሳ ደቂቃ በኋላ ደወለና ገናኘ ሳይቀር የተዘጋጀለት ሞቱ የሚጠበቀው ሰው "ዘመዶቼንና ከቅርብ የመጡ ጎረቤቶቼን ሸኝቼ መግባቴ ነው" ብሎ በስልክ ለነብዩ ሲናገር አብረን ሰምተን እግዚአብሔርን አከበርን፡፡

የእኔ ባለቤት ለአስራ አራት አመት ያህል በከፍተኛ ሕመም ስትሰቃይ ቆይታ በመጨረሻ የማህፀን ዕጢ ነበረባትና ወደ ካንሰር እንደተለወጠ ከሀኪም ተረዳን፡፡ ከዚህ የተነሳ ከአሰላ አዲስ አበባ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ድረስ ብዙ ጊዜ ተመላልሰናል፡፡ በአመት ሁለቴም ሦስቴም እንመጣ ነበር፡፡ በዚያ ላይ በመኪና መጓዝ አስቸጋሪና ከህመም ጋር የማይሄድ በመሆኑ ብዙውን ጊዜ በአይሮፕላን መምጣት ነበረብንና ይህ ሁሉ ሆኖ ካንሰር ደረጃ መድረሱ ተስፋ አስቆረጠን፡፡

በመጨረሻ ዶክተሩ ከአምስት ቀን በኋላ የማህፀን ቀዶ ጥገና እንደሚደረግላት ነገራት፡፡ እኔም ሁኔታው በጣም ስለከበደኝ ስልክ ለነብዩ በመደወል ያለሁበትን ችግር ነገርኩት፡፡ እሱም ለቀዶጥገናው ሁለት ቀን ሲቀረው ደውሎ "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ቢላዋ አያርፍባትም በሽታው ሁሉ የለም ከእሷ ላይ ተነስቷል ነገ ሆስፒታል ሂዱና አረጋግጡ እኔም ነገ ወደናንተ እመጣና ጌታን አብረን እናመሰግናለን" አለን፡፡ እንደተባልነው በቀጠሮው ቀን ወደ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ሄድን፡፡ ከቀዶጥገናው በፊት መደረግ ያለበትን የመጨረሻ ምርመራ ዶክተሩ አደረገ፡፡ ውጤቱ ላይ ሲደርስ ሦስት ነገሮችን እያየ ግራ በተጋባ ሁኔታ ብቻውን ያወራል፡፡ ባለቤቴን ያዩል ደግሞ የብዙአመት የበሽተኝነት ፋይሏን ያገላብጣል በመጨረሻም ምንም በሽታ የማያሳየውን የጤንኝነቷን ውጤት ያመሳክራል፡፡

"የሚገርም ነው የመጨረሻው ውጤት ምንም አይነት የማህፀን በሽታ አያሳይም ፍፁም ጤነኛ ስለሆንሽ ቀዶጥገናው አያስፈልግሽም





በሰላም ወደ ቤትሽ ሂጂ" አላት፡፡ "ምነው ዶክተር ባለፈው ካንሰር ደረጃ ደርሷል ያልከኝ አንተ አይደለህም" ስትል ብትጠይቀውም "እርግጥ ነው ብዬሽ ነበር አሁን ግን የለም የኔ እህት አስራ አራት አመት በሽታ አለብኝ እንዳልሽ ሁሉ ዛሬ ደግሞ ጤነኛ ነኝ ብለሽ ራስሽን አሳምነሽ ሂጂ" አላት እውነትም ባለቤቴ ከዚያ በኋላ ፍፁም ጤነኛ ሆነች፡፡

እኔ ነብይ ገርቦሌ ቤት በእንግድነት አድሬ ሳለሁ ያለማቋረጥ ለብዙ ሰዓታት በስልክ ለተለያዩ ሰዎች አገልግሎት ይሰጥ ስለነበር መድከሙን እኔና ባለቤቱ አዲ ስለተመለከትን እረፍት እንዲያደርግ ስልኩን ዘጋነው፡፡ ነገር ግን ቆይቶ ከምሽቱ ወደ አራት ሰዓት ላይ "እባካችሁ ይህ ስልክ ይከፈት" ሲል ለመነን፡፡ እኛም እግዚአብሔር ተናግሮት ይሆናል ብለን ከፈትንለት፡፡ ወዲያው ስልኩ ሙሽ ሲያነሳው በከፍተኛ ችግር ውስጥ ከነበረ ቤተሰብ ነበር የተደወለው፡፡ የቤተሰቡን ሚስጢር መናገር ባያስፈልግም እግዚአብሔር ያንን ቤት በዚያ ምሽት ከጥፋት ታደገ፡፡"

# መታዘዝ ሲያፈራ

ከገርቦሌ ህይወት አስቀድሞ እግዚአብሔር የፈለገው ነገር መስራትንና መታዘዝን ለፈቃዱ ማደሩን ነበርና ይህ በሆነ መጠን ቀስ በቀስ የችግር ደመና እየገፈፈ መብላትም መጠጣትም መልበስም ጀመረ፡፡ ሁለት ሙሉ ልብስ ነበረውና እንደውም በላዩ ላይ ሊጨምር "ጌታ ሆይ ለየት ያለ አንድ ሙሉ ልብስ ስጠኝ" ሲል ጠየቀ፡፡ መልሱ አልዘገየም "እነዚህንም ለአረጋና ለሀይሌ ትሰጣለህ" የሚል፡፡ ወዲያው ወ/ዊ አረጋና ወ/ዊ ኃይሌ በደጅ የነበሩ ያህል የሰላምታ ድምፅ እያሰሙ ወደቤት ገቡ "ወደ አገልግሎት እየሄድን ነበር፡፡ ነገር ግን ህዝብ ፊት ለብሰን የምንቆምበት ሙሉ ልብስ ያስፈልገናልና እባክህ ፀልይልን ጌታ እንዲያዘጋጅልን" አሉት፡፡ "አልፀልይላችሁም የምትፈልጉትን ልብስ እግዚአብሔር አዘጋጅቷል ላለቀ ነገር ምን ፀሎት ያስፈልጋል?" በማለት አውጥቶ አንዳንድ አከፋፈላቸው፡፡ ወደነቀምት ሊሳፈርበት በኪሱ መቶ ብር ነበረውና "ሃምሳ ሃምሳ አከፋፍላቸው" የሚል ተጨማሪ ድምፅ መጣ፡፡ የተባለውን ሁሉ አድርጎ በባዶ እጁ ወደ አዲስ አበባ ለመሄድ ወደ መነሀሪያ አቀና፡፡

በኪሱ የነበረው አንድ ብር ብቻ ነበር፡፡ "ገንዘብ በኪሴ ባይኖር እግዚአብሔር በዙፋኑ አለ፡፡ በማለት "ነቀምቴ የሚሄደው መኪና ውስጥ ገባና ቁጥር ሁለት ወንበር ላይ ተቀመጠ፡፡ መኪናው ተነሳ ወደኋላ የሚያውቀው ካለ በማለት ለማየት ዞር ቢል አንድም የለም፡፡ እያሰላሰለ እንቅልፍ እንደያዘው መስኮቱ ላይ ደገፍ ብሎ ጉዞውን ቀጠለ፡፡ ገንዘብ ተቀባዩ ሂሳብ መሰብሰብ ጀምሯል ከአንድ ቁጥር





ወንበር ላይ ተቀብሎ ወደ ሁለት አለፈ እኚህኛው ተሳፋሪ ተኝተዋል ኋላ ሲነቁ እቀበላቸዋለሁ ብሎ ላለመረበሽ ወደ ቁጥር ሦስት አለፈ፡፡ መጨረሻው ወንበር ድረስ ተቀበለ፡፡ ሁለተኛ ዙር "መልስ ያላችሁ" እያለ ከደረሰኛቸው ጀርባ የፃፈውን እየሰረዘ መልስ ሰጠ፡፡ ወጨ ወራጅ ሥራ አበዛበት፡፡ ጉቲን ደረሱ፡፡ የቁርስ ቦታ ስለሆነ ሰው ሁሉ ለቁርስ ወረደ፡፡ ገርቦሌ አንድ ነገር አሰበ መንገድ ላይ ከሚያዋርደኝ እዚህ ከተማ የማውቃቸው ወገኖች ፈልጌ ልክፈለው አለና ተሳፋሪዎቹ እስኪመለሱ በሩን ለመቆለፍ ለቆመው ረዳት ጠጋ ብሎ "እኔኮ ሂሳብ አልከፈልኩም" አለው "አይደለም አንድ ሰው አንዶዴ ላይ ከፍሎልህ ወርዷል" ሲል የምስራች ነገረው፡፡ "ምን አይነት ሰው ነው?" መልሶ ጠየቀ፡፡ "እኔ ከገንዘቤ እንጂ ከመልኩ ምን አለኝ አይነቱን አላስታውስም" መጀመሪያ ያልነበረ ሰው ከየት መጥቶ ከፈለ ሰው ይሆን መልዓክ እየተገረመ ነቀምት ገባ፡፡

በኪሱ የነበረችውን አንድ ብር መነዘረና ሃምሳ ሳንቲሙን አንድ ኪስ ሌላውን ሃምሳ ሌላ ኪስ ከቶ "ይህ መቶ ሳንቲም መቶ ብር ይሁን" ብሎ ነበርና የተናገረው እስኪፈፀም መንገድ ላይ ወዲያ ወዲህ ሲንጎራደድ ከቃቄ ወደ አዲስ አበባ ሲጓዙ ነቀምት ያደሩ ባልናሚስት ወደ ሆቴል ሲያመሩ አዩትና ጠርተው ሰላምታ ተለዋወጡ፡፡ "እባክህ ና! ምሳ አብረን እንብላ" ሲሉ ጋበዙት፡፡ "አይ እኔ ሰው እየጠበቅሁ ስለሆነ ጌታ ይባርካችሁ እናንተ ሂዱና ብሉ" በማለት ግብዣውን በትህትና አመስግኖ ለመለየት ፈንጠር አለ፡፡ ሁለቱ ተመካከሩና መቶ ብር ሰጥተውት ሂዱ፡፡ አሁን መቶ

ሳንቲሞቹ ሥራቸውን ስለጨረሱ ለለማኝ ሰጥቶ በምትካቸው ሃምሳ ሃምሳ ብሮችን ተካ፡፡

በማግስቱ ጉዞ ወደ አዲስ አበባ ሆነና አመሻሽ ላይ ገባ፡፡ ወ/ዊ ገብሩ ወልዱ እየፈለገው እንደነበር ስለሰማ በመደዋወል ተገናኙ፡፡ "በጣም ስፈልግህ አገኘሁህ ወንድሜ ጀርመን ሄጄ ፈረንጆች "GERBOLE" ምንድነው ያገር ወይስ የሰው ስም ይሁን አላወቅንም አፍሪካ ውስጥ እንዲህ አይነት ስም ካወቅህ እባክህ እርዳን ብለው ጠየቁኝ እኔም የሰው ስም እንደሆነና ኢትዮጵያ ውስጥ የሚያገለግል ወ/ዊ ስም መሆኑን ነገርኳቸውና እባክህ አድርስልን ብለው አደራ ሰጡኝ ላንተ የመጣ ነው ሰዎቹን እያዘዘ የስምህን ፊደላት ያፃፉቸውና እንዲልኩልህ የነገራቸው ራሱ እግዚአብሔር ነው" በማለት ስሙ የተፃፈበትን ትልቅ የተቆለፈ ሻንጣ ከነቁልፍ አስረከበው፡፡

ሁለት ሙሉ ልብሱን ጊዳ ላይ ሰጥቶ መለወጫ ሸሚዝና ካልሲ በፌስታል አንጠልጥሎ ካገሩ የወጣው የእግዚአብሔር ባሪያ ትልቅና ከዚያ በፊት ያንን አገር ረግጦ የማያውቅ ሻንጣ አሸክሞ ከመነሀሪያ ወደ ቤቱ አመራ፡፡ ከአዲ ጋር ጌታን ስለሆነው ነገር አመስግነው ሻንጣው ሲከፈት አምስት ሙሉ ልብስ አሥራ ሰባት ሸሚዝ አሥራ ሁለት ከረባት ለአዲ ሹራብና ጃኬት ነበረበት፡፡ አዲም ብትሆን ሳትሰጥ አይደለም እነዚህን ያገኘችው ሙሉ ልብሱን ስለመስጠቱ ሲነግራት "ምን ችግር አለው ጌታ ካዘዘ" ብላው ሳለ አንዲት እንጨት የምታመጣላት ሴት "እባክሽ ገቢያ ስወጣ የምለብሰው ቀሚስ አጣሁ አውሽኝ" አለቻት፡፡ እግዚአብሔርን





ስመታዘዝ የምትወደውን ቀሚስ አውጥታ ሰጥታ እኩል ባዶ ሆነው ነበር፡፡

የሚያምን ሰው ይታዘዛል፡፡ እምኖ የታዘዘ ሰው እግዚአብሔርን ያዛል፡፡ እግዚአብሔርም ይታዘዛል፡፡ እምኖ የሚታዘዝ ሰው ልመናውም ለእግዚአብሔር ክብር በሆነ ጉዳይ ላይ ስለሆነ እግዚአብሔርም ያደርገዋል፡፡ "ይህ ወጡ ሳይወጠወጥ ወስከንባው ቂጢጥ" እንደተባለው ራሳቸውን ለመንፈሳዊው አለም ሳይገሩ ስለራሳቸው ብልፅግና እግራቸውን እያነሱ "እዘዙኝ ብኋል እናዘዋለን" የሚሉትን ጥራዝ ነጠቆች አይመለከትም፡፡ ስለ እምነት ጀግኖች ግን "…እነሱ በእምነት መንግስታትን ድል ነሱ ፅድቅን አደረጉ የተሰጣቸውን የተስፋ ቃል አገኙ የአንበሶችን አፍ ዘጉ የእሳትን ኃይል አጠፉ ከሰይፍ ስለት አመለጡ ከድካማቸው በረቱ በጦርነት ኃይለኞች ሆኑ የባዕድ ጭፍሮችን አባረሩ" (ዕብራውያን 11:33-34)

የእናቱ ዕድሜ እየገፋ መሄድና በዚያው አንፃር ያለማመን ጭፍሮች አለመባረር አሳሰበውና "ጌታ ሆይ ዘመኑ እየረዘመ ሄደ እናቴም እስካሁን አልዳነችም እስከመቼ ነው ሳታምን የምትኖረው ድንገት ልንለያይ እንችላለን ይህ ዕድል በእጃችን እያለ እባክህ አንድ ነገር አድርግ" ብሎ ለመነ፡፡

የጌታ መንፈስ "ሥልጣንህን ተጠቀም" አለው፡፡ ስልጣኔን እንድጠቀም ከተፈቀደ በማንኛውም በምናገረው መንገድ ሁሉ ተዐምር ይሆናል ስለዚህ በተዐምር ታምናለች ማለት ነው" አለና

አሰበ፡፡ እናቱ እባብ በጣም ይፈራሉ፡፡ እናም ለአዳነች "ዛሬ ወደ እናቴ ቤት እባብ ይመጣል" አላት "እንዳይበላቸው" አለች፡፡ "ይመጣል አልኩሽ እንጂ ይባላል አላልኩም" በማለት ከማስፈራራት ያለፈ ያልተፈቀደለት መሆኑን ነገራት፡፡ "አደራ እንዳይደነግጡ" ስትል ዳግመኛ ለመነችው፡፡

የን ጊዜ ጎረቤት ስለነበሩ እባብ እንደሚመጣ አውቆ በውጪቱ ለመጠቀም ሰፈር ወዲያ ወዲህ ሲል በድንገት እናቱ ጮኹ፡፡ አዳነች ሮጣ ገባች እርሱ ተከተለ፡፡ "ምን ሆንሽ" አለ እናቱን "ቤቱ ትል ገባ" አሉ እባብ ስለሚፈሩ ትል እያሉ ነው ድሮውንም የሚጠሩት፡፡ "ትል አትበይ እባብ በይ" አለ እውነታውን ለማክበድ፡፡ "ስሙን አትጥሪ ይበላኛል" በልመና ተናገሩት፡፡ "እንዳይበላሽ በጌታ በኢየሱስ እመኚ ብዙ ጊዜ ነግርኩሽ እምቢ አልሽ አሁን በዚህ በአንዱ ካላመንሽ ገና ከወንዝ ወደዚህ እየመጡ ያሉ ብዙ አሉ" ሲል መለሰላቸው "መጀመሪያ ይኼንን አውጣልኝና አምናለሁ" አሉ "ግዴለም አንቺ እዚህ ተንበርከኪ አዳነች እንዳይበላሽ ትጠብቃለች" አለ ጭንቅላቱን ግድግዳ ጥግ የአይጥ ጉድጓድ ውስጥ አስገብቶ ሌላው አካሉ ወደሚታየው እባብ እያሳየ፡፡ እንደመጣ ጭንቅላቱን ጉድጓዳው ውስጥ ነበር ያስገባው፡፡ በዚሁ ተስማምተው በእባብ በትርነት አስፈራርቶ ያለማመንን ጭፍሮች ለማባረር እናቱ ተንበረከኩ አዳነች ጠባቂ ሆነች ገርቦሌ ንስሀ አስገባ፡፡ ስልጣኑን ተጠቅሞ ንስሀ አስገባ፡፡ ከሞት ወደ ህይወት የማሸጋገሪያው ተግባር ተፈፀመ፡፡ የወ/ሮ ተረፈች ቤኛ ኃጢአት በኢየሱስ ደም ነፃ ስማቸው በህይወት





መፅሐፍ ተፃፈ በሰማይም በገርቦሌም ጎጆ ደስታ ሆነ፡፡

ከተንበረከኩበት ሲነሱ "እሺ አሁን አውጣልኝ" አሉ ወደ እባቡ እያሳዩ፡፡ ግማሽ አካሉን ጉድጓድ ውስጥ ደብቆ ከፊሉ ውጪ የሆነውን እባብ በጨርቅ ጎትተው ለማውጣት ቢሞክሩም ውጪ ያለው ተጎርዶ ጉድጓዱ ውስጥ ያለው ቀረ፡፡ ምንም ማድረግ ስለማይቻል በላዩ ላይ ጋዝ አፍስሰው እሳት አነደዱበትና ተውት፡፡ ነገር ግን በላዩ ላይ እሳት ቢነድበትም "እኔ እዚህ ቤት አላድርም ጉራጁ ካልወጣ" በማለት አሮጊቷ አስቸገሩ፡፡ ልጃቸው "ተይው እማዬ የፈራሽው ቤትሽ ጉድጓድ ውስጥ የቀረውን ጉማጅ አይደለም እሱ ሕይወት የለውም እኛ ያልነውን ስላደረግሽ አንቺ የምትይውን እናደርጋለን ላንቺ ለመታየትም ቢሆን ወጥቶ ይታይልሻል ትንሽ ጠብቂ" አለና የሞተው ጉማጅ ነፍስ ዘርቶ እስከሚያዩ ድረስ ደጅ መቀመጫ ተሰጥቷቸው ተቀመጡ፡፡

ጉድጓድ ውስጥ በቀረው ግማሽ እባብ ላይ ጋዝ ተጨምሮ እሳት እንዲነደድበትና በመጨረሻም ጉድጓዱ እንደተደፈነ እየታወቀ "ቤቱ ውስጥ ተጎርዶ የቀረው ካልወጣ ይበላኛል" በማለት ከሚገባው በላይ ስላስጨነቋቸው ደግሞም ቀድሞውኑ እሳቸው ስለነፍሳቸው እንዲወስኑ እነገርቦሌ ስለ እባቡ ሀላፊነት ሊወስዱ ስለተስማሙ ግዳጃቸው እናትየዋ በሚፈልጉት መንገድ ዳር መድረስ አለበት፡፡ "እባክህ ጌታ ሆይ ይህ ጎራጅ ተበጣጥሶም ከሆነ ይገጣጠም ሞቶም ከሆነ እንደምንም እዚህ ደጅ ድረስ ካለበተ ይምጣና አሳርፋት" ብሎ ለመነ ትንሽ ቆይቶ ግማሹ አካል በትል ፍጥነት እየተጎተተ ግቢው

ውስጥ ታየ፡፡ በእንጨት ወዲያ ወዲህ ቢያደርጉትም ራሱንም አይከላከልም አይሸሽም የመጣው ለመታየት ብቻ ስለነበር እንደውም ይባስ ብሎ እዛው ሞቶ ቀረ፡፡ ወደ ውጪ በእንጨት ወረወሩትና አሮጊቷን ነፃ ወደሆነው ቤት አስገቡ፡፡

ሌላ ጊዜ አንድ ድንጋይ አንስቶ ሌላ ድንጋይ ላይ ጣለና "የእከሌ ልብ ተሰበረ" አለ ጌታን እንዲቀበል የሚፈልገውን ሰው ስም በመጥራት፡፡ ያ ሰው ትንሽ ቆይቶ በገርቦሌ ደጅ ሲያልፍ ሰላምታ ተለዋወጡና "ግባ ወደ ቤት" ብለው አስቀመጡት ወንበሩን "የዚህ ሰው ልብ ካልተሰበረ አትልቀቀው" ብሎት ነበርና ያ ሰው ለረጅም ጊዜ ቁጭ ብሎ ገርቦሌ የሚነግረውን ይሰማ ነበር፡፡ "መሄድ ኢቃተኝ ልቤ ተሰበረ" አለ "ልብህ ከተሰበረ ተነሳና ሂድ" ብሎ እጁን ይዞ አስነሳው፡፡ ያም ሰው በወንጌል አመነ ባለስልጣን ነበር ያኔ፡፡

አንዳንድ ጊዜ በመደዳ በርካታ አብያተክርስቲያናትን ለማገልገል ይጓዝ ነበር፡፡ በዚህን ጊዜ ከጊምቢ ጀምሮ ነጆ ቡኬ መንዲ አሶሳና ቤጊ ካገለገለ በኋላ ሲመለስ ቂልጡ ካራ ከመንገድ ወጣ ስለምትል ወደዚያ ገብቶ እንዲያገለግላቸው ጌታ አዘዘው፡፡ የእግዚአብሔር ሰው መጥቷል ተብሎ የሰማ ላልሰማ እየነገረ ምሽት ላይ የቤተክርስቲያኗ መሪዎች ሰብሳቢ ግቢ ድንኳን ተጣለና አገለገላቸው፡፡ በማግስቱ መኪና እየጠበቀ እያለ ሁለት የተቸገሩ ሰዎች አሳየውና ካገለገልካቸው አብያተክርስቲያናት ለመንገዱ ከተሰጠህ ሦስት ሺህ ብር ላይ ግማሹን ስጣቸው የሚል ትዕዛዝ አደመጠ፡፡ ወደ ሰዎቹ ቤት ሄዶ ሰጠና ወደጊምቢ ለመሄድ መኪና





ተሳፈረ፡፡ እዚያም ፀሎት ወደሚያስፈልጋቸው ቤተሰብ አሳየውና ጎበኛቸው የሚል ትዕዛዝ ደረሰው፡፡ ሻንጣውን አንድ ወንድም ሱቅ አኖረና ወደተባለው ቤት ሄደ፡፡ "በኪስህ የቀረውን አውጥተህ ስጣቸው" አለው፡፡ ከቤቱ ከወጣ ሁለት ወሩ ነው የቤቱ ባዶነት የልጆቹ ጥያቄ ተንጉዞ ቤቱ መድረሱ እነዚህ ሁሉ ገንዘብ የሚፈልጉ ቢሆኑም ሁሌም በማያጠራጥር ሁኔታ ለሚሰማው ድምፅ ታዘዘ ሰጥቶ ወጣ፡፡ ሻንጣውን ወሰደና አውራ መንገዱ ላይ ቆመ፡፡ "ጌታ ሆይ ወይ የሚወስደኝ መኪና ወይም የምሳፈርበት ገንዘብ ስጠኝ" ከማለቱ ቶዮታ ላንድ ክሩዘር ፊቱ ቆመች፡፡ ሰዎቹን ጊዳ ያውቃቸዋል፡፡ ሰላምታ ተለዋወጡና ወደነቀምት የሚሄድ ከሆነ እንዲገባ ጠየቁት፡፡ አብረው ሄዱ፡፡" አንተ ከመንገድ ነው የምትመጣው" ብለው ራት ጋበዙት የአልጋ ከፈሉለትና አንድ ሆቴል አድረው በማግስቱ ወደጊዳ መሄድ አለመሄዱን ጠየቁት "እሄዳለሁ" አለ በደስታ ቤቱ አደረሱት፡፡

በናፍቆት የሚጠብቁትን ቤተሰቡን ከሳመ በኋላ "ጎረቤት መምጣትህን ሲሰማ ሊያይህ መምጣቱ ስለማይቀር ሳንቲም ካለህ ለቡና ትሰጠኛለህ" ስትል አዲ ጠየቀችው፡፡ ምጥ ያዘው አራቱም ኪሱ ቢገባ ያገኘው አንደኛው ኪስ ውስጥ ተለጥፈው ያመለጡ አራት ብሮች ብቻ ነው፡፡ "እንቺ ለጊዜው ለኋላው ደግሞ ኋላ ይመጣል" አለና ከጭንቀቱ የተነሳ ትንሽ ልፀልይ ብሎ ገለልተኛ ቦታ ፍለጋ ወደ መኝታ ቤት ገባ፡፡ በዚህ ጊዜ አንድ ሰው የገርቦሌን ቤት አሳዩኝ ብሎ እየተመራ እነ አዲ ደጅ ደረሰ፡፡ ወደ ቤት ገብቶ "አንድ ሰው በህልሜ ለቤታቸው ገንዘብ ስለሚያስፈልጋቸው ወስደህ ስጣቸው ብሎ አዞኛል" በማለት ለአዲ የሚያስፈልጋቸውን ያህል ቀደም ሲል

ገርቦሌ በሁለቱ ቦታዎች ለተቸገሩ ሰዋ ከተባለው የሚያጥፍ ገንዘብ ሰጥቶ "ገርቦሌ ከፀሎት ሲነሳ ቤት እንዲመጣ" ብሎ ሄደ፡፡ ለመፀለይ ሳይሆን ከችግር ለመደበቅ ወደ ውስጥ የገባው ሰው ተረጋግቶ ሲወጣ አዲ የሆነውን ሁሉ ነገረችው፡፡ የጎበኛቸውን አዲስ ተመድቦ የመጣ የባንክ ማናጀር ለማግኘት ወደ ባንክ ሄደ፡፡ የማናጀሩ መኖሪያው እዛው ባንኩ ያለበት ግቢ ውስጥ ስለነበር በቀላሉ አገኘው፡፡ "አንተ የእግዚአብሔር ሰው እሱ ለኔ ሥራ ይደክማል ምንም የለውም ብሎ ጌታ ነግሮኛል ለትራንስፖርትና ለልብስ ይሆንሀል በማለት ለብቻ ለዚሁ ያዘጋጀውን ገንዘብ አስረከበው፡፡

ከባንክ ግቢ ሲወጣ አይሱዙ መኪና ውስጥ የነበሩ ሁለት ሰዎች ጠሩትና "እባክህ አገሩን ካወቅህ አንድ ገርቦሌ የተባለ የእግዚአብሔር ሰው ታውቅ  እንደሆነ" ብለው ጠየቁት፡፡ "አዎን አውቀዋለሁ" አላቸው "ቤቱን ልታሳየን ትችላለህ" እሺ ብሎ መኪናው ውስጥ ገባና  ወደ ገርቦሌ ቤት አስነዳቸው፡፡ በሩ ላይ ሲደርስ "ካለ እስቲ ልየው" ብሎ ገባ፡፡ ወዲያው ወጣ ብሎ "አለ ግቡ" አላቸው፡፡ ገቡና ተቀመጡ "የእግዚአብሔር ሰው ቤት ይሄ ነው እሱ የት ነው" ሲሉ በፊታቸው የተቀመጡትን አዲንና ገርቦሌን ጠየቁ፡፡ "የት እንዳለ ንገሪያቸው" አላት አዲን "እሱ ነው" አለቻቸው አብሯቸው የመጣውን ገርቦሌን እያሳየች በጣም በመገረም እንደኤማሁስ መንገደኞች ሆን" አሉ፡፡ ከመኪናቸው ላይ በጌታ ትዕዛዝ የጫኑላቸውን አውርደው ወደ ቤት አስገቡ ገንዘብም ጨምረው ሰጧቸውና መንገዳቸውን ሄዱ፡፡ መታዘዝ ፍሬ አፈራ ብዙ ፍሬ አፈራ፡፡





ሌላ ጊዜ አዱ ወደ ገርቦሌ ጠጋ ብላ ስትፈራ ስትቸር "ገርብዬ በቤቱ ውስጥ እኮ ምንም እህል የለንም" ስትል ጭንቀቷን አጋራችው፡፡ ስለ ጉድለት እሱን መጠየቅ አትፈልግም በነፃነት እንዲያገለግል ነው ሀሳቧ፡፡ ያን ዕለት ግን ደፍራ የቤቱን ባዶነት የዱቄት ዕቃውንና የማቡኪያውን የሌማቱን መራቆት ጨክና ነገረችው፡፡ በኪሱ አስር ብር ነበረው፡፡ "ይመጣል" አላትና እንደሚሸምት ሰው ወደገቢያ ሄደ፡፡ ዕለቱ ቅዳሜ ነው፡፡ በአስሩ ብር የገዛው ጤፍ ወይም በቆሎ አይደለም፡፡ አምስት ባዶ ማዳበሪያ ነው ገዝቶ የመጣው፡፡ አምስቱን ባዶ ማዳበሪያዎች በቃና ዘገሊላ ባዶዎቹን የወይንጠጅ ጋኖች የሞላ ጌታ ይሞላቸዋል አለና ትንቢት ተናገረባቸው፡፡ አመሻሽ ላይ አምስት ማዳበሪያ ጤፍ የተጫኑ አህዮች እየተነዱ በሩ ላይ ደረሱ፡፡ ገጠር የሚያውቁት ያልታሰቡ ገበሬዎች ነበሩ "ልጆች ይሆናል ብለን ነው" አሉና ጭነቱን ፈትተው ወደ ቤት አስገብተው ተሰናብተው ሄዱ፡፡

ሰው እህል የሚያምረው እህል ሲጠፋ ነው፡፡ እህል ሲገኝ ሌላ አብሮ የሚሄድ የጥራትና የአይነት ጥያቄ ይነሳል፡፡ አንድ ጊዜ ቤተሰቡን ያማረው ሥጋ ነበር፡፡ ኬና ትልቋ ልጁ ስጋ አማረኝ አለችና ተነሳች፡፡ የአምሮቷ መነሻ የመስዋዕቱን በግ እግዚአብሔር ያዘጋጃል በማለት አባቷ ካካፈላቸው ቃል ነበር፡፡ "እግዚአብሔር በግ ካዘጋጀ እኔ ሥጋ አምሮኛል በግ ያዘጋጅልናል" ስትል አባቷን ጠየቀችው፡፡ "አዎ ያዘጋጃል" ነበር የአባቷ መልስ፡፡ ይዘጋጃል ከተባለ ምን ይጠበቃል በጧት ተነስተው ቤቱን ማስማመር ሥራ መከፋፈል ሞቅ ሞቅ ማድረግ ነበርና አሟሟቁት፡፡ በእምነት ቤቱ ሥጋ ሥጋ

ሸተተ፡፡ ሽንኩርት በርከት ተደርጎ ተገዛ፡፡ "አንተ የትም እንዳትሄድ እዚሁ ተቀመጥ" ተባለና ወንበር ወጥቶለት አባት ተቀመጠ፡፡ የመታገት ያህል ተጨነቀ፡፡ "ጌታ ሆይ ምን ይሻላል አታሳፍረኝ" ለመፀለይ ሞከረ፡፡ ረጅም ሰዓት ደጅ ደጁን እያየ ጠበቀ "እረ ከጉድ አውጣኝ" አሥር ሰዓት ላይ ትልቅ ሙክት እየነዳ የዘጠኝ ሰዓት መንገድ የተጓዘው ወንድሙ እንደምንዋላችሁ ብሎ ገባ፡፡ ይህ ሰው በጌታ አያምንም ጠጪና አጫሽ ነው ከዚህ በፊት ጴንጤ ይዞ ለቀበሌ ላስረክበ ጠመንጃ ይሸለማል ሲባል ወንድሙን ገርቢሴን እየነዳ ለአብዮት ጠባቂዎች በመስጠት መግሪያ ተሸልሞ የገባው ወንድሙ ሂርጳ ነው፡፡

"የናንተሰው ነው መሰለኝ አንድ ቀይ ቆንጆ ሰውየ ሌሊት በህልሜ ይሄንን ሙክት ወስደህ ካልሰጠሀቸው ከብቶችህ ያልቃሉ አለኝ ፈርቼ መጣሁ" አላቸው፡፡ ሲጠበቅ የነበረውን በግ ወዲያው አርዶ ገፈፈ ሽንኩርቱ ቀድሞውንም ተልጦ ተከትፎ ስለነበር ቀሪው ሥራ ቀለለ ተቀላጠፈ፡፡ አመሻሽ ላይ በዕምነት ቅቅል ቅቅል ጥብስ ጥብስ ዱለት ዱለት የሸተተው ቤት የእውነት ሆነለት፡፡ ያም ሰው ጌታን ተቀብሎ ሲጋራውንና ሀጢአቱን ጊዳ ጥሎ "ጌታን ተቀብለህ ባሮጌ ልብስ አትገባም" አለና ገርቢሴ የራሱን ልብስ ቀይሮለት ወደ ቤቱ ተመለሰ፡፡ ሲሄድ ካረባው በግ ጋር ሲመለስ ከእግዚአብሔር በግ ጋር ትልቅ ትርፍ፡፡





## የሚያውቁት ሲናገሩ

በኢሳያስ 6፡8 "ማንን እልካለሁ ማንስ ይሄድልናል" የተባለው አሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገድ የእግዚአብሔር ወዳጅ የአብርሃም ልጆች በድንቅ በተዓምር ከባርነት ነፃ ወጥተው የቃል ኪዳን ሕዝብ ሆነው የእግዚአብሔር ክብር የተገለጠባቸው ርስት የተሰጣቸው አንድ ነገድ ሙሉ ካህናት ያሉበት ሕዝብ ሆኖ ሳለ እንዴት ማንን እልካለሁ ተባለ? ካህናቱስ? ሊቀካህናቱስ? የት ሄደው የሚላክ ጠፋ? ገርቢሴ የተገኘበት ብዙዎቻችን ያልተገኘንበት መስኪያስ ይኖር ይሆን?

የዚህ ክፍል ዋና ትኩረት እግዚአብሔር በባሪያው በኩል ካደረጋቸው የአገልግሎት ተግባራት ባሻገር ከህይወቱና ከአገልግሎቱ ሌሎች ምን ይማራሉ፤ ለሌሎችስ አብነትና ምሳሌ የሚሆነው በምን በምድነው ደግሞ እግዚአብሔር በሰውና በሰው መሀል አያደላምና በዚህ አገልጋይ ሕይወት ፊት ለፊት ከመነጋገር ያለምንም ውጣ ውረድ በቀላሉ ነገሮች እንደባሪያው ቃል የሆኑበት ምክንያት ምንድነው? ሌላው ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ባለው ግንኙነት ምን ቢጎለው ነው እንደዚህ ባሪያው ያልተጠቀመበት ለሚሉና ለሌሎችም ጥያቄዎች ምላሽ እናገኛለን፡፡

ገርቢሴ ጌታ ኢየሱስን በትክክል ካወቀና ሕይወቱን ከሰጠበት ከ1966 ዓ.ም ይህ መፅሐፍ እስከተዘጋጀበት 2003 ዓ.ም ድረስ የሠላሳ ሰባት ዓመት ጊዜ አለ፡፡ በነዚህ አመታት የሚያውቁት ያገለገላቸው አብረውት ያገለገሉ ለኛ ትምህርት የሚሆኑን የሚሉት

ምን አለ? ያንዳንዶቹን እንመልከት፡፡

"እኔ ነብይ ገርቦሌን የማውቀው ገና ልጅ እያለ በ1967 ዓ.ም ነው፡፡ ገና ልጅ እያለ ጌታን ከአቅሙ በላይ ይወዳል በነዚያ የስደት አመታት ቀስ ብለህ እያስተዋልክ ተንቀሳቀስ ስንለው እኔ ለጌታ ለመታሰር ብቻ ሳይሆን ለመሞትም ዝግጁ ነኝ እያለ ከአገልግሎቱ ወደ ኋላ ሳይልና ሳይፈራ ያንን ክፉ ዘመን አሳልፏል፡፡

በ1968 ዓ.ም ከኢቨንቱ ቅዱሳን እየተለቀሙ ሲታሰሩ እሱ ሳይያዝ በመቅረቱ ወገኖቼ ታስረው እኔ እንዴት እለያቸዋለሁ በማለት እኔም እንደነሱ ነኝ ደባልቁኝ ቢላቸው አሳሪዎቹ "ሂድ ከዚህ" ብለው እንዳባረሩት አስታውሳለሁ፡፡ የወገኖችን ችግር ጭምር መካፈል የሚወድ ንፁህ ሰው ነው፡፡ ገና ከልጅነቱ ጌታንና የጌታን አገልግሎት የሚወድ የመንፈስ ቅዱስ ቅባት ያለበትና ሰውን ሁሉ እኩል የሚወድ ጠባብነትና ዘረኝነት የማያጠቃው ጭንቅ ሐዘንና ማጉረምረም የማይወድ የፍቅርና የእምነት ሰው ነው፡፡ ደግና ሊጋስ በመከራ የሚፀና እምነቱና አገልግሎቱን ለይቶ ያወቀ እግዚአብሔርን የተረዳ ሰው ነው፡፡ የሚገርመኝ ብዙ ሰዎች ይነሳሉ ከጥቂት አመታት በኋላ ይረሳሉ፡፡ በአንድ ነገር ተጠምደው ከትክክለኛው ሩጫቸው ሰውም እግዚአብሔርም ስለሚያጣቸው አይዘልቁም ዘልቀው የጨረሱ ሰዎች የታደሉ ናቸው፡፡ ነብይ ገርቦሌም በዚሁ እንዲጨርስ ስመኝ ከልጅነት እስከ ሽበት ካምላኩም ከሰውም ጋር ግንኙነቱ ሳይበላሽበት በመዝለቁ ለብዙዎቻችን ምሳሌ ይሆናል"

ፓስተር ደረሰ ገለታ ምሥራቅ ወለጋ፡፡





"ስለ ገርቦሌ ሁለት ነገሮችን መናገር እፈልጋለሁ" ያለው ፓስተር ጌታቸው ተሰማ ከድሬዳዋ ነው፡፡

1. ሁለቱም ኪዳኖች ማለትም ብሉይም ሀዲስም የተጠቃለሉት "ጌታ አምላክህን በፍፁም ልብህ በፍፁም ነፍስህም በፍፁም አሳብህም ውደድ፡፡ ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትዕዛዝ ይህች ናት፡፡ ሁለተኛይቱም ይህችን ትመስላለች እርስዋም ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ የምትለው ናት፡፡ በእነዚህ በሁለቱ ትእዛዛት ሕጉም ሁሉ ነቢያትም ተሰቅለዋል" (ማቴዎስ 22፡36-40)

መላው መፅሐፍ ቅዱስ የእምነታችን መሠረት እንደመሆኑ መጠን ፍሬ ሀሳቡም ሲጠቃለል እግዚአብሔር አምላክን ከሁሉ በላይ መውደድ ቀጥሎም ባልንጀራን እንደራስ መውደድ ከሆነ የገርቦሌን አኗኗር ስንመለከት ለአምላኩም ለሰዎችም ፍቅር አለው፡፡ ገርቦሌ በተግባር የተገለጠ በሥራ የሚታይ ለትንሽ ለትልቁ ለእብድና ለጤነኛው ለሁሉም እኩል ሥፍራና ፍቅር አለው፡፡ ከጉድለቱ ያካፍላል፡፡ የወፍ ጫጩቶች እናት ለሆዲ የማትውጠውን ብትውጠው የሚጠቅማትን በአፏ ይዛ ወደ ጎጆዋ በመሄድ ለጫጩቶቿ ታጎርሳለች ይህም ሰው እንዲሁ ነው፡፡ ለራሱና ለቤተሰቡ እያስፈለገው ለሌላው ያካፍላል፡፡ የለበሰውን አውልቆ ይሰጣል፡፡

ፍቅር የሁሉ ነገር መሰረት እንደመሆኑ ማለትም ሰው አጠገቡ ያለውን ወንድሙን ሳይወድ እግዚአብሔርን እወዳለሁ ቢል ይዋሻል እንደተባለ የገርበሌን ማንነት ለመለካት በህይወቱ ያለውን ፍቅር መመልከት በቂ ነው፡፡ ክርስቲያን ብንባል መጋቢ ወይም ሐዋርያ ተብለን ብንጠራ በፍቅር አንፃር ባዶ ከሆን ውሸተኞች መሆናችንን የዚህ ሰው ሕይወት ያስተምረናል፡፡ እኛን ለመለካት እግዚአብሔር በመካከላችን ያስቀመጠው ሰው ይመስለኛል፡፡

2. እምነት፡ በእግዚአብሔር ላይ ያለው እምነት ፅኑ ነው፡፡ ለሱ እግዚአብሔር ቅርብ ነው፡፡ ከአንደበቱ የሚወጣውን እንደሚያደርገው ጥርጥር የለውም፡፡ ሳይንበረከክ በቀጥታ በእግዚአብሔር ላይ በመደገፍ የሚናገረው እንደሚሆን ያምናል

"በፊቱ የቆምሁት የእስራኤል አምላክ ሕያው እግዚአብሔርን ከአፌ ቃል በቀር በእነዚህ ዓመታት ጠልና ዝናብ አይሆንም" (1ኛ ነገስት 17፥1)

እንደተባለ በአፉ ቃል ውጤት ይታያል፡፡ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ሆኖ ስለሚናገረው መፈፀሙን ያምናል፡፡ ይህ የሆነው ሕይወቱን ሙሉ ለሙሉ ለእግዚአብሔር ስለሰጠ ተፈትኖ ስላለፈ የራሱ ስላልሆነ የእግዚአብሔር ቀስትና ጦር ሆኖ ለመንቀል ለመትከል የተመቻቸ ህይወትን ስለሚኖር ነው፡፡ በዚህ ላይ የአፉ ቃል





ከእግዚአብሔር አጠቃላይ ሀሳብና ፈቃድ ጋር ስለማይጣረስ ልክ ካሌብ "ማሸነፍ እንችላለን እንውጣ እንውረስ" (ዘኁልቁ 13፡30) እንዳለው ለእግዚአብሔር ፍቃድና ክብር ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ተስማምቶ ስለሚናገር እግዚአብሔር ቃሉን ለማክበር አይዘገይበትም፡፡" ብሏል፡፡

**ፓስተር ጌታቸው ተሰማ ከድሬዳዋ**

"የነብይ ገርበሌ አገልግሎት በታላላቅ ተዓምራት የታጀበ ሲሆን ለሌሎቻችን ምሳሌ የሚሆንበት በተለይ እግዚአብሔርን የሚያደምጥና በርሱ ምሪት የሚሄድ መሆኑን አይቻለሁ፡፡ ለስብከት ተጋብዞ ከሆነ በጊዜው እግዚአብሔር የሚለው መፀለይ ከሆነ ወደዚያ ለመዞር ፈጣን ነው፡፡ በሰው መርሀ-ግብርና ቀጠሮ አይገኝም፡፡ ሌላውና ለየት የሚያደርገው የህይወት ልምምዱና ፀሎቱ በእምነት ላይ የተመሠረተ መሆኑ ነው፡፡ በእምነት ካደረጋቸው ተዓምራት 1991 ዓ.ም በነጆ ሙሉ ወንጌል ቤተክርስቲያን በተዘጋጀ ኮንፈረንስ ላይ የተደረገውን መጥቀስ እፈልጋለሁ፡፡ ኮንፈረንሱ እየተካሄደ እያለ ታላቅ ዝናብ በነጎድጓድ ድምፅና ብልጭት እያስገመገመ መጣና ማንጠባጠብ ጀመረ፡፡ ኮንፈረንሱን በዚህ ሁኔታ ማቋረጥ የማይታሰብ ነበር፡፡ ነብዩ እያገለገለ የጌታም አብሮነት እየተገለጠ ባለበት ሁኔታ እንዲህ ሲል ተናገረ "አንተ ዝናብ ይህን ጊዜ እንፈልገዋለን ለጊዜው ወደ ሌላ ቦታ እለፍና ዝነብ ሌላ ጊዜ እዚህ ትዘንባለህ" አለው፡፡ ዝናቡም ጭንቱ እንደከበደው ቀስ ብሎ እንደተንጠለጠለ አለፈና በርቀት መዝነብ ጀመረ፡፡ በዚህ አይነት የሚዘንብ ዝናብ በጌታ ስም

በመናገር ሲያቆም አይቻለሁ ስለዚህ ፀጋ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፡፡

## ዓለሙ ዋቅጅራ (የፒኤች ዲ ተማሪ)

"በኔ ህይወት ውስጥ ነብይ ገርቦሌ ትልቅ ድርሻ አለው፡፡ እኔ ገና ልጅ እያለሁ በሬዎች ጠምጄ ሳርስ ወደ እርሻው ቦታ መጣና "አሁን ይበቃሀል ከእንግዲህ የወንጌል እርሻ ታርሳለህ" በማለት በህይወቴ ይሚገተኝ በነበረው የአገልግሎት ላይ ጥሪ ቁርጥ ያለ ውሳኔ እንድወስን አድርጎኛል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በብዙ ወንድሞችና እህቶች የሚወደድ በተዓምራዊ የፈውስ አገልግሎት ተጠቃሚ በሆኑና በሚያውቁት ሁሉ የእግዚአብሔር መልዕክተኛ ፍቅሩ የማይቀዘቅዝና የመለዋወጥ ባህሪ የሌለው ፍቅርን የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ አድርጎ የሚገልጥበት ከሁኔታዎች ጋር የማይሞቅና የማይበርድ አድማ የማያውቅ ሁልጊዜ ካምላኩ ጋር ስላለው ግንኙነት የሚጠነቀቅ እንደቃሉ የሚኖር በመሆኑ ምሳሌ ልናደርገው ይገባናል፡፡"

### ፓ/ር መሰለ ታደሰ ከሻምቡ

"እኔ በአገልግሎቱ ስለተከናወኑ ተዓምራት አይደለም ነብይ ገርቦሌን የምመዝነው፡፡ በርግጥ አገልግሎት የህይወት ፍሬ ስለሆነ ዋጋ አለው ደግሞም በስሙ ድንቅና ተዓምር አድርጎ በመጨረሻ አለመታወቅም አለ፡፡ ገርቦሌን የምመዝነው በማንነቱ በክርስቲያንነቱ ነው፡፡ ብዙ ሰዎች ሞኝ ነው ብለው ይገምታሉ፡፡





በርግጥ በአለም ፍጥረትና ጥበብ አይራመድም፡፡ በዚህ ወደኋላ የቀረ ነው፡፡ ሰዎች የሚመዝኑት ከራሳቸው የህይወት እሴት በመነሳት ነው፡፡ ውስጡ ግን ሞኝ አይለም ከብልጦች ይበልጣል፡፡ ስለሱ ሁለት ነገሮችን ማስቀመጥ እፈልጋለሁ፡፡

1. ላመነበት ነገር ዋጋ የሚከፍል ታማኝና ቁርጠኛ ሰው መሆኑን አይቻለሁ፡፡

2. አገልግሎቱ የብሉይ ኪዳንን ነብያት አገልግሎት ይመስላል፡፡ የአዲስ ኪዳን ነብያት በማነፅ ቃሉን በትንቢታዊ መልኩ መናገር በማስተካከልና በመሳሰሉት ላይ የሚያተኩር ሲሆን የብሉይ ኪዳን ነብያት ከባህሪያቸው ጀምሮ አነጋጋሪ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ሆሴዕ እስራኤልን ለመግለፅ አመንዝራይቱን ሴት በገንዘብ ገዝቶ አገባ ልጅችም ሲወልድ እግዚአብሔር ሊያደርገው ላለው ሥራ ገላጭ የሆነ አስደንጋጭ ስም አወጣ፡፡ ሕዝቅኤልም በየቀኑ የስደተኛ ኑተትና ጓዝ ይዞ ከቦታ ወደ ቦታ በመሄድ የህዝቡን ትኩረት እንዲስብ እንጀራውንና ውሃውን በድንጋጤ እንዲመገብ በአንድ ጎኑ ለረጅም ቀናት እንዲተኛ ሚስቱ ስትሞት እንዳያለቅስ የታዘዘ ነበር፡፡ የገርቦሌ አገልግሎት ከነዚህ ነብያት ጋር ይመሳሰላል፡፡ የምልክት አገልግሎት ያገለግላል አንድ ጊዜ አንዲት እህት ልጅ ሞቶባት ለቅሶ ሄደ፡፡ ትንሽ እንደተቀመጠ የጌታ መንፈስ እንዳዘዘው ምክማን ቴፕ አውጥቶ መዝሙር ከፈተ ለጊዜው ለለቅሶ ግጥም ብሎ የተቀመጠው ሕዝብ ግራ ቢጋባም ብዙም ሳይቆይ በሚያምኑ ለቀስተኞችና በሀዘንተኛዋ ሴት ላይ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸውና በልሳን መፀለይ መዘመርና ማመስገን

ጀመሩ፡፡ ከሁሉም ያቺ እናት ባሰችና በመንፈስ ሆና "ልጁ ወደጌታ ነው የሄደው አልተጎዳም" እያለች ታመስግን ጀመር፡፡ ከዚህም ሌላ ተሰዶበት ከነበረው መሸሸጊያ ቦታው ደጋጎሊና ሲያገባ ቤተሰቡ የሰጠው ደረቅ የእርሻ ቦታ ላይ ቀድሞ ያልነበረና የእርሱን ሁኔታ ተከትሎ የመነጩ ሁለት ምንጮች እንደመነጩና እስከዛሬም በመስኖ ዘመዶቹ እየተጠቀሙባቸው እንደሆነ ይመሰክራሉ፡፡

ከበታቶ የተባለው ቦታ ላይ ሲያገለግል ለጉባኤው ትዕዛዝ ሰጠ "ከመሬት እንጨት አንሱ ብሎ ለማሳየት ቁራጭ ጭራሮ አነሳ የያዛችሁትን እንጨት ወደቤታችሁ ይዛችሁ ግቡ በቤታችሁ ጤና ይሆናል ከብቶቻችሁን ጎተራችሁን እስነኩ አላቸው፡፡ እንዲሁ አደረጉ ምድሪቱ በሚደንቅ ሁኔታ ተባረከች፡፡ እሱ ለምሳሌ የተጠቀመባትን እንጨት መሬት ሲጥላት ከሌላ ቤተክርስቲያን የመጣ አገልጋይ በእምነት ወስዶ ለቤተክርስቲያን ተሀድሶ እንዲመጣ ሰው ሁሉ እየረገጣት በሚገባበት የአዳራሹ ደጃፍ ላይ አደረጋት፡፡ እንዳመነውም ሆኖ በዚያ ቤተክርስቲያን የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ ከቀድሞው በተለየ ሁኔታ ተገለጠ"፡፡

## ነብይ የሺጥላ መቹ

ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ እንደሚተዋወቁ የሚናገረው መጋቢ ሀብታሙ "በተደጋጋሚ አብሬው የማገልገል ዕድል አግኝቼ ስለነበር በነዚህ ጊዜያት የሥጋ ፈውስ ተራ ነገር ሆኖ አይቸዋለሁ፡፡ በጣም የምደነቅበትን ክስተት ያየሁት በካ ላይ በነበረው ኮንፈረንስ ሲሆን





የእግዚአብሔር ክብር ሰው ሊቋቋመው ከሚችለው በላይ የተገለጠበት ነበረ፡፡ ሁለት ዲያቆናት ማታ የነብይ ገርቦሌን እግር ለማጠብ ቀረቡ፡፡ "እኔ ልጠብ" "እኔ ልጠብ" ከተባባሉ በኋላ በመጨረሻ እንዳንድ እግር ለማጠብ ተስማሙ፡፡ እያጠቡ መንፈስ ቅዱስ በሀይል ወረደባቸው በልሳን እየተናገሩ ሮጡ፡፡ እነሱ ብቻ ሳይሆኑ መዘምራንና ሌሎችም አገልጋዮች ሀይወታቸውም አገልግሎታቸውም ተለወጡ፡፡

ከዚህ የእግዚአብሔር ባሪያ ለሌሎች መታነፅ ይሆናል የሚለው አገልጋዩ በማድረጉ ወይም በመናገሩ የሚከሰቱ ውጤቶችን በማስደገፍ ሳይሆን በመገኘቱ ብቻ እግዚአብሔር የሚሰራበት በመሆኑ ሚስጥሩ ያለው ከእግዚአብሔር አብሮነት ጋር እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ እግዚአብሔር ከኛ ጋር ከሆነ እኛ መድከም አያስፈልገንም፡፡ እሱ ይሰራል፡፡ እግዚአብሔር በሙላት ከእርሳቸው ጋር መሆኑን አይቻለሁ፡፡

እግዚአብሔር ከእርሳቸው ጋር መሆኑን በማወቃቸውና ይህንንም በሄዱበት ሁሉ በመለማመዳቸው የሚገጥማቸውን ማንኛውንም መንፈሳዊ አገልግሎት ተማምነው ያደርጋሉ፡፡ ለምሳሌ አንድ ጊዜ ባኮ እርሻ ኮሌጅ የተማሪዎችን ኅብረት ሲያገለግሉ የኅብረቱ ኮሚቴ አባል የነበረ ምትኩ የሚባል ተማሪ በጨጓራ ህመም እየተሰቃየ መማር እስከማይችል ደርሶ ስነበር ወደቤቱ ለመመለስ ወስኖ የሚጠብቀው እንደኮሚቴ አባልነቱ የነበረበትን ኃላፊነት በመወጣት የኮንፈረንሱን መጠናቀቅ ነበር፡፡ ነገር ግን ነብይ ገርቦሌ ከዚህ በሽታው መፈወሱን ነገሩት፡፡ ለማረጋገጥ ወደ ወጥ ቤት ሄዶ

ሁለት ሲኒ ቡና ጠጣ፡፡ ምንም አልሆነም፡፡ ያም ሆኖ መፈወሱን ይጠራጠር ስለነበር ወደ እግዚአብሔር ሰው ቀርቦ "መፈወሴን በምን አረጋግጣለሁ" በማለት ጠየቀ፡፡ እንደኮሌጅ ተማሪነቱ ማስረጃ ለሱ ትልቅ ሥፍራ አለውና፡፡

"ጌታን ጠይቅ ይነግርሀል" ቢሉትም አልተዋጠለትም፡፡

ምልክት እንደፈለገ ስለገባቸው ወደሱ መለስ ብለው "ከእጅህና ከእግርህ የትኛውን ለእግዚአብሔር ትሰጣለህ" ሲሉ ጠየቁት "እግሬን" ሲል መለሰ፡፡ "ቀኙን ወይስ ግራውን" እንዲለይ ጠየቁት "ግራውን" አለ፡፡ እሳቸውም ግራ እግሩን በጣታቸው ነካ አደረጉ፡፡ ወዲያው ልጁ ተዝለፍልፎ ወደቀ፡፡ ጓደኞቹ "ምንሆንክ ተነሳ" ቢሉትም "እግሬን እያለ ይሎህ ጀመር" እግርህ ምን ሆነ" ቢሉት "ሽባ ሆነ" ምንም አይሰማኝም ድንጋይ ሆነብኝ ወይኔ እግሬ" ሲል ብዙሰው ተሰበሰበ፡፡ "ምነው በቀረብህ" አሉት ጓደኞቹ፡፡ በመጨረሻ ነብዩ "አሁንስ መፈወስህን አመንክ" ሲሉ ጠየቁት፡፡ "አምናለሁ አምናለሁ" አለ፡፡ አሁንም በጣታቸው ግራ እግሩን ነካ ሲያደርጉት ዘሎ ተነሳ እግሩም እንደነበር ወደ ጤነኛነቱ ተመለሰ፡፡ ተማሪውም የዕለቱ ፕሮግራም ሲጀመር ለጉባኤው ቆሞ እግዚአብሔር ያደረገለትን መስክረ እንዳሰበው አቋርጦ ሳይገባ ትምህርቱን አጠናቀቀ፡፡

እዛው እባኮ እያለን ማለትም በ1996 ዓ.ም ከፍተኛ የወባ ወረርሽኝ በመላ ሀገሪቱ ተነስቶ ብዙ ህዝብ እንደቅጠል ይረግፍ በነበረበት ጊዜ የግል ህክምና ባለሙያዎች ከሌላ ቦታ እየመጡ ትልልቅ መኖሪያ ቤቶችን በመከራየት ወደ ክሊኒክነት ለውጠዋቸው ሳለ እኝህ የእግዚአብሔር ሰው "የሞት መንፈስ ከዚህ ምድር ለቀህ





ሂድ" ብለው ተናገሩ፡፡ ወረርሽኙ ቆመ፡፡ ለህክምና ተተክለው የነበሩት ድንኳኖች ፈረሱ፡፡ ወደክሊኒክነት ተለውጠው የነበሩ ቤቶች ወደቀድሞ አገልግሎታቸው ተመለሱ፡፡ ሌሊቱን ሸሽቶ እንደሄደው የወልይአዴር ሠራዊት በዚያ ምድር ገብቶ የነበረው ታላቅ ሞት ሀገሩን ለቆ ሄደ፡፡

ከሁሉ በፊት እግዚአብሔርን መፈለግ እንዳለብን ከነብዩ አገልግሎት ተምሬአለሁ፡፡ እግዚአብሔርን ብንፈልግ እሱም ከኛ ጋር ቢሆን ለግለሰብ፣ ለቤተክርስቲያን፣ ለሀገር መፍትሄ እንደሆናለን፡፡ የሀገራችንን ገፅታ ለመቀየር እግዚአብሔርን የሚፈልጉ አገልጋዮች መገኘት ወሳኝ መሆኑን እንመለከታለን፡፡ የምድሪቱ ተስፋ በቅዱሳን ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ላይ የተመሠረተ መሆኑን ከዚህ አይነቱ አገልጋይና አገልግሎት መረዳት እንችላለን፡፡

አንድ አጠንክረን ልንረዳው የሚያስፈልግ ነገር አለ፡፡ ገርቦሌ ነብይ ሆኖ አልተወለደም፡፡ ነብይ ሆኖ ኖረ እንጂ፡፡ በጁ ያለውን እግዚአብሔር የሰጠውን ዘመን ለእግዚአብሔር መገልገያነትና መገለጫነት አመቻችቶ ሰጠ፡፡ ሐዋርያት በጌታ ከመጠራታቸው በፊት መልዕክተኞች ሆነው የሰውን ዘር ዘላለማዊ ፍፃሜ የሚለውጥ ተልዕኮ ይዘው ወደ አለም ስለመላካቸው አስበውትም አያውቁም፡፡ በየራሳቸው የህይወት ስምሪት ደፋ ቀና ሲሉ ነው ታላቁ ጥሪ የደረሳቸው፡፡ ከዚያ በኋላ የበጉ ሐዋርያት ሆኑ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅድ አፈፃፀም በእጃቸው ወደቀ እነሱም በጠሪያቸው ታመኑ፡፡ ሐዋርያነትን ኖረው ሐዋርያነትን ሞቱ፡፡ ከመቶ ዘጠና

ዘጠኙ እጅ ሰማዕት ሆነው አለፉ፡፡ አሁን እግዚአብሔር ያጣው ጥሪውን የሚኖር ሰው ነው፡፡ ጥሪያቸውን የኖሩ ሰዎች ለእግዚአብሔር ይኖራሉ፡፡ ለሕዝብ ይተርፋሉ፡፡ ለእግዚአብሔር የተሰጡ ሰዎች መንፈሳዊውን አለም የሚያልፍ ለሀገር የሚጠቅም ሥራ ይሠራሉ፡፡ እንደ እኛ ሰው የሆነው ኤሊያስ በመንፈሳዊው ሚዛን እንከን የማይወጣለት ነብይ ነበር፡፡ ከዚያም ጋር ጨምሮ ፍትህ ስላጓደለው ስለ አካአብ ቤት ተሟግቷል ምድርን በማድረቅም በማርጠብም ሀገራዊ ሥራ ሠርቷል፡፡ ኢጋንንታዊ አምልኮ በነገሠበት የእግዚአብሔርን አምላክነትና ታላቅነት አስመስክሯል፡፡ ወደ ሥልጣን ስለሚወጣው ከስልጣን ስለሚወርደው ገዶታል፡፡

ኤልሳም ሲተካ አገልግሎቱን ሲጀምር የሚያስጨንግፈውን ክፉ ውሃ በመፈወስ የሰዎች ኑሮ ጣዕም ያለው እንዲሆን በማድረግ ነው፡፡ የህብረተሰባችንን ሕይወት ለመለወጥ የምድር ጨውነትን የተቀበልን ክቡር የሆነው ሰው የሚጠፋ እንስሳትን እንዳይመስል ለዘላለም ክብር ክርስቶስ ሞቶለት ሳለ በሲያል እንዳይጨንግፍ የመለወጥ ሀላፊነት በቤተክርስቲያን ላይ ማለትም በኛ ላይ ማረፍ እየታወቀ ቤተክርስቲያን ላለችበት ህብረተሰብ ምን አደረገች?

ኤልሳም በዘመኑ ለባልቴቶችና ለመካኖች መፍትሄ ለርሀብ ዘመን ጥጋብ ነበር፡፡ ሀገሩን ከሶርያ አደጋዎች በዘመናችን ቋንቋ አሸባሪዎች እንደምንለው ደጋግሞ ያዳነ ሰው ነው፡፡ በዚህ ስሌት መሄድ ግድ ነውና ሀገራችን ከርሀብ ከበሽታ ከደም መፍሰስ እንድትድን አስተዳዳሪዎቻችን ስኬታማና እግዚአብሔርን የሚፈሩ





እንዲሆኑ በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ ያለው ሕይወት በመኖር ለውጥ ማምጣት ይጠበቅብናል፡፡ የቤተክርስቲያን ስልጣን ታላቅ ነው፡፡ ጌታ በምድር ላይ በሥጋ በነበረበት ዘመን ለተጎዳ ሁሉ ይጠቅም ነበረ፡፡ የተራቡትን መግቧል የታመሙትን ፈውሷል፡፡ ሙታንን አስነስቷል፡፡ ከትንሳኤ በኋላ ግን ሐዋርያትን ወደ ባህር ሄዶ ከማግኘትና የተጠበሰ አሳ ከመመገብ ያውም ለሐዋርያት ብቻ እንደቀድሞው ለፈለገው ሁሉ ሲገኝ አናይም፡፡ ምክንያቱም የማሰርንም የመፍታትንም ስልጣን ለቤተክርስቲያን ስለሰጠ ነው፡፡ ማንኛውም ለሰው የሚደረግ ነገር በቤተክርስቲያን በኩል እንዲደረግ አሳልፎ ሰጥቷል፡፡ ቤተክርስቲያን ካልሰራችው ሳይሠራ ይቀራል፡፡ ዛሬ ቤተክርስቲያን ተልዕኮዋን ስላልተወጣች ምድራችን በድህነት በበሽታ እግዚአብሔርን ባለማወቅ ትማቅቃለች፡፡ የሀገሪቱን ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማኅበረሰባዊ ሁኔታዎች ለእግዚአብሔር ክብር ለህዝባችን ጥቅም ከመለወጥ ባለፈ ይህ ሕዝብ ለእግዚአብሔር መንግስት ሊታጨድ የተገባው የገረጣ መከር መሆኑን ጭምር መዘንጋት የለብንም፡፡

ሶማሊያ ለምን ፈራርሳ ቀረች? በዚያ የምትማልድ ቤተክርስቲያን ስለሌለች ነው፡፡ እኔ ሞቃዲሾን ሳውቃት በከተማው ውስጥ አንድ ድሮ ቅኝ ገዢዎቹ ጣሊያኖች ከሠሩት የካቶሊክ ቤተክርስቲያን በስተቀር ምንም ቤተክርስቲያን አልነበረም ያም ህንፃ ጣሊያኖቹ ኢያረጁ ሲያልቁ ባዶውን ቀርቶ ሳለ በጦርነቱ ወቅት ጣሪያ እየተነቀለ መዝጊያ እየተፈለቀቀ ሲሸጥ እጣ ፈንታው ይኸው ሆኖ መስቀል እንኳ የማይታይበት አገር ሆነች፡፡ የሚማልድ

ባለመኖሩ የጦርነት እሳት የሚሞቅባት ምድጃ ሆና ቀረች፡፡ የቅዱሳን ጣልቃገብነት ለሀገር ሰላምና ብልፅግና ወሳኝ ነው፡፡

ወንጌል ግለሰብን ማህበረሰብን ብሎም ሀገርን ይለውጣል፡፡ ይለውጣል ስንል ፍትሀዊ የሆነ የተረጋጋ ፖለቲካዊ አስተዳደር የታነፀ ስነምግባራዊ የአኗኗር ዘይቤና ከጉስቁልና የተላቀቀ የተባረከ ኢኮኖሚያዊ ስርዓት ይፈጠራል ማለታችን ነው፡፡ ለዚህም ማስረጃ የሚሆኑን ብዙ የቀድሞዎቹ የምዕራብ አገሮችና ከምስራቅም እንደደቡብ ኮሪያ ያሉት ሀገሮች ናቸው፡፡ ለምሳሌ ዛሬ በተረጋጋ ፖለቲካ ኢኮኖሚ ከሚታወቁት ሀገሮች ስዊድንን ብንወስድ ወንጌልን እስካገኙበት እስከ አሥራ አንደኛው ክፍለዘመን ድረስ ስዊድናውያን ኋላ ቀር አዳኞች የነበሩ ሲሆን ቦኒፌስ የተባለው የወንጌል ሰባኪ ከእንግሊዝ ሲሻገር ዛፍ ሲያመልኩ ነው ያገኛቸው፡፡ ሀሙስ ሀሙስ ቶር የተባለ ጣዖትን በዛፍ ሥር ተሰብስበው ያመልካሉ፡፡ ወንጌልን ሲሰብኩላቸው "አምላችን ይህን ዛፍ ነው" አሉት "ይህን ዛፍ እኔ እቆርጠዋለሁ ሊላም እውነተኛና ብቸኛ የሆነውን አምላክ ታውቃላችሁ" ቢላቸው "ተው ቶር ይገልሀል" በማለት ሊያግባቡትሞከሩ፡፡ ፈቃዳቸውን ካገኘ በኋላ ዛፉን ጣለው፡፡ አልሞተም፡፡ ፈለጠው ቆራረጠው አሁንም አልሞተም፡፡ በእንጨቱ ዳስ ሰራበትና ኑ ግቡና ወንጌልን ስሙ አለ፡፡ ቶር ራሱን ካላዳነ ብለው ስዊድናውያን ወደ ክርስቶስ ወንጌል ዞሩ፡፡ ህዝባቸው በየቦታው በመስፈር የተረጋጋ ኑሮ መኖር ጀመረ፡፡ ስነ-ምግባር ያለው የተባረከ ሕዝብ እየሆነ ሄደ፡፡ ወንጌልን ወደ ራሺያ ይዘው





ሄዱ፡፡ ወንጌል ኖርዌይንም ኖርዌይ ራሺያንም ራሺያ ስዊድንንም ስዊድን አደረገ፤ አሁን ቢረሱትም፡፡

ለሀገራችን ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ስነምግባራዊ ለውጥና ተሀድሶ ከፈለግን ሕዝባችንን በክርስቶስ ከራሱ ጋር የማስታረቅ አጀንዳ ሸክማችን መሆን አለበት፡፡ ይህ ሲሆን የሀገሪቱን ልማትና ሰላም ያለማቋረጥ በአምላካችን ፊት በምልጃ ማቅረብ ይጠበቅብናል፡፡ አፍ ለሌለው ተናገረ እንደተባለ ለሀገራችን ለመናገር እግዚአብሔር የሚሰማው ቋንቋና አፍ ያለው ቤተክርስቲያን ውስጥ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ከጉስቁልና መውጫ ብቸኛው መፍትሄ ስለ ምድሪቱ የቅዱሳን መቃተትና የራስን አስተዋፅዖ ማበርከት ነው፡፡

ነብይ ገርቦሌ በመንዲ መስመር ቦጂ ድርመጂና ጨቆርሳ በነበረ ጊዜ ለከተሞቹ ዕድገት ፀልዮ ነበረ፡፡ ያን ጊዜ የህክምና አገልግሎት ችግር በዋነኝነት የመንገድ ችግር ሕዝብ የተማረረበት ጉዳይ ሆኖ ሳለ በማይታመን ሁኔታ መንገዱ አስፖልት የሚሆንበትንና ሌሎችም የዕድገት ተግባሮች እንደሚከናወኑ መልዕክት ነግሯቸው ነበር፡፡ እግዚአብሔር እንደተናገረው ሆነ፡፡ አካባቢው ተለወጠ በልማት ተሸላሚ ወረዳ እስከ መሆን ደረሱ፡፡ አስር ፃድቃን ቢገኙ የሰዶም ሁኔታ ይቀየር እንደነበረው አሁን በሀገራችን ውስጥ ያሉት አብያተክርስቲያናት የኢትዮጵያን ሁኔታ ለመቀየር ከበቂ በላይ ናቸው፡፡ መጋቢ አእምሮ መልካሙና ወ/ዊ አቦሴ ባኤስ ስለአካቢያቸው ተግተው በመፀለይ ለውጥ ማየት እንደቻሉ ከመሰከሩት የተወሰደ ነው የጨቆርሳውንና የቦጂ ድርመጂ ጉብኝት፡፡

በኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተክርስቲያን የምልዐት መጽሔት አዘጋጅ በነበሩበት ጊዜ ወደ ጊዳ አያና ተጉዘው ለዘጠኝ ቀን ስለ ነብዩ የቃለመጠይቅ ዘገባ የሠሩት ጋዜጠኛ ሃብታሙ በለጠ የተመለከቱትን በአጭሩ አስቀምጠዋል።

"ነብይ ገርቦሌ ሂርጳን በማንነታቸውና በአገልግሎታቸው አውቃቸዋለሁ። ሆሮሙ ድረስ በመዝለቅ ከቤተሰቦቻቸው ከወንድሞቻቸውና ከእህቶቻቸው ጋር ተገናኝቻለሁ። በዚህ ወቅት የተረዳሁት ነገር ነብዩ አብዛኛውን የህይወታቸውን ውጣ ውረድ ያሳለፉትን መከራ ክብደት ለዘብና ቀለል አድርገው የእግዚአብሔርን ድንቅና ተአምራት በማድነቅ ያወጋሉ። እኝህ ሰው ከሚታወቁበት ልዩ ባህሪያቸው አንዱ የፍቅር ሰው መሆናቸው ነው። እኔ እስከተረዳሁትና እስከገባኝ ድረስ በብዙ አገልጋዮች ህይወት የማናገኘውን ከግብዝነት የራቀ ንፁህ ፍቅር መፅሐፍ ቅዱስ የሚገልፀው አይነት ፍቅር በህይወታቸው ሲገለጥ አይቻለሁ። ፍቅራቸው ከቸርነት ጋር ነው። ለተቸገሩ ከመስጠት ጋር ራስን ከመቁረስ ጋር በመሆኑ ተግባራዊ ሰው ናቸው።

ጊዳ በመኖሪያ ቤታቸው ሆንተብሎ ለእንግዳ መቀበያ የተዘጋጁ ማረፊያ ክፍሎች አሉ። ወደ ጊዳ ያቀናና ወደ እሳቸው ቤት ጎራ ያለ እንግዳ ሁሉ በልቶ ጠጥቶ አርፎ መንፈሳዊ አገልግሎት አግኝቶ ይመለሳል። ይህ አገልግሎት የጠንካራዋ ባለቤታቸው የወ/ሮ አዳነች ቶሌራ ተግባር ነው። በሙሉ ፈገግታና በትህትና የመጣውን እንግዳ ያስተናግዳሉ። ልጆቻቸው ትጉ ሠራተኞች ሆነው ከእናታቸው ሥር ሳይወጡ እንግዶቻቸውን





ያስተናግዳሉ ቤቱ በአብዛኛው የፀሎትና የእግዚአብሔርን ቃል የመካፈል አገልግሎት ይካሄድበታል። በሥጋም በነፍስም እረፍት ያለበት የበረሀ ገነት (ኦሲስ) ነው። የታመሙ ተፈውሰው ያዘኑ ተፅናንተው የደከሙ በርትተው ይመለሳሉ።

በዚህ የቃለ መጠይቅ ጉዞዬ ተወልደው ወዳደጉበት ሆሮሙ ሰፈራቸው ድረስ በመሄድ ስለብዙ ነገሮች መስማትና መመልከት ችያለሁ። በጎች ሲጠብቁ ከሚወዷቸው ከኢየሱስ ጋር ይውሉበት የነበረውን መስክ በስደት ከቤት ከተባረሩ በኋላ ተሸሽገውበት የነበረውን ዱጋጎሌ የተባለውን ዋሻ፣ በኢሰፓ ካድሬዎች ሲፈለጉ ተሸሽገው ይፀልዩ የነበሩበትን ጫካና አለታማ ተራራ አይቻለሁ። ይህ ቦታ የመርዛማ እባቦችና የዘንዶ መኖሪያ ሲሆን እሳቸውንና ከእርሳቸው ጋር የተሰደዱትን ቅዱሳን ሳይተናኩሉ ሰዎቹም ዘንዶዎችም በቅርብ ርቀት በሰላም ይኖሩ እንደነበር ተነግሮኛል። "ወደኛ አትምጡ እኛ የሰማይና የምድር አምላክ አገልጋዮች ነን" ብለው እንዳያጠቋቸው በእግዚአብሔር ስም ተናግረው ስለነበር ፍጥረት ሁሉ ደግሞ የእግዚአብሔርን ድምፅ ይሰማል ይታዘዛልና ተከባብረው ኖረዋል። ሰዎች የሞተላቸውን ጌታ ሲያሳድዱ እንስሳት ግን በስሙ ስልጣን ይገዙላቸው ነበር።

ሌላው ያስተዋልኩት ነገር ያሳድዷቸው የነበሩ ወንድሞቻቸው ሁሉ አሁን በጌታ መሆናቸውን ነው። የእሳቸው መጠንከር ለቤተሰቦቻቸው መዳን ምክንያት ሆኗል። በፈተና የሚፀና ብፁዕ ነው እንደተባለ ዛሬ ዝርያቸው ተቀድሷል።"

ወ/ዊ ገመቹ ቶሌራ የበካው የአቦ ተሌራ ልጅና የአዲ ወንድም እንደመሆኑ መጠን ከነብዩ ቤተሰባዊ ኑሮና አገልግሎት ጋር ብዙ የተጣመሩ ውጣ ውረዶችን አብሮ አሳልፏል፡፡ ብዙ የሚለው ነገር ቢኖረውም ጥቂቱን እንመልከት፡፡

"ነብይ ገርባሴ የቤተሰብን ፍቅር ሳይጠግብ ገና በልጅነቱ በስደት ቢወጣም በውጭም የጠበቀው በደርግ ካድሬዎች መሰደድ ነው፡፡ በዚያ ላይ በዚያን ዘመን ብዙ አማኞች አልነበሩም የነበሩትም ጥቂት እዚህ ጥቂት እዚያ ሲሆን ከአንዱ ወደ ሌላው ለመድረስ ከሰዓታት እስከ ቀናት ሊያስጉዝ ይችላል፡፡

እንግዲህ በዚህ ሁኔታ ውስጥ በልጅ አቅም ረሀብንና መታረዝን መገፋትንና መጠላትን ተቋቁሞ ፀንቶ ማሳለፍ በኋላኛዎቹ አመታት በአገልግሎቱ ለሚታየው ፍሬ መሠረት እንደሆነ ልንረዳ እንችላለን፡፡ ያንን የመከራና የስደት ምዕራፍ ባይቋቋም ለዚህኛው በረከት ባልበቃም ነበር፡፡ በዚያ ውስጥ እንዴት ፀንቶ አለፈ ብለን ብንጠይቅ ሁለት መልሶች ይኖሩናል፡፡ አንደኛው የክርስቶስ ፍቅር ታላቅ ነው፡፡ ብዙ ውሀ ፍቅርን ሊያጠፋ አይችልም እንደተባለ ጌታ ወደ ልቡ የገባ ሰው ማንኛውንም ዋጋ ለመክፈል ይበረታል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ራሱ ጌታ የጠራቸውን ያፀናል ያቆማል፡፡ ትንሹን ልጅ ሳሙኤልን ከእናቱ ተቀብሎ ያሳደገና ለታላቅ ሥራ ያበቃ እግዚአብሔር ብዙ ልጆችን አባትና እናት ሆኖ በፍቅሩ አሳድጎ ለክብሩ አውሏል፡፡ ለገርባሴም እንዲሁ ነው፡፡ ሌላ ቀርቶ ወደ ቤተሰብ ከተጠጋና ማገልገል ከጀመረ በኋላ እንኳ





የአባይን በረሀ ተሻግሮ ጎጃም ድረስ ከዚያም በአዲስ አበባ ዞሮ እያገለገለ ባለበት ጊዜ የቤተክርስቲያን መሪዎች አንተ ልጅ ነህ ሂድና ለቤተሰብህ ሥራ ርዳቸው ተብሎ ተመልሷል፡፡ የዚህ ሰው መገፋት ከቤተሰብ ወይም ከሥርዓቱ ብቻ አልነበረም፡፡ በቤተክርስቲያን መሪዎችም አይወደድም ነበር፡፡ ከሚሰጠው ምክንያት የመጀመሪያው "ስታድግ ታገለግላለህ" ሲሆን ሁለተኛው "ፍቅርህ ገደብ የለውም በልክ ሁን" ነው፡፡ ኋላ ኋላ አገልግሎቱን መሸፈን ባልቻሉበትና የግዴታ አገልጋዮችን ነው ብለው መቀበል በቻሉበት ጊዜ እንኳ በወር ሦስት ብር ቀለብ እየተሰጠው ለብዙ ጊዜ አገልግሏል፡፡ ከዚያውም ላይ አብሮት ያገለግል የነበረው ሰው ሚስቱ ምጥ ይዟት ስለነበር ሦስት ሦስት ብራቸውን ተቀብለው ሲመለሱ ለንደኛው ጨምሮለት ባዶ እጁን የገባበትን ጊዜ እንደነበር አስታውሳለሁ፡፡ የፍቅር ሰው በመሆኑ ጥላቻ አይገባውም፡፡ በነዚህ ረጅም አመታት ትውውቃችን ይህ ነው የሚባል ንብረት ባይኖረውም ሁሌም ሲሰጥ ነው የማየው፡፡ የሚሰጠው ነገር እግዚአብሔር አሳጥቶት አያውቅም፡፡

"ለዘሪ ዘርን ለመበለትም እንጀራን በብዙ የሚሰጥ እርሱም የምትዘሩትን ዘር ይሰጣችኋል ያበረክትላችሁማል የፅድቃችሁንም ፍሬ ያሳድጋል" (2ቆሮንቶስ 9፡10)

ቢያጣ እንኳ የመጨረሻ ነገሩን ወይም የቤተሰቡን ነገር አንስቶ ይሰጣል፡፡

በአገልግሎቱ በርካታ ድንቅና ተዓምራት ሲፈፀም ባይም ሦስቱን ብቻ ልንገራችሁ፡፡ በምዕራብ ሸዋ ዞን ቶኬ ኩታዬ ወረዳ

የጉደር ከተማ ዜሮ አንድ ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት ወንድም አንጋሱ ሁንዴሳ በመስርያ ቤት በሥራ ላይ እያሉ የተደበላለቀ የግብር ሰነድ ሁለት ሁለት ለማያየዝ ብዙ የወረቀት መርፌዎች በጥርሶቻቸው ነክሰው እያለ በድንገት አንዷ የወረቀት መርፌ (ስቴል) ሾልካ ወደ ጉሮሮአቸው ገባች፡፡ በታላቅ ጭንቀትና ህመም ለሦስት ወር ሲሰቃዩ እንደቆዩ በጉደር ሙሉ ወንጌል ቤተክርስቲያን የተዘጋጀ ኮንፈረንስ እንዳለ ሰምቼ እኔም ለመካፈል ወደዚያው ሄድኩ፡፡

በሁለተኛው ቀን ነብይ ገርቦሌ ሊያገለግል ወደ መድረክ እንደወጣ "ከዚህ በፊት ሀኪም ቤት ሄዳችሁ ምንም መፍትሄ ያጣችሁና በሽታችሁ ያልታወቀ በዚህ ጉባኤ መካከል አላችሁ ለእናንተ አሁን መፍትሄ ከጌታ ዘንድ አለ የብዙዎቻችሁ በሽታ በሳልና በትውከት ይወጣል" አለ፡፡ የወረቀት መርፌ ለሦስት ወር በሆዳቸው ያስቀመጡት አንጋሱ ሁንዴሳም ፋታ የሚነሳ ሳል አጣደፋቸው ሳሉ ከታች ከሆዳቸው ወደ ላይ የሚስብ ማስመለስ ነበር፡፡ ደምና መግል ለብሶ የወፈረና የጠጠረ ነገር ጎትቶ በማውጣት አስመለሳቸው፡፡ በዚያ ወስጥ ያቺ ተንሸራታ የገባችው የወረቀት መረፌ ነበረች፡፡ እኚህ ሰው እንደቀድሞው በአፋቸው ስቴል ይዘውም ባይሆን ጤነኛ ሆነው በመስራት ላይ ይገኛሉ፡፡

ሌላው በ1999 ዓ.ም በምስራቅ ወለጋ በኤበንቱ ወረዳ በአንዴ ከተማ በአብያተክርስቲያናት ኅብረት ክሩሴድ ተዘጋጅቶ ሳለ ከአዘጋጆቹ መካከል ወንድም ገብሬ ለሚ በጠና ታሞ ራሱን በመሳት ኮማ ውስጥ ገባ፡፡ በኮንፈረንሱ መሀል ቢሞት የዚህ ወንድም ሀዘን ባልተጠበቀ ሰዓት በህዝቡ ላይ ከመውደቁም ባሻገር





አብያተክርስቲያናትን ሁሉ ያካተተው ታላቅ መንፈሳዊ ዝግጅት ፍሬ አልባ እንዳይሆን መሪዎች በጭንቀት ላይ እያሉ ነብይ ገርቦሌ ወደዚያ ሄደ፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ኮማ ውስጥ ገብቶ ወደሚጠበቀው ሰው ቤት መራው፡፡ በታመመው ሰው ደጅ ቆሞ ድምፁን ከፍ በማድረግ "ገብሬ ለሚ ሆይ ተነስ" ብሎ በጩኸት ተጣራ፡፡ ገብሬ ለሚም ይህን ድምፅ ሰምቶ ወዲያው ከኮማ ውስጥ ነቅቶ ድኖና ሙሉ ጤነኛ ሆኖ ተነሳ፡፡ ወደመደበኛ የኮንፈረንስ ዝግጅት ሀላፊነቱም ተመለሰ፡፡ የመንግስት ሠራተኛ ስለነበር ብዙ ባልደረቦቹ እሱን ለማየት እየመጡ ተደንቀው ጌታን የግል አዳኛቸው አድርገው ተቀበሉ፡፡ ከዚያም ባለፈ በቦታው የተገኙና ያመኑ ባለስልጣናት "እግዚአብሔር እውነትም አምላክ ነው ቤተክርስቲያንን መደገፍ ይገባል በማለት የአምልኮ ቦታ አልነበራቸውምና እንሲሰጣቸው አዘዙ፡፡

በመጨረሻም ስለነብይ ገርቦሌ የእምነት ፀሎትና ስለ ውጤቱ መናገር እፈልጋለሁ፡፡ አገልግሎቱ በእምነት ፀሎት የተደገፈ ነው፡፡ አንድ ጊዜ በምዕራብ ወለጋ ደምቢደሎ አካባቢ የጎሪ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተክርስቲያን ባዘጋጀችው ኮንፈረንስ ላይ ያገለግል ነበር፡፡ በዚያም ብዙ ሕዝብ ተሰብስቦ ስለነበር አገልግሎቱን በቤተክርስቲያን አዳራሽ ውስጥ ማካሄድ ስላልተቻለ ጉባኤው በሰፊ ሜዳ ላይ እንዲካሄድ ተወሰነ፡፡ ነብዩም እንደመድረክ በአፈር ተደልድሎ ከተሰራው አራት ማዕዘን መደብ ላይ ቆሞ ማገልገል ጀመረ፡፡ ይሁን እንጂ ጊዜው የበጋው ሙቀት በጣም ከፍ የሚልበት የየካቲት ወር

ስለነበር ከየአካባቢው የአጎራባች አብያተክርስቲያናት መጥቶ በአውላላው ሜዳ ላይ ለፈሰሰው ሕዝብ ሙቀቱ ሊቋቋሙት የማይቻል ነበር፡፡ ታዳሚዎቹ በእግዚአብሔር ቃል ጥማት የፀሐዩን ሀሩር ወቅቱ ነውና ከተጨባጩ አለም ዕውነታ ውጪ ምን ይደረጋል በማለት አንዳንዱ ጨርቁን ሌላው የዛፍ ቅርንጫፍ ግንባይ ራሱ ላይ በማድረግ ንዳዱን እየተቋቋመ ከሰማያዊው ማዕድ ይረካ ነበር፡፡

ለነብዩ ገርበሌ ግን ከተጨባጩ አለም ዕውነታ ውጪ በሚሰራው አምላክ መደገፍ የተለመደና የሚቻል ነውና "እስቲ ይህ የፀሐይ ሙቀት ወደቀዝቃዛ አየር እንዲለወጥ በእምነት እንፀልይ" አሉና ሕዝቡ ተነስቶ እጆቹን ወደ ላይ በመዘርጋት አብሯቸው እንዲፀልይ አዘዘ "አቤቱ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ሆይ እነሆ ቃልህን ለመስማት የመጡ ወንድና ሴት ልጆችህ የፀሐዩን ሙቀት መቋቋም አልቻሉም ስላንተ ፍቅር ታግሰው በዚህ ሁኔታ ቆይተዋልና ጌታ ሆይ መልካም ፈቃድህ ከሆነ ከዚህች ደቂቃ ጀምሮ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ቀዝቃዛ አየር ይሆን ዘንድ እኛ ልጆችህ በመስማማት በአንድነት እንለምንሀለን" ሲሉ ጉባኤውን በፀሎት በእግዚአብሔር ፊት አቀረቡ፡፡ ወደ ላይ የተነሱት እጆች ወደቦታቸው እየተመለሱ እያለ ከሩቅ ያልመጣ ከዚያው የተፈጠረ ይመስል ጥርት ብሎ ከአድማስ እስከ አድማስ በሚታየው ሰማይ ላይ ደመና መታየት እየሩም መቀዝቀዝ ጀመረ፡፡

ይህን የተመለከተውና ፀሎቱ በቅፅበት ሲመለስ ያየው ህዝብ በታላቅ እልልታና ጭብጨባ ለረጅም ጊዜ ለእግዚአብሔር ክብር





ሰጠ፡፡ በሀገሪቱ ላይ በቅፅበት የበጋውን ሀሩር ያበረደው ጌታ ሥራ በነዋሪው ሁሉ ዘንድ ስለታየ ማለትም የተደረገው ተአምር ከስብሰባው በላይ ካለው ሰማይ ያለፈ ስለነበር እግዚአብሔር በግልፅ እየታየ ወደ ጌታ አለመምጣት እንደሞኝነት ተቆጥሮ እጅግ ብዙ ሕዝብ አመነ የእግዚአብሔርም መገኘት ለብዙዎች እምነትን ጨመረ፡፡"

ቀደም ሲል አጋሮ የነበረውና በዚያ ነብዩ ሲያገለግል ያስተዋለውንና ለየት ያለበትን ሁኔታ እንዲህ ይገልፀዋል፡፡ "የጌታ መንፈስ ከዚያ በፊት አይቼ በማላውቀው ሁኔታ ወረደ፡፡ ከዚያ በፊት ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ከሰባት እስከ አስራ ሦስት አመት ዕድሜ ያላቸው ልጆች ጭምር የእግዚአብሔር መንፈስ ወርዶባቸው በደስታ ሰክረው ነበር፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ ብዙ ሰዎች ከበሽታቸው ተፈውሰዋል፡፡ ነብዩ ያረፈው እኔ ቤት ስለነበር ብዙ ሰዎች በስልክም በአካልም ለማግኘት ይመጡ ነበር፡፡ በተለይ አንዲት ሴት እህቷ በጣም ታማ ስለነበር እንዲፀልይላት ፈልጋ ብዙ ጊዜ ደወለች፡፡ እሱም ከጌታ አዳምጦ "እህትሽ በሚቀጥለው ሳምንት ትሞታለች የምትፈልገውን ሁሉ ስጪት ደስ የሚላትን ምግብ አዘጋጁላት በደስታ እያጫወታችኋት በሚቀራችሁ ጊዜ ውስጥ ውስጡን ተሰናበቷት" አላት እንዳለውም ሆነ፡፡

አገልግሎቱን ጨርሶ በሚሄድበት ቀን ብዙ ሰዎች በማለዳ በራችን ላይ ተሰበሰቡ፡፡ አመጣጣቸውም ሊሰናበቱትና ስጦታ ሊሰጡት ነበር፡፡ በሰሞኑ ከተደረገው ድንቅና ተዓምር የተነሳ ሰዎች "ጌታን ከማየት ይልቅ ለኔ ክብር ሊሰጡ ይፈልጋሉና በነፃ የሰጠሁህን

በነፃ ሰጥተህ ውጣ ብሎኛል ደብቀህ ከዚህ ከተማ አስወጣኝ" ስላለኝ በመኪና አውጥቼ ወደ ጅማ አሳፍሬ ሸኘሁት፡፡"

ናስር ከጅማ

ገርቦሌ ገና ልጅ ሆኖ በ1966 ዓ.ም ታሞ በሰው ሸክም ዳረጎስ ፀሎት ቤት ሲወሰድ የፀለየለት ኋላም አብረው ለተወሰነ ጊዜ የኖሩት ወ/ሮ ሴቀታ ገለታ "ለሠላሳ ሰባት አመት አውቀዋለሁ ለሰዎች ያለው ፍቅር እምነቱና ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ያልተቋረጠ አንድነት በጣም ይገርመኛል፡፡ ጌታን ካወቀ ጀምሮ ብዙ ውጣ ውረድ ያለበት ሕይወት በመራም ፀንቶ በመቆም ለብዙዎች ሞዴል የሚሆን ሆኗል፡፡ እግዚአብሔርም የሚፈልግብን ጀምረን እስከምንጨርስ ብርሃናችን እየጨመረ እንዲሄድ እንደመሆኑ ሁሉ ይህን ሰው ከልጅነት እስከሽበት ሳውቀው ለባህሪውና ለመንፈሳዊ ሕይወቱ ከፍተኛ ጥንቃቄ አድርጎ የኖረ ሰው ነው፡፡" ብለዋል፡፡

"ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ" /የሐዋርያት ሥራ 13፡3/

ጌታ አገልጋዮችን ለመንግስቱ ስራ ይጠራል፡፡ በተጠሩትና በሥራው መካከል መታለፍ ያለባቸው ስርጓጉጦች አሉ፡፡ ጀማሪ አገልጋዮች የቀደሙት ምክርና ፀሎት ለቀሪ ዘመናቸው ውጤታማነት እጅግ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ወ/ሮ እሸቱ ሆርዶፋ ዛሬ እንዲህ የነፃአውሮ አለም አቀፍ የወንጌል አገልግሎት (ሚኒስትሪ) ከመጀመሩ በፊት ጊዳሜ የሚኖር ጌታ የጠራው ትንሽ ልጅ ነበር፡፡ ወደፊት የሚሮጠው ሩጫ ያለው በእግዚአብሔር ሀሳብ ብቻ ውስጥ እንጂ ራሱም ሆነ የነበረበት ቤተክርስቲያን አያውቁም፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር ይህንን





ልጅ አሳድጎ ሊሰራበት ያለውን ሥራ እንዲነግረውና ከፍ ያለ ሰማያዊ ጥሪ የመጣለት መሆኑን ነብይ ገርቦሌ ወደ ጊዳሜ ሄዶ እንዲናገር ተላከ፡፡ ስለሆነም በጌታ የተላከው ነብይ ጊዳሜ እንደደረሰ ይህንን አይቶት የማያውቅ ልጅ "ሂድና እጁን ይዘህ አውጣልኝ ብሎኝ ነው የመጣሁት ብሎ ሕይወቴን በዝርዝር ነገረኝ እንደተባለው በ1992 ዓ.ም ከዚያ ወጣሁ ቀስ በቀስም ወደዚህ ታላቅ አለም አቀፍ አገልግሎት ገባሁ" ወ/ሮ እሸቱ ሆርዶፋ፡፡ በተጨማሪም ስለ ነብዩ እሸቱ የሚለው አለው "በጣም የሚገርመኝ በመጀመሪያ እግዚአብሔርን መስማቱ ነው፡፡ የአሰማሙ ሁኔታ ራሱ ያልተለመደ ነው፡፡ ሰው ሰላም እያለ መልዕክት ተቀብሎ ያስተላልፋል፡፡ መንፈሳዊ ጆሮቹ ለብዙዎች እንቆቅልሽ መፈታትና መፍትሄ እንዲሆን ከማድረጉም ባሻገር ሰዎች ያሉበትን ሁኔታ ዋሽተው ቢነግሩት ወደ እውነቱ የግድ እንዲህና እንዲህ አይደለምን ብሎ ይመልሳቸዋል፡፡

ለሌሎች የሚኖር ሰው መሆኑ ሁለተኛው ጥሩ ነገሩ ነው፡፡ አገልግሎቱን ወይም ፀጋውን ብቻ ሳይሆን ተጨምሮ እራሱን ለሌሎች ይሰጣል፡፡ ገንዘቡን ልብሱን ልቡን ጊዜውን አሳልፎ ይሰጣል፡፡ የሚኖረው ለሌሎች የመሰዋዕትነት ኑሮ ነው፡፡ ሌላው ያየሁበት መልካም ነገር አገልግሎት አይሰለቸውም ሙሉ ቀን በመድረክ ቆይቶ ሌሊት ሲፀልይ ያድራል፡፡ ሰዎችን ያናግራል ያማክራል፡፡ የሱ ፀሎት ችግርን ወደ እግዚአብሔር ከማቅረብ ያለፈ ነው፡፡ የጌታን ፊት በመናፈቅ ነው ወደ ፅድቅ ዙፋን የሚቀርበው፡፡

እግዚአብሔር በተለየ ሁኔታ የሚጠቀምበትም መሆኑን አይቻለሁ፡፡ የማያውቃቸውን ሰዎች በትክክለኛ ስማቸው ሲጠራ አይቻለሁ፡፡ ይህ ሰው ለብዙዎቻችን ምሳሌ የሚሆኑ በርካታ መንፈሳዊ እሴቶች አሉት፡፡"

"ነብይ ገርቦሌ የፍቅርና የርህራሄ ሰባኪና አዋጅ ነጋሪ ነው" የሚለው ወንጌላዊ ሰለሞን በንቲ ስለ አገልጋዩ ያስተዋላቸውን ሦስት ነጥቦች እንዲህ ሲል ያስቀምጣል፡፡

1ኛ. ገርቦሌ እግዚአብሔር በሀይል የሚሠራበት የእግዚአብሔር ባሪያ ነው፡፡ በሚያስደንቅ ሁኔታ የተነገሩና የተፈፀሙ አብረን ባገለገልንባቸው ቦታዎች ጭምር የሆኑ ነገሮችን አይቻለሁ፡፡

2ኛ. በግል በቤተሰብ ደረጃ ስለምንቀራረብ አገልጋዩ ጥሩና ለሁላችንም ምሳሌ የሚሆን የተቀደሰ ሕይወት የሚኖር ሰው ነው፡፡

3ኛ. ሰውን እኩል ይወዳል፡፡ አገልግሎትንና ጥቅምን ከተማና ገጠርን ለይቶ ሳያይና ሳያወዳድር ሁሉንም የጌታውን ፈቃድ በመጠየቅ ያገለግላል፡፡"

"እኔ አብሴ ሚዛኑ በተደጋጋሚ የወሊድ ችግር ደርሶብኛል የመጀመሪያ ልጄን በሰባት ወር ወልጄ አራት ወር ከቆየች በኋላ ሞተችብኝ፡፡ በመቀጠልም ፅንሼ ለመውለድ ሳምጥ ሳለ ፅንሱ በማህፀኔ ውስጥ ስለሞተ በኦፕራሲዮን ወጣልኝ፡፡ በዚህ ዓይነት ከትዳር የሚገኘውን የልጅ በረከት ባለማግኘታችን በማዘንና በተሰበረ





ልብ ስንኖር ሳለ ነብይ ገርቦሌ ለጉዳያቸው ወደ እኔ ቢሮ መጡ፡፡ በጣም ያዘንኩበት ነገር እንዳለና እንዲፀልዩልኝ ነገርኳቸው፡፡ ቢሮ የምቀመጥበት ወንበር ላይ ፀልየው ካበቁ በኋላ "ከአንድ ወር በኋላ ትፀንሻለሽ ፅንሱ ሦስት ወር ሲሆነው ንገሪኝ" ብለው ተለያየን፡፡

እንደተባለው ከወር በኋላ ፀነስኩኝ፡፡ አራት ወር ሲሆነው ወደቢሮዬ መጥተው ፀለዩልኝ፡፡ በሰባተኛውም ወር እንዲሁ፡፡ የመውለጃ ጊዜዬ እንደደረሰና ሆስፒታል እንደገባሁ ማንም ሳይነግራቸው መጡ፡፡ በሰላም እንደምወልድ እንደነገሩኝ ሆኖ ልጄን ታቅፌ ወጣሁ፡፡ የልጅን ነገር በተመለከተ ከባድና ከተሰፋ መቁረጥ እስከመፀነስና ልክ እንደሀኪም በየጊዜው እየተከታተሉ በምጤ ቀን ሳይቀር ሳይለዩኝ እውነተኛ የእግዚአብሔር ባሪያና አገልጋይ ሆነው በመገኘታቸው እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፡፡"

"ስለ እርሱ ሰምቼ ብዙ ጊዜ ላገኘው ስመኝ ሳለ ወደ ነቀምት ከዋናው ወርልድ ቪዥን ቢሮ የህብረተሰብ ልማት ፕሮጀክት ለመክፈት በመላኬ ነብይ ገርቦሌን በአካል የመተዋወቂያ ዕድል ስለፈጠረልኝ በመጀመሪያ በስልክ ከተዋወቅን በኋላ ቀጥሎም በአካል ተገናኝተናል"፡፡ በማለት የሚናገሩት አቶ በካኮ ዱጉማ ናቸው፡፡ "በዚያን ጊዜ ምንም ሥራ ቢበዛብኝ በተጣበበም ሰዓት ቢሆን ልጆቹ ነቀምት ሲማሩ ይኖሩበት ወደነበረው ቤት ሄጄ አገኘሁት፡፡ ተጨዋወትን አብረንም ፀለይን፡፡ ይህ ሰው በልጆቹ እጅግ ተወዳጅ ባህሪና ጨዋነትም የተባረከ መሆኑን አይቻለሁ፡፡ የእግዚአብሔር ፀጋ በእርሱ ላይ ብቻ ሳይሆን በነዚህ ቆንጆጅት ሴቶች ልጆቹ ላይ

መኖሩን ለሰው ባላቸው አክብሮትና ፍቅር ለማስተዋል ችያለሁ፡፡ በአጠቃላይ በነብዩ ሕይወት ያየሁትና ለሌሎች ምሳሌና አብነት ሊሆን ይችላል የምላቸው ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- እውነተኛ የእግዚአብሔር ሰው መሆኑንና የክርስትና ሕይወት የሚገለጥበት አማኝ መሆኑን አስተውያለሁ፡፡
- እግዚአብሔር ለሰው ካካፈላቸው ባህሪያት አንዱ ፍቅር ነው፡፡ ፍቅር የወንጌልም ማዕከል ነው፡፡ ይህ ሰው ይህ ዕውነተኛውና ለሰዎች የተገለጠው መለኮታዊ ፍቅር በግልጥ የሚታይበት ሰው በመሆኑ ስለሱ እግዚብሔርን አመሰግናለሁ፡፡
- ሌላው በገርበሌ የማየው የከበረ ህይወት በቁሳቁስ ሀብት አለመሳቡ ነው፡፡ አገልግሎቱን ሁሉ የሚያያይዘው ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር እንጂ አብሮት ከሚመጣው የወርቅ ሚዛን ጋር አይደለም፡፡ ለምሳሌ አንድ ጊዜ በጆሮዬ የሰማሁትን ነገር ለመጥቀስ ከእንግሊዝ አገር የአገልግሎት ጥሪ በአንድ ወንድም አማካይነት ደረሰው፡፡ እሱም ለዚያ ወንድም ከአንድ ቦታ የእግዚአብሔር ቃል ካነበበለት በኋላ ግብዣው ከእግዚአብሔር የመጣ ባለመሆኑ እንደማይቀበለው ነግሮ አሰናብቶታል፡፡ ያለንበትን ተጨባጭ ሁኔታ ስንመለከት ለብዙ አገልጋዮች በጥቅምና በእግዚአብሔር ፈቃድ ወይም አገልግሎት በዕድቅ ኑሮ አንፃር መካሪና ምሳሌ የሚሆን የከበረ አቋም በዚህ ሰው እናያለን፡፡ ገቢውን ተምኖ ከሚንቀሳቀሰው ከበለዓም ልብ ከፍ ያለ መንፈስ አለው፡፡

እግዚአብሔር ከነብዩ ሳሙኤል ጋር እንደነበርና የአፉ





ቃል መሬት እንደማይወድቅ ሁሉ በራሴም በሌሎችም ሕይወት የነብዩን አገልግሎት እንዲሁ እንደሆነ አስተውያለሁ፡፡

ደሳለኝ ተረፈ እንዳሁኑ ወ/ዊ ሆኖ የእግዚአብሔር መንግስት ሠራተኛ ከመሆኑ በፊት ሱሰኛና አንድ እግሩ በዝሆኔ በሽታ በመጠቃቱ ሕመምተኛ ነበር፡፡ ከንጉሡ ዘመን ጀምሮ ጌታን በድብቅ ያመልኩ የነበሩ ወ/ሮ ሥዩም ኩማ የሚባሉ እናት አንድ ሚስጥር ነገሩት፡፡ "ልጄ መዳን ትፈልጋለህ?" ሲሉ ጠየቁት "እንዴታ እማማ" በማለት መለሰላቸው፡፡ "እንግዲያውስ ሚስጥሩን ለማንም ሳትናገር የምታደርገውን እነግርሀለሁ፡፡ እዚህ አቶ መኮንን ነገዎ ቤት ሌሊት ሌሊት የሚደረግ ፀሎት አለ፡፡ የሚያገለግለው ሰው እዚያ በድብቅ ስላለ ታገኘዋለህ ሂድና እንዲፀልይልህ ለምነው" አሉት፡፡

ከዚህ በኋላ የሆነውንና ስለዚህ የእግዚአብሔር ባሪያም የሚለውን ጨምሮ እንዲህ ብሏል፡፡ "እንደነገሩኝ ወዲያውኑ መሄድ ፈለኩ ነገር ግን አገልጋዩ ተደብቆ ስላለ ማታ በጭለማ ማግኘት እንዳለብኝ ስለነገሩኝ በትዕግስት እስኪመሽ ጠበቅሁ፡፡ ጨለምለም ሲል ወደ አቶ መኮንን ቤት ሄጄ አገኘሁት፡፡ ገርበሌም ሰላም አለኝና ዝም አለኝ፡፡ ታማሚ በመሆኔ እንዲፀልይልኝ ለመንኩት፡፡ "ነገ ና ዛሬ ላንተ መልዕክት አልተሰጠኝም" ስላለኝ እያዘንኩ ግዙፉን ያበጠ እግሬን በጨለማ እየጎተትኩ ወደ ቤት ተመለስኩ፡፡

በሁለተኛው ምሽት ሄድኩና አገኘሁት፡፡ "ጌታን ማወቅና ማመን ትፈልጋለህ" አለኝ እኔማ ትናንትናውኑ ፈልጌ መጥቼ ነበር አልኩት፡፡ "ስለ ፈውስህ የሚወስነው መንፈስ ቅዱስ እንጂ እኔ ስላልሆንኩ ነው እስከምፀልይ ያቆየሁህ አለኝ፡፡ ከዚያም ውሀ ቀድቶ ሰጠኝ "ይህንን ጠጣና ሁለት ነገር ይሆንልሀል አንደኛው እግርህ ይድናል፣ ሁለተኛው ከዚህ ውሀ ተከትሎ የጌታ መንፈስ ወደ ውስጥህ ይገባል ይለውጥሀል ሕይወትህን ይቀይራል፡፡" ተቀብዬ ጠጣሁ፡፡ ጥርስ እንዳለው ነገር እግሬን እየበላ ይጠዘጥዘኝ የነበረው ቁስሌ ተወኝ እብጠቱም ጠፋና ጤማ የሚያስገባ እግር ሆነ፡፡ እዚያው ቤት ወደ ጌታ የሚመጡትን ሰዎች ሲያስተምር ሌሊት ወንዝ ወስዶ ሲያጠምቅ ከርሱ ባለመለየት ረዳቱ ሆንኩ፡፡

በዚህ አይነት በተደጋጋሚ ወደዚያ አገር እየመጣ ሲያገለግለን ሳለ አንድ ጊዜ በክትትል የደረሱበት ካድሬዎች ሁላችንን አቶ መኮንንን ጨምሮ አፍሰው አሰሩን፡፡ በማግስቱ ወደ ፖሊስ ጣቢያ በመንገድ አጅበው እየወሰዱን እያለ ነብይ ገርቦሌ ከሚነዱት እስረኞች መሀል ተለይቶ ወጥቶ ሄደ፡፡ እኛ እስረኞቹ እያየነው አጃቢዎቹ ፊት ለፊታቸው የሚሆነውን ነገር ባለማየታቸው ተገረምን፡፡ በማግስቱ በትልቅ አገልግል ስንቅ ተሸክሞ ጣቢያ ድረስ አመጣልን፡፡ የጠየቀውም ስለሱ ያነሳም አልነበረም፡፡





ሌላም ጊዜ ከለላ እሚባል አገር ለወንጌል ሥራ ሄደን የአገሩ ሰዎች የሚያመልኩትን የአድባር ዛፍ አየ፡፡ "ሊመለክ የሚገባው አንድ እግዚአብሔር ብቻ ነው ሰዎችን አሳውረህ ከአምላካቸው የለየህ የጨለማ አሠራር አንተንም ይህን ማምለኪያ ዛፍም አፈርሳለሁ በሰዎቹም ላይ ያለ ጨለማ ተገፍፎ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ እፀልያለሁ" በማለት ተናገረ፡፡ ዛፉም ደረቀ የሕዝቡም ልብ ከአጋንንታዊ አምልኮ ወደ ወንጌል ተመለሰ፡፡ በከለላ እግዚአብሔር ከበረ፡፡

**መጋቢ ሀምቢሳ ታሲሳ ስለ ነቢዩ የሚከተለውን ብሏል፡-**

"ነቢይ ገርቦሌን በደንብ ማወቄ ብዙ ጠቅሞኛል፡፡በእምነት ስለመኖር፣ በእግዚአብሔር ስለመደገፍ፣ ስለትዕግስት፣ የሚጠሉንን ስለመውደድ፣ ለሚያሳድዱንና ስማችንን ለሚያጠፉ መልካም ስለማድረግ፣ ስለመቆረስ/ስለመስጠት/ና እግዚአብሔርን ስለመስማት ከእሱ ብዙ ተምሬያለሁ እግዚአብሔር ይባርከው፡፡

ነቢይ ገርቦሌ በዘመናችን እግዚአብሔር ያስነሳዉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያገለግል የእግዚአብሔር ባሪያ ነዉ፡፡ይህንን ደግሞ በብዙ መንገድ ማረጋገጥ በመቻሌ ዕድለኛ ነኝ፡፡

እግዚአብሔርን ሳይሰማና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሳይረዳ ምንም አለማድረጉ፡- አብዛኛዉን ጊዜ እግዚአብሔርን እየሰማና ፈቃዱ ምን እንደሆነ ከተረዳ በኋላ ነገሮችን ማከናወንን ይወዳል፡፡እግዚአብሔር ሳይናገረዉ ምንም ነገር ማድረግ

አይፈልግም፡፡ እግዚአብሔር የተናገረዉን ማንኛውንም ነገር ዋጋ ቢያስከፍለዉ ይከፍላል እንጂ ከማድረግ አይቆጠብም፡፡ ይህን ብዙ ጊዜ በእሱ ሕይወትና አገልግሎት አይቻለሁ፡፡ለምሳሌ፡-

- ከብዙ ቦታ ለአገልግሎት ሲጠይቁት ፀልዩ እግዚአብሔር ካለ ይሆናል ይላል እንጂ ጥሩ ነዉ መጥቼ አገለግላለሁ ሲል ሰምቼ አላውቅም፡፡ ሰዎችን ለማሳመን ብሎ ብዙን ጊዜ የተለያየ ነገር ሲያደርጉና እሱ እግዚአብሔር አልተናገረኝም ብሎ እምቢ ሲል አያለሁ፡፡ እሱ እምቢ ሲላቸው በእኔ ምልጃ እሺ እንዲላቸዉ ጥረት ሲያደርጉና እኔም ለምን እምቢትላለህ ብታገለግላቸዉ መልካም ነዉ ብለዉም እግዚአብሔር አልተናገረኝም ብሎ እምቢ ብሎኛል፡፡ አንዳንድ ቦታ ደግሞ ሰዎችም ሳይጠይቁት እግዚአብሔር ሂድ ብሎኛል ብሎ ከእነሱ ምንም ሳይፈልግ ሄዶ ያገለገለበት ሁኔታ አለ፡፡ስለዚህ በሰው ግፊትና ምሪት ሳይሆን እግዚአብሔር ወደ መራው ለመመራት የወሰነ አገልጋይ ነዉ፡፡ ከዚህም የተነሳ ሁኔታዉ አንዳንድ ጊዜ በደንብ ለማያውቁት ሰዎች እንቆቅልሽ ይሆናል፡፡

- አንድ ጊዜ ለአገልግሎት አብረን አንድ ቦታ ሄድን፡፡ምሳ በልተን በምናድርበት ክፍል ዉስጥ ሆነን ስለእግዚአብሔር ሥራ እየተነጋገርን እያለን አንዲት እህት በጣም እያለቀሰች የእግዚአብሔር ሰዉ ፀልዩልኝ ብላ እምባዋን እያፈሰሰች ትጠይቃለች፡፡ከእምባዋ ብዛት የተነሳ እኔ በጣም አዘንኩላት፡፡እሱ ግን ዝም ብሎ ያያታል፡፡አለባበሷ በጣም





መልካም ነዉ፣ጥሩ ኑሮ የምትኖር ትመስላለች በዉጫዊ ገጽታዋ፡፡ ደጋግማ እባክዎን የእግዚአብሔር ሰው ይጸልዩልኝ ስትል በታላቅ ቁጣ ድምጽ "እምቢ አልፀልይልሽም" አላት፡፡እኔ በጣም ደነገጥኩ፣ምክንያቱም ለምን እንዲህ ትባላለች ከማለት የተነሳ፡፡እሷ ግን ተስፋ ሳትቆርጥ አሁንም የእግዚአብሔር ሰዉ ይፀልዩልኝ ብላ እያለቀሰች ለመነች፡፡ "ለአንቺ የእኔ ፀሎት ሳይሆን ንስሐ ነዉ የሚያስፈልግሽ ስለዚህ ንስሐ ግቢ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቂ" ሲላት የበለጠ ደነገጥኩ፡፡ቀጥሎም "እንዴት ይህን የመሰለ ኃጢአት ትሰርያለሽ" ብሎ የሰራችውን ኃጢአት በዝርዝር ከወረቀት እንደሚያነብ ሰው ሲነግራት መቆም አቅቷት ተዘረረች፣ንስሐም ገባች፡፡በዚያን ጊዜ እኔ እንደሐዋሪያት ዘመን ሰዎች የሚሉትን ሳይሆን ሐዋሪያት የሚዋሹትን እንዳጋለጡት ሁሉ በዚህ ዘመንም እግዚአብሔር የሚለዉን ብቻ ተረድቶና ተገንዝቦ የሚያደርግ ቅሬታ እግዚአብሔር እንዳለዉ ተረዳሁ፡፡

የእግዚአብሔርን ፈቃድ አዉቆ ማድረጉ ብቻ ሳይሆን እንዴት ማድረግ እንዳለበትም አስተዉሎ ያደርጋል፡፡ከዚህም የተነሳ አንዳንዶች እግዚአብሔር በእሱ በኩል የሚያደገዉን ሥራ ሳይረዱ ይችላሉ ብዬ አስባለሁ፡፡ የእኛ ሰዉ የለመደው መልዕክት፣ፈዉስ፣ተአምራት ወዘተ ሲፈጸም በፀሎት ዓይንን በመጨፈን እንደሆነ ያስባል፡፡ነቢይ ገርቦሌ ግን ከሌሎች የሚለየው በጨዋታ መሀል፣በጥቅስ፣በፀሎት ፣በድርጊት

እግዚአብሔር የተናገረዉን ያደርጋል፤እግዚአብሔር አድርግ ያለዉን ያደርጋል፡፡ስለዚህ በደንብ የማያውቁት ብዙ ነገሮች ሊያመልጣቸው ይችላል፡፡አንድ ጊዜ አንድ የእግዚአብሔር ሰው የሆኑ ቄስ እንዲህ አሉኝ እሱን በደንብ የማያውቁ እሱ የጨረሰዉን ገና ይፈጽምልናል ብሎ ይጠብቃሉ ብሎኛል፡፡ሌላ ሰው ደግሞ ከአዲስ አበባ እስከ ነቀምቴ አብሮ በአንድ መኪና መጥቶ እያንዳንዱ ንግግሩና አደራረጉ መልዕክት ነው ብሎኛል፡፡እግዚአብሔር ደግሞ ስለሁሉ ነገር ይነግረዋል ሁሉም ደግሞ ትክክል ነው ብሎ ነበር፡፡

አንድ ሰው አንድ ጊዜ እንዲህ ብሎ ሲመሰክር ሰምቻለሁ፡፡ አዲስ አበባ ቡና ጭኖ አምጥቶ ከሸጠ በኋላ ወደ ብር72,000 ተዘረፈ፡፡የሚያደርገው ግራ ገባዉ፡፡ምን ማድረግ አለብኝ ብሎ አውጥቶ አወረደ፡፡ይህን ሁሉ ብር ተዘርፌ እንዴት እገባለሁ ሰው ምን ይለኛል ራሴን ላጥፋ ክርስቲያን ስለሆንኩኝ እንዴት ይህን አደርጋለሁ ምን ላድርግ ታዲያ እያለ አዲስ አበባ ሹፌሮች ሆቴል የሚባል ቦታ ፊት ለፊት ቆሞ ብቻውን ከራሱ ጋር እያወራ እያለ አንድ ሰው እጁን ጨብጠ ሰላም ላንተ ይሁን ይለዋል በአፋን ኦሮሞ፡፡ከሰላምታው ቀጥሎ ተዘረፍክ አይደለም ያለህን ሁሉ አጣህ አይደለም አንተ ለምን የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር አልሰጠህም ስለዚህ ይህ ደርሶብሃል እኔ ደግሞ ገርባሌ እባላለሁ ሲል በስምና በዝናው ያውቀው ስለነበር በጣም ደስ አለው ከዚያ በመቀጠል ከአሁን በኃላ የእግዚአብሔርን ሁለተኛ ለራስህ እንዳታደርገዉ





አሁን ግባና ተኛ ጥዋት በማለዳ አንድ ሰዉ ዕቃ ገዝተህበት እንድትገባ ገንዘብ ያመጣልሃል ድሮ ከምትገዛው በታች ገዝተህ አትገባምና ሂድና ዕረፍ አለው፡፡

ቡና በሸጥኩበት ብር ሸቀጥ ገዝቼ ወደ ቤት እመለስ ነበር፡፡ ወዲያውም ገብቼ ተኛሁ ደንበኛ እንቅልፍም ወሰደኝ እንደተባለዉ ጥዋት በማለዳ አንድ የሚያዉቀኝ ሰዉ ችግሩ እንዳደረሰብኝ ሰምቶ ሸቀጥ ገዝቼ እንድገባበትና በኋላ እንድመልስለት ብር10,000 ይዞልኝ መጣ፡፡በጣም ደስ አለኝ ከዚያ ወደ ደንበኛዬ ዕቃዉን ለመግዛት ሲሄድ እሱም የደረሰብኝን ዝርፊያ ሰምቶ በጣም አዝኖ ስለነበር ሲያየኝ በጣም ደስ አለው ፈገግ ብሎም ተቀበለኝ፡፡ከዚያም እግዚአብሔር ያደረገዉን ስንነጋገር እንዲህ አለኝ ተጨማሪ የምትፈልገው ዕቃ ካለ ውሰድ ሸጠህ በኋላ ታመጣልኛለህ አለኝ፡፡እግዚአብሔር በነቢዩ በኩል የተናገረዉን ፈጸመ ብዙ ሸቀጥ ይዤ ገባሁ፡፡

እቤት ስደርስ የደረሰብኝን ቤተሰቦቼም ሰምተው ስለነበር ሲያገኙኝ እውነት አልመሰላቸውም በጣም ደስ አላቸው፡፡የባለቤቴ አባት ወደ ቤታቸው ጠርተው ስለደረሰብህ ችግር ምንም እንዳታስብ ልጅ ስለሆንክ የበለጠ ሰርተህ ማግኘት ትችላለህ ብለው ከመከሩኝ በኃላ ወስደህ የመጣውን የሰዉ ዕዳ አንድ መኪና ቡና እሰጥሃለሁና ሂደህ ሸጠህ ክፈል አሉኝ፡፡አሁን ሁሉ ነገር ተስተካከሏል" ብሎ እኔና ነቢይ ገርባሌን አንድ ቀን እራት ጋብዞን መስክሮልናል፡፡በመርካቶ ውስጥም ተስፋ ለቆረጡት እግዚአብሔር

መልዕክተኞች ልክ ከሞት ታድጎ ታሪካቸውን ይለውጣል።ግን እንዲህ አይነት ቦታ እሺ ብሎ መሄድ የሚከብድ ይመስላል።እግዚአብሔርን ሰምቶ ለሚታዘዙት እግዚአብሔር በሁሉ ስፍራ ከእነሱ ጋር ይሆናል።

አንድ ጊዜ ለአገልግሎት አንድ ቦታ አብረን ሄድን።ፕሮግራሙ የሶስት ቀን ኮንፍራንስ ነበር። በሶስተኛ ቀን አጠቃላይ የሆነ ፀሎት ለበሽተኞች ያደርጋል ነቢይ ግርቦሌ። በመገለጥ የተናገረው ነገር አልነበረም። የፀሎት ጊዜዉም በጣም አጭር ነበር። ፀሎቱ አልቆ ወደ ሌላ ፕሮግራም ለማለፍ ትንሽ እንደተቀመጥን ከጉባዔ መሀል አንድ እናት እየዘለሉ የለም እኮ የለም እኮ እያሉ ሆዳቸውን በእጃቸው ያሳያሉ። እሳቸዉን ያየ ሁሉ ከጉባኤው መካከል እየዘለለ ይወድቃል። አንዳንዶች ደግሞ ግራ ገብቶአቸዉ ነገሩን በትክክል ለማጣራት ብሎ ተነስቶ ቆሟል። እኛም ነገሩን ማወቅ ስላልቻልን ግራ ተጋባን። በኋላ ንገሩን ምንድነው ብለን ስንጠይቅ እኚህ እናት ሆዳቸው አብጦ ለብዙ ጊዜ እንዳረገዘች ሴት ሆኖ ኖሯል። መጀመሪያ አከባቢ ሰዎች በሽታ መሆኑን ሳያዉቁ ብዙ ነገር ብለዋል። ግን እግዚአብሔር ነቢዩ በፀለየው አጭር ፀሎት ይህንን ተአምራት አድርጎ ጉባዔዉን ሲያስደስትና እኚህን እናት ሲያሳርፍ ማየት ችያለሁ ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን።እግዚአብሔር በሚፈልገው መልኩ ነገሮችን ስለሚያደርግ በእሱ ፀጋ ለመጠቀም የሚያደርገውን በደንብ መከታተል ያስፈልጋል ካልሆነ ግን ያመልጣል።





በቅርብ ጊዜ እራት ማለትም እኔና ባለቤቴ እንዲሁም ነቢይ ግርቦሌና ባለቤቱ ሆነን አንድ ቦታ እራት ለመብላት ገባን።እራት አዘን ሳለን እሱን የሚፈልጉ ሌሎች ሰዎችም መጡ።እነሱም የራሳቸዉን አዘዉ እየተጠባበቅን እያለን ሁለት ሴቶች መጥተዉ ተቀመጡ።እነሱን ተከትሎ ሁለት የዉጭ ሀገር ዜጎች መጥተዉ ከሁለቱ ሴቶች ጋር ተቀመጡ።ነቢይ ግርቦሌ በእነሱ ላይ ትኩረቱን ጣለ።ከእኛ ጋርም እሱን ፍላጋ ከመጡት ሌላው ቡድን ጋር ንግግር አቆመ።

ሰዎቹ የሆነ መጠጥ አዘው መጣላቸው፣ተከፈተላቸዉም።ነቢይ ግርቦሌ ትኩረቱ አሁንም በእነዚህ ሰዎች ላይ ነው። እጁን ወደ ላይ እያነሳ ሳለ። በቅጽበት መጠጡን የያዘው ጠርሙዝ ፈንድቶ ይሁን ወድቆ ይሁን ምን እንደሆነ ሳላውቅ ተሰባብሮ መጠጡ በአራቱም ልብስ ላይ ፈሶ ምንም ሳይሉ አፍረው የሆነ ነገር እንደሚያባርረዉ ሰው በችኮላ ሽሽተው ሲወጡ እሱ ከእኛ ጋር ተቀምጦ እራት በልቷል።

ሰውን ሁሉ መውደዱ ፡- በሰዎች መካከል በምንም ልዩነት ሳይፈጥር ከልቡ ሰውን ይወዳል። ሰዎች ከልቡ ስለሚወድ ሰላምታው ይለያል። አቀራረቡም ይለያል። በደንብ በማያዉቁት ላይ ጥያቄን የሚፈጥር ነው። ሰውን ከልቡ ስለሚወድ ለሰው ያዝናል። ለሰው ያስባል።ለሰው ይቆረሳል።

አንድ ጊዜ አንድ ወንጌላዊ በጣም ርቦኝ በነቀምቴ ከተማ

ዉስጥ ስሄድ መንገድ ላይ ነቢይ ገርባሌ አገኘኝ አለ፡፡እንዳገኘኝም ሰላምም ሳይለኝ "ተራብክ አይደለም" ብሎኝ ይዞኝ ወደ ምግብ ቤት ገብቶ ሁለት ምግብና ሁለት ለስላሳ አዘዘ፡፡ሲቀርብ የአንተ ነው አመስግነህ ብላ አለኝ፡፡እኔ ግን ሁለት ስለሆነ ሁለቱንም መብላት አለብኝ ስል እምቢ ለማለት ሰሞክር አንተው ሁለተኛ እንዳይርብህ በደንብ ብላ አለኝ እኔም በደንብ በላሁ ከዚያ ቀን ጀምሮ እግዚአብሔር ብዙ ነገሮቼን ለወጠ ብሎኛል፡፡ሰውን ከመውደድ የተነሳ ለዚህ ሰው ተቆረሰ በዚያዉም በዘመኑ ፈውስ እንዲሆን አደረገ፡፡

በ1992 ዓ/ም መጨረሻ ላይ የመንግስት ሥራ አቁሜ አገልግሎት ጀመርኩ፡፡ ቤተክርስቲያን ደግሞ በዚያን ጊዜ ከፍተኛ የሆነ ችግር ላይ ነበረች፡፡ አንድ ቀን አንድ ብር ብቻ ኪሴ ዉስጥ እያለ ማታ አንድ ሰዓት አከባቢ ነቢይ ገርባሌን አገኘሁት፡፡ የሆነ ቦታ ለመሄድ ይቸኩል ነበር፡፡ የተገናኘነው ታክሲ ቦታ ነው፡፡ እሱ ታክሲ ለማያዝ ፈልጓል፡፡ እንዲህ አለኝ "አንድ ብር አለህ አይደለም" አለኝ ቶሎ አዎ አልኩ የታክሲ እንድከፍልለት የፈለገ መስሎኝ አንድ ብር አለ አልኩት፡፡ ከዚያ እንዲህ አለኝ እኔም ያለኝ አንድ ነዉ አምጣ እንለዋወጥ አለኝ፡፡ ሰጠሁትና ወሰድኩ፡፡ በኃላ የሰጠኝን ስመለከተዉ አስር ብር ነዉ የሰጠኝ፡፡ በጣም ተገረምኩ፡፡ የእኔን ችግር ተረድቶ እኔ ብቸገር ይሻላል ብሎ አስቀደመኝ፡፡ ሰውን ከልቡ ስለሚወድ ከራሱ ይልቅ አብዛኛዉን ጊዜ የሰውን ያስቀድማል፡፡ ይህንን በማድረጉም እግዚአብሔር አላሳፈረውም፡፡ እግዚአብሔር ጻድቃንን ይባረካልና፡፡ (መዝ.5፡12)





ጌታ ኢየሱስ በነብይ ገርባሌ ያደረገው በወረቀት ተጽፎ የሚያልቅ ነገር አይደለም በጣም ብዙ ከመሆኑ የተነሳ፡፡ ለእኔ ደግሞ ነቢይ ገርባሌ በጣም የተለየ ነው፡፡ በእሱ ድጋፍና ፀሎት እግዚአብሔር ብዙ ድንቅና ተአምራትን ለእኔና ለቤተሰቤ አድርጓል፡፡ ግን ለሌሎች ትምህርት ይሆን ዘንድ ይህች አነስተኛ ምስክርነት ሰጥቻለሁ፡፡ እግዚአብሔር ይባርካችሁ፡፡

ፓስተር ሀምቢሳ ታሲሳ

## የምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ወንጌላዊያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ዋና ፀሐፊ

"ጌታ ባያት ጊዜ አዘነላትና አታልቅሺ አላት፡፡ ቀርቦም ቃሬዛውን ነካ የተሸከሙትም ቆሙ፡ አለውም አንተ ጎበዝ እልሀለሁ ተነሳ፡፡ የሞተውም ቀና ብሎ ተቀመጠ...እግዚአብሔር ህዝቡን ጎበኘ እያሉ እግዚአብሔርን አመሰገኑ" (ሉቃስ 7፡13-16)

ከላይ እንዳየነው የእግዚአብሔር ጉብኝት ሙታንን ከመቃብር ይመልሳል ወንድማችን መርጋ ስማ የእግዚአብሔር ጉብኝት ደርሶላቸው ከመቃብር ስለተመለሱና እሳቸውም የአይን መስክር የሆኑባቸውን ሁለት ሰዎች ታሪክ ለእግዚአብሔር ክብር ይነግሩናል፡፡

"ደረጀ ዳስጋ የተባለው ጓደኛዬ በጠና ታሞ ስናሳክመው ቆይተን በመጨረሻ ሀኪሞቹ ተስፋ ስለሌለው ወደ ቤት ይዛችሁት

ሂዱ ስላሉን ከሆስፒታል አውጥተነው ጧት በአውቶብስ ወደ አገራችን ለመግባት ነቀምት ሆቴል አሳረፍነው፡፡ በዚያው ምሽት ነብይ ገርቦሌ ነቀምት እንዳለ ወሬ ሰማሁ፡፡ ካለበት አፈላልጌ አገኘሁት፡፡ በሽተኛውን ወዳስተኛሁበት ሆቴል ይዤው ሄድኩና እባክህ ፀልይለት፡፡ ሀኪም ተስፋ እንደሌለው ቢነግረንም ለእግዚአብሔር የሚከብድ ነገር ስለሌለ እባክህ የልጆች አባት ነውና ፀልይለት አልኩት፡፡ ነብዩ ትንሽ ከፀለየ በኋላ ይህ የጥንቆላ ሥራ ነው፡፡ የሚፈለገውም አባትና ልጅ እንዲሞቱ ነው፡፡ ለምልክት እንዲሆናችሁ አገር ቤት ያለው ልጅ መታመሙን ከጥቂት ጊዜ በኋላ ትሰማላችሁ እግዚአብሔር ስለደረሰላችሁ ለምልክት ነው እንጂ ሁለቱም ይድናሉ በማለት ወደ በሽተኛው በመጠጋት በሽታው ያለው ጭንቅላቱ ውስጥ በመሆኑ ከላይ ወደታች እንደልብስ እስከ እግርህ ወርዶ ካንተ ይወጣል አለው፡፡ ራሱ ላይ የሚሰማው ሕመም ወደታች እየወረደ እየወረደ "የት ጋ ይሰማሃል?" ሲለው "ደረቴ ላይ፣ አሁንም ወረደ ወገቤ ላይ፣ ጉልበቴ ላይ" እያለ እንደተባለው እስከ እግር ጥፍሩ ሀመሙ ወርዶ ጠፋ ተነሳና ስፖርት ሥራ ብሎት ከአልጋው ተነስቶ ጎንበስ ቀና ማለት ጀመረ ፍፁም ጤነኛ ሆነ፡፡ እኔም ገርቦሌን ሸኘሁትና ወደ ሆቴል ስመለስ ልጁ በጠና ታሞ ለሀኪም ነቀምት እንዳመጡት ነገሩኝ፡፡ የጥንቆላ ሥራ ስለፈረሰ አልተደናገጥንም፡፡ ልጁም ተሻለውና ዳነ ከአባቱ ጋር ወደ ቤታችን ተመለስን፡፡

ሁለተኛው እግዚአብሔር ከሞት አፋፍ የመለሰው ሰው አብዲሳ ጎበና የሚባል የመስሪያ ቤቴ ባልደረባ ነው፡፡ ለሥራ ጉዳይ ከጊዳ ወደ ነቀምት እየመጣ እያለ "መርጋ" አለኝ አቤት አልኩት፡፡





"ዘንድሮን አላልፍም እሞታለሁ" አለ፡፡ አይዞህ አትሞትም ጌታ አለ በማለት ለማረጋጋት ብሞክርም እየባሰበት ሄዶ ከመጀመሪያው የከፋ ነገር ይናገር ጀመር፡፡ ነቀምት ከገባንም በኋላ ምናልባት በያዘው ሽጉጥ ራሱን ያጠፋ ይሆናል ብዬ ስለፈራሁ አልተለየሁትም፡፡ እጠብቀው ጀመር፡፡ በዚህ መሀል ነብይ ገርቦሌን ከሰዎች ጋር መንገድ ላይ አገኘሁት፡፡ በጣም እንደሚያስፈልገኝ ብነግረውም አሁን ከነዚህ ሰዎች ጋር ነኝ በኋላ እመጣለሁ አለኝ፡፡ በምንም አይነት እንደማለቀው ነገርኩትና አብሮን ወዳረፍንበት ቦታ ሄደ፡፡ ለአብዲሳ ፀልይለት አልኩት፡፡ አብዲሳን ትኩር ብሎ ካየው በኋላ "ሠላም ነህ" ሲል ጠየቀው "አዎ ሰላም ነኝ" ሲል መለሰለት፡፡ ምን ሰላም ነህ ልትሞት የቀረህ ጥቂት ሰዓታት ነበሩ አሁን ወደ ደቂቃ እየወረዱ ነው ሰላም አይደለህም ሲል መለሰለት፡፡ ፀለየለትና ሊወስድህ የመጣው ሞት ካንተ ሄዷል በህይወት ኑር አለው፡፡ ጌታን እያመለከ እስከ ዛሬ በሰላም አለ፡፡

"እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያት ሌሎቹም ነቢያት ሌሎቹም ወንጌልን ሰባኪዎች ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ፡፡ ሁላችን የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት ሙሉ ሰውም ወደመሆን የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥረትና ለክርስቶስ አካል ሕንፃ ፍፁማን ይሆኑ ዘንድ፡፡" (ኤፌሶን 4፡11-13)

ለቤተክርስቲያን መታነፅ ጌታ ከሰጣቸው ስጦታዎች ውስጥ አንዱ የነብይነት ፀጋ ነው፡፡ እውነተኛ ነብያት የሚለዩባቸው

ባህሪያት የሚከተሉት ናቸው በማለት ስለነብይ ገርባሌ አገልግሎት ያለውን ከበሬታ የሚገልፀው ፓ/ር ኢያሱ ቶሎሳ የሚከተለውን ብሏል፡፡

"እውነተኛ ነብያት፡- ለእግዚአብሔር ቃል ታማኞች ናቸው
የእምነት ሰዎች ናቸው
የፀሎት ሰዎች ናቸው
የፍቅር ሰዎች ናቸው
በባህሪያቸው ትሁታን ናቸው፡፡

የዚህ ሰው እምነቱና ፀሎቱ ተግባራዊ ናቸው፡፡ ለምሳሌ በአንድ ወቅት ጋምቤላ አብረን የማገልገል ዕድል ገጥሞኝ በነበረበት ጊዜ የሆነውን መጥቀስ እፈልጋለሁ፡፡ ወሩ መጋቢት ሲሆን የዚያ አካባቢ ሙቀትም ከፍተኛ ባሬው በዚያ ወር ነውና የሙቀቱ መጠን አርባ ዲግሪ ሴንቲግሬድ ደርሶ ነበር፡፡ እንኳንስ ስብሰባ ተደርጎ አገልግሎት መስጠት ይቅርና ሰዎች በተቀመጡበት በሙቀቱ ምክንያት የሚሞቱበት ጊዜ ነበርና "ይህ አየር እንዲቀዘቅዝ እግዚአብሔ ዝናብ እንዲልክልን እፀልያለሁ ታምናለህ" ሲል ጠየቀኝ አምናለሁ ስል መለስኩለትና አብረን አጭር ፀሎት አድርገን ተኛን፡፡ ጧት ከነበረው ከባድ ዝናብ የተነሳ ወደ ምናገለግልበት ቤተክርስቲያን መሄድ እስከሚያቅተን ሁኔታው ተለወጠ፡፡ አገሩ ቀዘቀዘ እኛም በሰላም አገልግሎታችንን ጨርሰን ተመለስን፡፡"

የዚህ መፅሐፍ ደራሲ ባለቤት ወ/ሮ ታደለች ደገፉ ስለነብይ የሚከተለውን ብላለች፡፡ "ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር በዚህ ሰው ተናግሮኛል አፅናንቶኛል መክሮኛል ለየት ያለውና እግዚአብሔር





በቀጥታ ጣልቃ የገባበት ጉዳይ ግን በአባቴ ህመም ወቅት ነው፡፡ አባታችን በጠና ታሞ ከነበረበት ገጠር ወደ ከተማ በፈረስ በሰው ድጋፍ መጥቶ እየታከመ ከእህቴ ቤት ተኝቶ ነበር፡፡ ሕመሙም ድንገተኛ አጣዳፊና አስደንጋጭ ከመሆኑም በላይ ተለዋዋጭ ነበር፡፡ ቀን የሚያመው ሌላ ነው የሌሊት ሕመሙ ደግሞ ሌላ ነው፡፡ በተለይ ሌሊት በጣም ይጨነቃል ይሰቃያል፡፡ በዚሁ አይነት አንድ ምሽት እንዳች ነገር ጉሮሮውን ያነቀው ይመስል ፊፅሞ መተንፈስ አቃተው ካልተነፈሰ የሚቀጥለው ነገር ያስፈራቸው ዘመዶቹ ወዲያውኑ ደውለው ነገሩኝ፡፡ ቤታችን ውስጥ ጥቂት ከፀለይን በኋላ ባለቤቴ ለገርባሌ ደውሎ ሁኔታውን ነገረው፡፡ አባቴ የሚገኝበትን የስልክ አድራሻም ሰጠው፡፡

መተንፈስም መናገርም የማይችለው አባቴን በስልክ "አንተ ትንፋሻቸውን የያዝክ ልቀቅ" በማለት አዘዘና ፀለየለት የአባቴን ጉሮሮ ያነቀው ነገር ለቀቀው መተንፈስና መናገርም በዚያው ቅፅበት ቻለ፡፡ እኛም ከአዲስ አበባ ደውለን አነጋገርነው፡፡ ይህ በአይኔ ፊት የሆነ ተአምራዊ የእግዚአብሔር ጉብኝት ነው፡፡

# የፅድቅ ጠላቶች

"ዮሴፍም ፊቱ መልከ መልካምና ውብ ነበር... የጌታውም ሚስት በዮሴፍ ላይ አይንዋን ጣለች ከእኔ ጋር ተኛ አለችው እርሱም እምቢ አለ። (ዘፍጥረት 39፡6-7)

አንዴ በተባለችው ከተማ አገልግሎት ሰንብቶ ወደ ቤቱ ወደ ጊዳ እየተመለሰ ነበር። እንደሚታወቀው ሁሉም ጉዞው በእግር ነው። እሱ ብቻ ሳይሆን ሌሎችም አገልጋዮች ከነደረሰ ገለታና ከነዱሬሳ ዲንሳ እስከ ዶ/ር ኃይሌ ወ/ሚካኤል ድረስ ምድራቱን በእግራቸው ነው የሚያዳርሱት። ዛሬ ግን በቅሎ የሚነዱ ነጋዴዎች በመንገድ አብረውት ይጓዙ ስለነበረ ጠጋ ብሎ "እባካችሁ ሻንጣዬን በቅሏችሁ ላይ ጣል አድርጉልኝ" ሲል ነጋዴዎቹን ሴቶች ለመናቸው። እነሱም የሸንኩርት ነጋዴዎች ሲሆኑ ቤታቸው ጊዳ ሆኖ ሽንኩርት በሁለት በቅሎ ጭነው እየተመለሱ ነበር።

ሴቶቹ ወጣቱን በመሽኮርመም እያዩ እርስ በርሳቸው ተንሾካሾኩ። "እንጭንልሀለን ሃምሳ ብር ከከፈልክ" የሚስጥራቸው ውጤት መሆን ነው። "እኔ ያለኝ ሃያ ብር ነው ሃያ ብር ልስጣችሁ" ሲል ዳግመኛ ልመናውን አቀረበ። እያመነቱ እያለ ያለውን ሃያ ብር አውጥቶ ሰጣቸው። የልብስ ሻንጣውን ሽንኩርቱ ቀርቃባ መሀል በመጫኛው ጫፍ አሰሩለትና ጉዞ ጀመሩ። እየተጓዙ እያለ ጫካ ውስጥ ሲደርሱ ወደፊት ወደኋላ ካዩ በኋላ "መክፈል ያለብህ ሃምሳ ብር ነው" አሉት "ሀምሳ ብር የለኝም ያለኝን ሰጥቻችኋለሁ" አለ "መክፈል አለብህ" አሉና ፊቱ ቆሙ መንገዱን በመዝጋት። "የለኝም





ካልፈለጋችሁ ብሬን መልሱና ሻንጣዬን አውርዱልኝ" አላቸው። "አናወርድም ገንዘብ ከሌለህ ሌላ ምርጫ እንሰጥሀለን" አሉና በቅሎዎቹን መንዳት አቁመው ወደ እርሱ ጠጋ ብለው "ከሁለታችን ማን ያምራል?" ሲሉ ጠየቁት። "እግዚአብሔር ግሩምና ድንቅ አድርጎ ስለፈጠራችሁ ሁለታችሁም ታምራላችሁ" በማለት መፅሐፍ ቅዱሳዊ መልስ ሰጣቸው። "ሁለታችንም እኩል ቆንጆ ከሆን ከምትመርጠው ከአንዳችን ጋር ወደዚህ ጫካ ገብተን እንተኛለን" በማለት የበለጠ ተጠግተው መሀል አገቡት። "እኔ ባለትዳር ነኝ እንዲህ አይነቱን ነገር በያገኘሁበት የማደርግ ሰው አይደለሁም"አለ። "ወይ ሃምሳ ብር ታመጣለህ ወይ ካንዳችን ጋር ትተኛለህ ከሁለቱ ምረጥ" አፋጠጡት። ሃምሳ ብር የለኝም ያለኝን ሰጠኋችሁ ሲል መለሰላቸው። "ከሌለህ በግድህ ትተኛለህ" ኃይል በተቀላቀለበት ድምፅ። "አልተኛም ሃያ ብሬን መሬት አስቀምጡና ሂዱ" ከመሀላቸው ፈንጠር ብሎ ወጣ። "ሃያ ብርህማ እጃችን ገብቷል የማነህ ብልጥ አታገኛትም" እያሾፉ የፍቅር ልመና ባለበት መቅለስለስ መለሱለት።

ፈንጠር ብሎ በቆመበት አንድ ነገር ልንገራችሁ" ሲል ጀመረ "አንድ ኤልሳ የሚባል ሰው ነበረ እናንተ አታውቁትም እንደዚህ እንደኔ ከቦታ ቦታ ለተመሳሳይ ሥራ ሲዘዋወር ብዙ ልጆች ተሰብስበው ፀጉር ስላልነበው አንተ መላጣ ከዚህ ከተማ ውጣ እያሉ ሰደቡት። ሳይነካቸው በሰላም የሚሄደውን ሰው ሰላጠቁት በእግዚአብሔር ስም ረገማቸው ከጫካ ሁለት ድቦች ወጥተው ከልጆቹ ውስጥ የተወሰኑትን ሰባበሯቸው። ገንዘቤን መልሳችሁ ሻንጣዬን

ከበቅሎ ላይ አውርዳችሁ ስጥታችሁኝ በሰላም የማትሄዱ ከሆነ እኔ ደግሞ ንብ እጠራባችኋለሁ"፡፡ ከትከት ብለው አንጀታቸው ቁስል እስከሚል ሆዳቸውን ደግፈው ሳቁበት "እንደውም የምታመጣውን እናያለን" ብለው ቁጭ አሉ፡፡ ገርቦሌም የሚመጣውን ለማየት ወደ ኋላ ትንሽ መለስ ብሎ ጢሻው ውስጥ ካንዲት ዛፍ ላይ ወጣና "ጌታ ሆይ አንተ የጽድቅና የቅድስና አምላክ ነህ ንብ ላክልኝና ከነዚህ የሰይጣን መጠቀሚያ የፅድቅ ጠላት ሴቶች አድነኝ" ገና ከማለቱ ሦስት ንቦች በላዩ ላይ መዞር ጀመሩ፡፡ "ከናንተ ጋር ሺህ ጨምራችሁ ሄዳችሁ እነዚያን ሴቶች ንደፉ" በማለት ለሦስቱ ቀደምት ንቦች ያዝማችነት ሹመትና ትዕዛዝ ሰጣቸው፡፡

ስንት ክፍለጦር ንብ እንዳስከተቱ አይታወቅም ሦስቱ ንቦች ትዕዛዙን ተቀብለው ሄዱ፡፡ ወዲያውኑ ሴቶቹ ጮኹ፡፡ መሬት ላይ እየተንከባለሉ "ድረሱልን የሰው ያለህ" በማለት ኡኡታውን አቀለጡት፡፡ የደረሰላቸው ግን አልነበረም፡፡ በቅሎዎቹን እንዲነድፉ የተመደቡት ንቦች በትክክል ግዳጃቸውን ስለተወጡ ሁለቱም በቅሎዎች ፈርጥጠው ጭነታቸውን በየቦታው እያንጠባጠቡ ወንዝ ገብተው ሞቱ፡፡ ገርቦሌም ከዛፍ ወርዶ በቅሎዎቹሲፈረጥጡ ሻንጣውን ከጣሉበት አንስቶ በሌላ በኩል ወደ መንገድ ወጣ፡፡ የመኪና መንገድ ለመሥራት የሚጠርጉና የሚቀይሱ መሀንዲሶች አቆሙለትና ጭነው ጊዳ አደረሱት፡፡ ሴቶቹም ራሳቸውን እስከመሳት ደርሰው መንገደኛ አንስቶ ወደሰዎች ቤት ካስገቧቸው በኋላ ሦስት ቀን እዛው ተኝተው እንዳባበጡ ወደ ቤታቸው ከተወሰዱ በኋላ ያስበላቸው ሰው ይፈለግ ተብሎ አሰሳ ብጤም ተደርጎም ነበር፡፡





ሴቶቹ በንብ የተነደፉበት ቦታ ላይ በዚያኑ ዘመን ሁለት ጊዜ ኮንፈረንስ የተደረገ ሲሆን ቦታው የተመረጠበት ምክንያት የተንገዋረገገ ትልቅ የዝግባ ዛፍ ስለነበር በጥላው ሥር በየድንጋዩ ላይ ተቀምጦ መካፈል ስለሚያመች ነው፡፡ ያው የንብ መንጋ ይሁን ወይም ሌላ ለብዙ ጊዜ በዝግባው ውስጥ የሚኖር ንብ ነበር፡፡ ኮንፈረንስ ሲደረግ ግን ንቡ ቅዱሳንን አይተናኮልም ነበር፡፡ ንቡ ሀጢአት የሚጠላ መዝሙር የሚወድ ይሆን እንደሁ አልገባንም፡፡ በዚያን ጊዜ በዛፍ ጥላ ስር የተጀመረው ኮንፈረንስ በመጨረሻ በቦታው ለአንዴ ሙሉ ወንጌል አጥቢያ መመስረት ምክንያት ሆኗል፡፡

በነቢይ ገርቦሌ መግባት መውጣትና አገልግሎት ብዙ ተግዳሮቶች ቢገጥሙትም ሁልጊዜ ጠባቂው እግዚአብሔር ከርሱ ጋር ሆኖ እሱንም አገልግሎቱንም ይታደግ ነበር፡፡ አሙሩ አካባቢ ከወ/ዊ አረጋ ጋር ሲያገለግሉ የገጠማቸውን ወንጌላዊው እንዲህ ሲል ነግሮን ነበር፡፡ "ወደ አሙሩ ለኮንፈረንስ ሄደን ቦታው ላይ ስንደርስ ሁለት ረጃጅም ልብስ የለበሱና የተሸፋፈኑ ሴቶች ከነርሱም ጋር በተመሳሳይ የለበሱና የጠመጠሙ ሁለት ወንዶች ጉባኤው የተሰበሰበበትን ቦታ በርቀት በመሆን እየዞሩ እንደሆነ ገባን፡፡ ኃይለኛ የጠላት ሰልፍ እንዳለ ተረዳን፡፡ ነቢዩ በመንፈስ እንደተረዳው እነዚህ ሰዎች ጉኤውን ለማሰር የተላኩ ነበሩ፡፡ ስለሆነም እጆቹን ወደ ሰማይ አነሳና በአጭሩ የኤሊያስ አምላክ ወዴት ነህ አለ፡፡ ከየት መጣ ሳይባል አንድ እርቃኑን የሆነ እብድ እየሮጠ መጣ፤ ሁለቱን ሴቶችና አንዱን

ወንድ ለይቶ ፈንክቶ ደም በደም ካደረጋቸው በኋላ ጥሏቸው ሄደ ይህ የሆነው በአጋንንት ተልከው የመውጊያውን ብረት ስለተቃወሙ ነው፡፡ ብዙ ሰው ጻነ ብዙዎችም ከአጋንንት እስራት ተፈቱ ሕመምተኞችም ተፈወሱ፡፡ በአልጋ የመጣ ሰው ድኖ በእግሩ ወደ ቤቱ ገባ፡፡

እየዞሩ የሚያሟርቱ ብቻ አልነበረም ጠላትና ክፉ ሰዎች ያዘጋጁት፡፡ በስለት አገልጋዩንም የሚወጉ በጉባኤው ውስጥ አስቀምጠው ነበር፡፡ በስለት ለመውጋት የተዘጋጀው ሰው ተገዝቶ የመጣው ከርቀት ሲሆን ለረጅም ሰዓት ተቀምጦ የሚሆነውን ከማየት ውጪ ምንም ማድረግ አልቻለም፡፡ በመዝጊያው ፀሎት ላይ ነቢዩ በፀሎት ሲመሩን "አይናችሁን ከፍታችሁ ፀልዩ በዚህ ስለት ይዞ የተቀመጠ ሰው አለ፡፡ አንተ ሰው ከነአጃቢዎችህ ቢሮ መጥተህ አግኘኝ፡፡ እንዳሳብህ መውጋት አልቻልክም ዝም ብለህ ወደ ቤትህ ለመመለስ አስበሀል በማለት ጥሪ አስተላለፉ፡፡ ጨርሰን ወደ ቢሮ ስንገባ ከሁለት አጃቢዎቹ ጋር መጥቶ ንስሀ በመግባት ስለቱን አስረክቦ በምትኩ ጌታን ይዞ በገርቦሊ ደም ሳይሆን በክርስቶስ ደም ተነክሮ ወደቤቱ ገባ፡፡"

የአሙሩ አገልግሎቱ የሚያስታውሰን የመርጋ ጀርቦ ምስክርነትም አለ፡፡ "አሙሩ ወረቢሬ አካባቢ ጥንቆላ የበዛበት አገር ሲሆን ዘንዶ እየተቀለበ የሚመለከበትና ሌሎችም በርካታ ክፉ አምልኮዎች የነበሩበት አገር ነበር፡፡ አብረን በዚያ ስንጓዝ ስለዚሁ አጋንንታዊ አምልኮ ነገርኩት፡፡ "አሁን እንፀልያለን የሚሆነውን





ታያላችሁ" አለና ፀለይን፡፡ በማግስቱ እስከ አሙሩ ስሸኘው "በርቱና ፀልዩ እዚህ ቦታ የሚሆን ታላቅ ነገር አለ" ብሎን ተሰነባበትን፡፡ ለዘንዶው መስዋዕት የሚቀመጠው ሆሚ የሚባል ትልቅ ዛፍ ሥር ነው፡፡ በዚያ ብዙ እንስሳት ይታረዳሉ ቅቤው ማሩ ወተቱ ምድር ያፈራችው ሁሉ በኩራት በመስዋዕትነት ይቀርባል፡፡ መስዋዕቱ መቅረብ ባለበት ጊዜ ካልቀረበ ዘንዶው ዛፍ ላይ በመውጣት እየጮኸና እያፏጨ አካባቢውን ሁሉ ያውካል፡፡ ድምፁና ፉጨቱ ከአንድ ዘንዶ የሚወጣ አይመስልም በዱር የተሰማሩ እንስሳት ሳይቀሩ እየደነበሩ እስኪበታተኑ ይደርሳሉ ሰውም በያለበት የሚያስጨንቅ መንፈስ ከድምፁ ጋር አብሮ ወደ ውስጡ ስለሚገባ ምድሪቱ ትንቀጠቀጣለች፡፡

ያገሩ ሕዝብ የመስዋዕቱን ሥርዓት የሚያውቁት ሽማግሌዎችና ቃልቾች እየተመሩ "እዝጎ ማረን ይቅር በለን በማለት መስዋዕቱን በአጥፍ እናቀርባለን ሲሉ ዘንዶው ፀጥ ይላል፡፡ ብዙም መስዋዕት ይቀርባል ወርዶ ይቀማምሳል፡፡

እንግዲህ በዚህ አይነት ሰይጣን ምድሩን በግልፅ ሲገዛ ያየው ነቢይ በዚያ አገር ደካማም ቢሆኑ አጎቴና ሚስቱ ብቻ በጌታ ነበሩና እነሱ ቤት ባደረ ጊዜ ለእግዚአብሔር በመቅናት "ይህን ዛፍ የእግዚአብሔር እሳት ይብላ እነዚህም ሰዎች ከክፉው ነፃ ይውጡ በዚህም ቦታ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ትተከል" ብሎን ፀልዩላቸው ነበር ሲለያዩ፡፡ በዚያው ሰሞን እርጥቡ ግዙፍ ዛፍ ደረቀ፡፡ ቃልቻው ራሱ በጌታ ተማርከ ላሳታቸው ወንጌል እየሰበከ አገሩ ተለወጠና

በጌታ ተወርሶ እዚያው በታ ቤተክርስቲያን ተተከለች፡፡

አገልግሎትንና ተግዳሮትን ከነሳን የማናልፈው ነገር አለ ከደምቢ ዶሎ በታች በአሺ በኩል አልፎ ጎሬ ላይ ኮንፈረንስ ተዘጋጅቶ ነበር፡፡ አገልጋዩም ነብይ ገርበሌ ነበር፡፡ በፀሎት ያልተደገፈ ከመርሀ ግብር በመነሳት የተዘጋጀ ይመስል ሁሉም ነገር ደረቅና መንፈሳዊ ዳሰሳ ያልነበረበት ነበር፡፡ ነብዩ ተራው ደርሶ ወደመድረኩ ለስብከት ከመውጣቱ በፊት ጠላት የበረታበት ከጠላት ጋር ገና ትንንቅ የሚጠብቀው መሆኑ ገብቶታል ከዳሱ ውስጥ ወጥቶ ወደ ጓሮ ዞሮ ወዲያና ወዲህ ሲያማትር ከአንድ መጠለያ ውስጥ ጥግ ላይ አንዲት ልጅ ተደፍታ ስትፀልይ ነበርና ለዝግጅቱ መደበኛ ፀሎተኞች እንዳልተዘጋጁ ስለተረዳ "መሪዎች ለዚህ አገልግሎት በፀሎት አልተዘጋጃችሁም እንዴ? ይህች ልጅስ ብቻዋን ምን ትሠራለች የቢ ሸክም ብቻ ነው ይሄ ነገር" ብሎ ጠየቀ፡፡ "እኛ ልጅቷን ለፀሎት አልመደብናትም ከጀመረችው ግማሽ ሰዓት ያህል ይሆናታል ተነሺ እንዳንላት ፈራን" ሲሉ መለሱለት "ለምን ተነሺ ትሏታላችሁ" ተዋት እንጂ ብሎ ወደ አዳራሹ ገባ፡፡

የስብከት ሰዓት ደረሰና ወደ መድረኩ እንደ ወጣ ያቺ ብቻዋን ስትፀልይ የነበረች ወጣት እያለቀሰች ወደ ጆሮው ተጠግታ "ጉባኤው በፀሎት እንዲቆይ ንገራቸው" አለችው ከጉባኤ አስነስቶ ወደ ፀሎት የመራት ጌታ የገለጠላትን ተናገረች፡፡ "ጉባኤውን ለማወክ ከሩቅ ከጥልቁ ብዙ የክፋ መንፈስ ሠራዊት መጡ፡፡ በአየር ላይ ያለንበት አካባቢ ሲደርሱ ከነበረው የእግዚአብሔር ጥበቃ የተነሳ ያሰቡት





ሊሳካ አልቻለም፡፡ ስለዚህ ኃይል ጨምረን እንምጣ በማለት ተመልሰው ሄዱና በቁጥር በብዙ እጥፍ ሆነው ተመለሱ፡፡ ነገር ግን በትር የያዘ የእግዚአብሔር መልዓክ በትሩን ሲዘረጋው አየሩ በእሳት ነበልባል ስለተሞላ ተቃጠልን ብለው በአንድ መስመር የመጡት በብዙ አቅጣጫ ተበታትነው ጠፉ፡፡ ለሦስተኛ ጊዜ በአራቱም አቅጣጫ ሰማዩን ሞልተው መጡ፡፡ ያለንበት አካባቢ በአየሩ ላይ ሲደርሱ ከእግዚአብሔር ትዕዛዝ ወጥቶ በአየር ላይ አመድ ሆኑ አመዱም ምድር ላይ ረገፈ፡፡ ከዚህ በላይ ለምን እፀልያለሁ እግዚአብሔር ለዚህ ጉባኤ አስፈላጊውን ጦርነት ተዋግቷል" በማለት የቤተክርስቲያንን ለዚህ መንፈሳዊ ዝግጅት በፀሎት ያለመዘጋጀት ስንፍናና የእግዚአብሔርን ታማኝነት ጭምር ያስተዋለችውን ተናገረች፡፡ ያን ጊዜ ነቢዩ እግዚአብሔር ባደረገው ነገር ደንግጦ መድረኩ ላይ ቆም ብሎ አለቀሰ፡፡ ጉባኤውም በእግዚአብሔር ታማኝነትና ጥበቃ በመደነቅ በእንባ ተራጨ፡፡

ከዚያ በኋላ ጉባኤው ተፈታ አጋንንት ሎኸ መንፈስ ቅዱስ በኃይል ወረደ አዳራሹ ተናወጠ፡፡ ብዙ በሽተኞች በሚደንቅ ሁኔታ ተፈወሱ፡፡ ሌላ ቀርቶ ላንዳንድ መዘምራንና አገልጋዮች ጭምር ፈውስ ወጣ፡፡

ጉባኤው ከማንኛውም ክፉ መንፈስና ሕመም ፀዳ፡፡ ሁለት ወንጀለኞች ከእስር ቤት አምልጠው ለመሸሸግ ሲሄዱ ይህንን ስብሰባ ያዩና ለምን እንዳሉ ባይታወቅም ጎራ ይላሉ፡፡ ሰባኪው ያነበበው ክፍል "የመውጊያውን ብረት ብትቃወም ለአንተ

ይብስብሃል" (የሐዋርያት ሥራ 9:5) ሲሆን የስብከቱ ርዕስ "ይብስብሃል" የሚል ነበር፡፡ በዚሁ ርዕስ ላይ የእግዚአብሔርን ሀሳብ በመቃወም በራስ ላይ ስለሚደርሰው ጉዳት ከመፅሐፍ ቅዱስ ወደፊት ወደኋላም እያጣቀሰ የተሰበከውን ሁሉ ሰሙ፡፡ ነገር ግን የያዙት "ይብስብሀል" የሚለውን ብቻ ነው፡፡ "ከእስር ቤት ማምለጣችንን ይኼ የከተማ ሰው አውቋል፤ ሄዶ ሳይጠቁምብን በመንገድ እናስቀረዋለን በማለት ሲመለስ ሊያጠቁት ወንዝ ውስጥ ሸምቀው ጠበቁት፡፡

ነቢይ ገርቦሌ አገልግሎቱን ጨርሶ በሁለት ሸኚ ዲያቆናት በመታገዝ በተዘጋጀለት በቅሎ ላይ ሆኖ የመልስ ጉዞ ወደ አሸ. ተጀመረ፡፡ የተፈጥሮ ቡና ያለበትን ጫካ እያቋረጡ ቁልቁለቱን ወርደው ወንዝ ደረሱ፡፡ በቅሎዋ ወንዙን አልሻገር አለች፡፡ ብትባል ብትሰራ አሻፈረኝ ብላ ጭራሽ ኋልዮሽ ማፈግፈግ ጀመረች፡፡ ወርዶ ቢጎትቷትም እንኳ ሀሳቧን አለወጠችም፡፡ "ጌታ ሆይ ምን አጠፋሁ፡፡ እኔ እንደ በለዓም ለአመፅ አልተጓዝኩ አገለገልኩ እንጂ ምን አጠፋሁ" እያለ በመናገር ላይ ሳለ ሁለቱ ከእስር ቤት ጠፍተው "ይብስብሀል" በተባለው ስብከት ተነካን ያሉት ወንበዴዎች ሊበቀሉት ከጫካ ወጡ፡፡ ሁለቱም ዱላቸውን አሳምረው ይዘው ወደ መንገደኞቹ ተጠጉ፡፡ ነቢዩ ቢገሉትም እንኳ የነሱ ዱላ ከመሰንዘሩ በፊት የእሱን መሳሪያ ያም የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል ሰነዘረ፡፡ "ከናንተ ጋር ካለው ከኛ ጋር ያለው ይበልጣል" ሲል አንዱ ዱላውን መሬት ላይ ጣለና እንዳዞረው ሰው መሬቱን ፈልጎ ቁጭ አለ፡፡ ቀጥሎ የሆነውን ገርቦሌ እንዲህ ነገረን፡፡ "ወዲያው ለኛ የማይታዩ ለነሱ





የሚታዩ ከእነሱ አፍ እንደሰማነው ሁለት ወታደሮች መጥተው ያዟቸው፡፡ "አስያዛችሁን አይደል እነዚህን ሁለት ወታደሮች እዚህ ደብቃችሁ አስያዛችሁን አይደል እያሉ ከፊት ለፊታችን እየተነዳ እንደሚሄድ ሰው "እሺ" "እሺ" እያሉ ይሄዱ ጀመር፡፡ እነሱ ተደብቀው ቢጠብቁንም ታማኙ ጌታ ደግሞ ተደብቆ ጠበቃቸው፡፡ ለኛ የማይታዩን ጠባቂ ሠራዊት ለነሱ ታዩ፡፡ መታየትም ያለባቸው ለነሱ ነበር፤ ለኛ ማመናችን ማየታችን ነው፡፡

ይህ ከሆነ በኋላ በቅሎዋም በመታዘዝ ወንዙን ተሻገረች እነሱም ከፊት ለፊታችን እየተነዱ አሸ. ከተማ ገቡ፡፡ እኛም መጨሻውን ለማየት ከኋላ ስንከተል ነጂዎቹ መልዓክት ወደ ፖሊስ ጣቢያው ወስደው ከፖሊሶቹ ጋር አስተያዩዋቸው ፖሊሶቹም ነጂዎቹን ሰማያዊ ፖሊሶች ባያዩም ሁለቱ ተፈላጊ ወንጀለኞች ግን ሱተት ብለው በመምጣት እጅ የሰጡ መስሏቸው እያዋከቡ ወደ ውስጥ አስገብተው አሰሯቸው፡፡ ጴጥሮስ ከሩቅ በኢየሱስ ላይ የሚሆነውን ለማየት ይከተል እንደነበር እኛም የርቀት ክትትላችን አብቅቶ ሊሸኙኝ የመጡ ዲያቆናት እየተገረሙ ተሰነባብተን በቅሎዋን ይዘው ተመለሱ፡፡ እኔም ወደ ማርፍበት የወገኖች ቤት ገባሁ በሁኔታው ለብዙ ጊዜ ተገረምኩ በጌታም ጥበቃ ተደሰትኩ፡፡"

ከእግዚአብሔር ጥበቃ ሀሳብ ሳንርቅ ጥቂት እንጨምር፡፡ የሆነውን የሚያጫውተን የነብዩ ባለቤት የአዳነች እህት ባለቤት ነው፡፡ "አንድ ጊዜ እኔ ከኢሉባቦር ስመጣ እሱ ከአዲስ አበባ ወደ ቤቱ ወደጊዳ ሲመለስ ነቀምት ላይ ተገናኘን፡፡ የምናድርበትን አልጋ

ከያዝን በኋላ ራት ለመብላት ወጣን፡፡ እየሄድን ሳለ ድንገት ቆመ፡፡ "ምን ሆንክ አልኩት" እንመለስ ጌታ ተመለሱ ብሏል አለና ገብተን ጠማችንን አደርን፡፡ ጧት ከሰማነው ነገር እንፃር ጠም ማደራችን ተገቢ ነው፡፡ እዚያ የምንሄድበት አካባቢ ማታ ሰዎች ተጣልተው እርስ በርሳቸው መጋደላቸውንና ሌሎችም ጉዳዩ የማይመለከታቸው ሰዎች ጭምር መጎዳታቸውን ሰማን፡፡

በዚያው አመት ሌላ ጊዜ እዛው ነቀምት ተገናኘን፡፡ እሱ ወደአዲስ አበባ ይሄድ ስለነበር ቲኬት ቆርጦ አሳፈርኩትና ወደ አውቶቡሱ ገባ፡፡ ከመነሀሪያው ለመውጣት ሆር እንዳልኩ መሄድ ከጀመረው አውቶቡስ ወርዶ መጣ፡፡ ምነው ብየ ጠየቅኩት "ጌታ ውረድ ብሎኛል" አለ፡፡ ቲኬት የሚገኘው በብዙ ችግር ከመሆኑም በላይ መልሶ የሚገዛበት ገንዘብ ሳይኖረው ቲኬቱን ቀደደው፡፡ ሌላ ሰው ቢሆን በትርፍ ተለምኖ ይሸጠው ነበረ፡፡ ለሱ እግዚአብሔር ያልወደደለትን ጉዞ ቲኬት በመሸጥ ጉዳቱን ጭምር ለሌላ ማስተላለፍ አልፈለገም፡፡ ሊጓዝበት የነበረው አውቶብስ ነቀምትን ለቆ ወጣ፡፡ ስድሳ ኪሎ ሜትር ከተጓዘ በኋላ ስሬና ባኮ መሀል ገደል ገባ የሚል ወሬ ወደ ኋላ ተጉዞ አራት ሰዓት ላይ ነቀምት ደረሰ፡፡ ከስድሳ አምስቱ ተጓዦች አርባ ሦስቱ መሞታቸው በዜና ተነገረ፡፡

በነጋታው ወደ አዲስ አበባ ለመጓዝ ትኬት መግዣ ሳይኖረው ትናንት ውረድ ብሎ ያተረፈውን ጌታ ታምኖ ማለዳ ተነስቶ ወደ መነሀሪያው ገባ፡፡ እግዚአብሔር የሚያደርገውን እስከሚያደርግ ግቢው ውስጥ ወዲያና ወዲህ ሲል አንዲት ሴት በሰዎች መሀል እጇን እያወዛወዘች "ገርቢሌ! ገርቢሌ! ና! ወደዚህ" እያለች ስትጠራው





አየትና ወደሷ ሄደ፡፡ ቁና ቁና እየተነፈሰች ሰላምታ ከሰጠችው በኋላ
"የት ትሄድ ነው?"
"አዲስ አበባ"
"ትኬት ቆርጠሃል?"
"አልቆረጥኩም"
"አትቁረጥ እኔ አዲስ አበባ ልሄድ ከደምቢደሎ አዲስ አበባ ቀጥታ ቆርጬ ነበር አሁን ግን እዚህ የሚያቆይ ጉዳይ ገጠመኝ እንካ ቶሎ ግባ እዚህ አውቶብስ ውስጥ" በማለት ሞልቶ ሊወጣ ያለ አውቶብስ ውስጥ እየጣደፈች አስገባችው፡፡ እኔም ከእርሱ ጋር ለአንድ ተጨማሪ ቀን ስለቆየሁ ገንዘቤ አልቆ ስለነበር ወደመኪናው ውስጥ ሲገባ እኔስ ምን ላድርግ ብዬ ጠየኩት፡፡ "እዚሁ ቆመህ ጠብቅ እግዚአብሔር ይመጣልሀል" አለኝ፡፡ እሱ ሄደ እኔ መነኻሪያ ውስጥ ቆሜ ጠብቅ ያለኝን እግዚአብሔር መጠበቅ ጀመርኩ፡፡

እኔ እግዚአብሔርን ጠብቄ አላውቅም ልምዱም የለኝም የሚመጣበት ስለማይታወቅ ወዲህና ወዲያ እያማተርኩ ሳለ አንድ የማውቀው ያገሬ ሰው ከኢሉባቦር መጥቶ በሩቅ አየኝና ወደኔ መጣ ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ "እንኳን አገኘሁህ ምን ይውጠኝ ብዬ አገሩን የሚያውቅ ሰው ስፈልግ ነበር ለመንጃ ፈቃድ ነው የመጣሁት ዛሬ ከኔ ጋር ትውላለህ ጨርሰን ነገ አብረን እንሄዳለን በማለት በልመና መልክ ጠየቀኝና ጉዳዩን በዚያው ዕለት ጨረስን፡፡ "ከአሁን ጀምሮ የምትቆየው በኔ ወጪ ነው" አለ ጨምሮ ሆቴል ያዘልኝ ቲኬት ገዛልኝና መቶ ብር ሰጥቶኝ በማግስቱ ጉዞ ወደ ቤቱ ሆነ፡፡"

በአንዲት መንደር የገጠመው የአገልግሎት ላይ ተግዳሮት ሌላው ገጠመኝ ነው፡፡ በዚህች መንደር የሚገኙ አማኞች እንዲያገለግላቸው በተደጋጋሚ ቢጠይቁትም ሁሌም ለአገልግሎት ሲጠየቅ " ጌታ ሆይ ፈቃድህ ነው ወይ ብሄድ በቦታው ላይ በኔ የምትሰራው ሥራ አለወይ" በማለት ቢጠይቅም መልስ ስላላገኘ አልሄደላቸውም፡፡ ነገር ግን እነሱም ባልጠበቁት እሱም በረሳው ጊዜ የጌታ መንፈስ ወደዚያች ቤተክርስቲያን "ሂድ" አለው፡፡

ከጊዳ መምህር ጥላሁንን ይዞ ሄደ፡፡ የሚሰበሰቡበትን ቀንና ሰዓት ጠብቆ ወደ ስብሰባቸው ገባ፡፡ ከመሪዎቹ ጋር ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ "ጌታ ለናንተ የሚሆን መልዕክት የሰጠኝ አሁን ነው ጥላሁን ይመራል እኔ ደግሞ እሰብካለሁ" በማለት ያመጣውን ምክንያት ነገራቸው፡፡ ያመራር ኮሚቴ አባል ከሆኑት አንዱ ተነስቶ "እኛ ስንጠራህ አልመጣህም እኛ በፈለግን ጊዜ እንጂ አንተ በፈለክ ጊዜ አታገለግልም ህይወትህ የማይታወቅ ዝም ብለህ ትዞራለህ ለአገልግሎት ሳይሆን ለዝሙት ነው የምትዞረው እንደውም በኛ መድረክ ላይ አትቆምም" በማለት ወደ መድረክ እንዳይወጣ እየገፋ ወደ ኋላ መለሰው፡፡ ስብሰባው የሚደረግበት ቤት ባለቤትም ተነሳችና "ገርቦሌ አያገልግልም በፈለግነው ጊዜ ያልመጣ አገልጋይ ሕይወት አጠራጣሪ ነው በቅድስናው ላይ ችግር አለበት" ስትል በመጀመሪያው ሰውዬ ሀሳብ ላይ አከለችበት፡፡ ገርቦሌም የሁለቱንም ካደመጠ በኋላ "እናንተ አታውቁኝም እኔን የሚያውቀኝ ጌታ ነው አታገልግለን ካላችሁም እሺ ይቅርባችሁ" በማለት ወደ ኋላው እያፈገፈገ ለሰውዬው "እግዚአብሔር እንዲህ ይልሀል ዛሬ የቆምክበት





መድረክ ላይ ከዚህ በኋላ አትቆምም ይህ የመጨረሻህ ነው" በማለት የመጣለትን ነገረው፡፡ የገርቦሌ ባለቤት የአዳነች አባት በቦታው ስለነበሩና የአገልጋዩን ሕይወትና እግዚአብሔር በርሱ የሚናገረው ጠብ እንደማይል ያውቁ ስለነበረ "እባክህ አትርገማቸው ከረገምካቸው ሕዝቡ ሁሉ የተረገመ ይሆናል" ብለው ለመኑት "እኔ አልረገምኳቸውም መልካሙን ክፉ ክፉውን መልካም ለሚሉ ወዮላቸው ስለተባለ እርግማንን በራሳቸው ላይ ያመጡ እነሱ ናቸው" ብሎ ወጡና ወደመጡበትም ተመለሱ፡፡

መድረኩ ላይ ለመጨረሻ ጊዜ መቆሙ የተነገረለት ሰው ወዲያው ሁለመናው ሽባ ሆነ፡፡ ከሳምንት በኋላ ሞተ፡፡ በሰውየው ላይ ጨምራ የተናገረችውም ሴት መተዳደሪያዋ የነበሩ በርካታ በጎችና ፍየሎች አብደው ደም እየሸኑ በየሜካ ተበታትነው ሞቱ፡፡

# መለኮታዊ ጣልቃ ገብነት

"ኤሊያስ እንደ እኛ የሆነ ሰው ነበረ ዝናብም እንዳይዘንብ አጥብቆ ፀለየ በምድርም ላይ ሦስት ዓመት ከስድስት ወር አልዘነበም ሁለተኛም ፀለየ ሰማዩም ዝናብን ሰጠ ምድራቱም ፍሬዋን አበቀለች" /ያዕቆብ 5፡17-18/

እግዚአብሔር ቅርብ ነው፡፡ በተለይም በዕውነት ለሚጠሩት ቅርብ ነው፡፡ እርሱ ቅርብ የሚሆነው ለእርሱ ቅርብ ለሆኑት ነው፡፡ የቀረቡት የክብሩ መገለጫና አገልጋዮቹ ይሆናሉ፡፡ ሙሴ ለእግዚአብሔር ቅርብ ስለነበር በአመራሩ ዘመን በግብፅ ላይ አሥር መቅሰፍቶች ወርደዋል፡፡ ባህር ተከፍሏል ከአለት ውኃ ፈልቋል ኃያላን ነገስታት ድል ተመተዋል፡፡ ወደ እግዚአብሔር በመቅረብ ምሳሌ ከሚሆኑን አንዱ ነብዩ ገርበሊ ነው፡፡ በየሁኔታዎች ውስጥ እግዚአብሔር ጣልቃ ገብቶ እንዲከናውንና ለቀረነውም ወደ እግዚአብሔር መጠጋት ያለገደብ መጠቀሚያ ዕቃው ሊያደርገን እንደሚችል ያስተምረናል፡፡ "ብታምኑ እኔ ካደረኩት በላይ ታደርጋላችሁ" እንደተባለው ማለት ነው፡፡

በ2001 ዓ.ም መጨረሻ ክረምት እንደገባ ነብይ ገርበሊና አዲ ዲላ ዩኒቨርሲቲ ተምሮ የሚመረቀውን ወንድሚን በደስታው ላይ በመገኘትና ለማስመረቅ ወደዚያው ተጉዘው ነበር፡፡ ከአዲስ አበባ ተነስተው ወደ ስምጥ ሸለቆ እንደታከ ጫማ እያዘቀዘቀ የሚሄደውን መንገድ ይዘው ሞጆ ሲደርሱ ወደ ደቡብ ዘጠና ዲግሪ ዞረው ረጅሙን መንገድ ተያያዙት፡፡ በመቂ በዝዋይ በሻሸመኔ በአዋሳ





ገስግሰው የስምጥ ሸለቆውን የግራ ከንፈር ይዘው በአቦስቶ ቀና ብለው ከፍ ወዳለው መሬት ደረሱ፡፡ ከቆላማው መሬት ወደ ወይናደጋማው ቢወጡና ጊዜውም የክረምት ቢሆንም አንኳ አገሩ ሀሩር ሆኗል፡፡ በዲላና በአካባቢው የነበረው አረንጓዴነት በዚያን ጊዜ አልነበረም፡፡

ወቅቱ የበቆሎ ሰብል ማሳውን ከመሸፈን አልፎ አንጓ ማውጣት የሚጀምርበት ቢሆንም እንኳ ለረጅም ወራት አልዘነበም፡፡ የክረምቱም ዝናብ እንኳን ሊዘንብ ምልክቱም የለም፡፡ ለምልክት እንኳ በሰማይ ደመና አይታይም፡፡ ዝናቡን ተስፋ አድርገው ሳይሆን ወሩን ቆጥረው አልፎ አልፎ ዘርተው የነበሩ ገበሬዎች ቡቃያቸው ጠውልጎና ደርቆ አንገቱ ወደ መሬት ተቆልምሟል፡፡

ያ በቡና በእንሰትና በተለያዩ አዝዕርት ደምቆና ተውቦ ተመልካችን ያማልል የነበረ ዲላና አካባቢው ከው ብሎ ደርቆ የልምላሜ ካባው ተገፎ የዛፎች ቅጠል ረግፎ ምድራቱ ተራቁታለች፡፡ ዲላ ዩኒቨርሲቲ አስመራቂ ወላጅና እንግዶቿን እንዲህ ራቁቷን ሆና ነው የተቀበለቻቸው፡፡ ከወቅቶች ታማኝነት ጋር የተቆራኘ ሕይወት ላለን ለእኛ ለኢትዮጵያውያን የክረምት መዘግየት ወይም መራዘም የአብዛኞቻችንን ትኩረት መሳቡ የተለመደ ነውና በክረምት ወቅት ጠራራ ፀሐይ የገጠማቸው የዲላ እንግዶች ስለዚያ ሀገር መደንገጣቸው አይቀርም፡፡ ነገር ግን ከእንግዶች መሀል ለችግሩ መፍትሄ ያሰቡ ሁለት እንግዶች ነበሩ፡፡ ሊሊቱን በያዙት ሆቴል መተኛት አልቻሉም፡፡ ከሙቀቱ የተነሳ ቀን ያዩት ድርቀት የሊሊት ረባሽ ሙቀት ጋር ሲደመር መፍትሔ ሊፈለግ ይገባል ብለው አመኑ

ደግሞም ተስማሙ፡፡ አዲና ገርቦሌ ሌሊቱን አጭር ፀሎት ፀለዩ ቅርብ ወደ ሆነው ጌታ "እባክህ ነገ የምርቃቱ ስነስርዓት ካበቃ በኋላ ዝናብ ስጥ፡፡"

የምርቃት መርሃ ግብሩ ተጠናቆ ሰው ወደ ማረፊያው ከተመለሰ በኋላ የሰማይ መስኮቶች ተከፈቱ ዝናብም ዘነበ፡፡ ተሰነጣጥቃና አፏን ከፍታ የነበረችው ምድር ጠማቾ ረካች አፏንም ዘጋች ክረምቱም ቀጠለ፡፡

"ሳሙኤልም አደገ እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር ነበረ ከቃሉም አንዳች በምድር ላይ አይወድቅም ነበረ" /1ሳሙኤል 3:19/

የእግዚአብሔር ሥራ ከዚህ አለም ገዢ ከሰይጣንና ከመላእክቱ ጋር የፍልሚያ ሥራ ነው፡፡ ወንጌልም በደረሰበት ሁሉ ክፋውን እያስለቀቀ ሜካውን እየመነጠረ ይወርሳል እንጂ ባዶ ሥፍራ አግኝቶ አያውቅም፡፡ "በጨለማ የኖረ ሕዝብ ብርሃን አየ" የተባለው ስለዚህ ነው፡፡ ሰዎች በብርሃን ካልሆኑ በጨለማ ናቸው፡፡ ብርሃን እንዲሆን ጨለማ መወገድ አለበት፡፡ በጨለማ ብርሃን ይብራ" እንደተባለ "እግዚአብሔርም ብርሃን ይሁን አለ ብርሃንም ሆነ" /ዘፍጥረት 1:3/ የወንጌል አገልግሎት የተገኘውን የብርሃን ሕይወት መንከባከብና በጨለማ ብርሃን ይሁን የማለት ተግባር ነው፡፡ ይህ ደግሞ ከዚህ አለም ገዢ ጋር ግጭት ነው መንግስት አፍርሶ መንግስት የመመስረት ነገር ስለሆነ፡፡ ቤተክርስቲያን የጠላትን መንግስት በማፍረስ የእግዚአብሔርን መንግስት ታንፃለች፡፡

እንደማንኛውም አገልጋይ ነቢዩም በአገልግሎቱ የጠላትን





መንግስት ከመናድ የሚነሱ ተግዳሮት በየጊዜው የነበሩ ቢሆንም ቤተክርስቲያንን የገሀነም ደጆች አይችሏትም ተብሏልና በአስደናቂ ሁኔታ የእግዚአብሔር ክንድ እየተገለጠ ያደረገውን አልፎ አልፎ ለእግዚአብሔር ክብር እንዲሆን ቀጥለን እንጠቅሰዋለን፡፡

"በ1985 ዓ.ም በምዕራብ ወለጋ ዋንኪ ሁለት ጊዜ ያገለገለ ሲሆን በመጀመሪያው ላይ በዚያ ሀገር አጋንንታዊ አምልኮ ይፈፀምበት የነበረ ታላቅ ዛፍ ነበርና ምድሪቱ ከእግዚአብሔር እንድትርቅና እንድትጎሳቆል ያደረገው ይህ ነው" በማለት ከእንግዲህ የማይመለከ መሆኑንና ሕዝቡም ወደ እውነተኛው አምላክ ዘወር እንደሚል ተናገረ፡፡ ብዙም ሳይቆይ ዛፉ ደርቆ ወደቀ የሕዝቡም ልብ ለወንጌል ተከፈተ፡፡ በጨለማ ብርሃን በርቶ በቦታው ትልቅ ቤተክርስቲያን ተተከለች፡፡

ድጋሚ በዚያው በዋንኪ ባገለገለበት ጊዜ የነበረው የቀበሌ ሊቀመንበር ቤተክርስቲያንን የማይወድ አሳዳጅ ነበርና ጉባኤው ለፀሎት በተሰበሰበበት ቤት ታጣቂዎችን ይዞ ገርቦሌን ለመውሰድ መጣ፡፡ ፊት ለፊት የነበረውን ገርቦሌን መያዝ አልቻለም፡፡ ሌሎችን ወስዶ አሰራቸው፡፡ የሰውየውን ቤት ለገርቦሌ ማንም አላሳየውም ነገር ግን እጁን ዘረጋና የወንጌልን እንቅፋት ገሰፀ፡፡ አገልግሎቱን ጨርሶ ከከተማው ሲለቅ የሊቀመንበሩ ልጆች በቤታቸው ላይ እሳት ለኩሰው ቤቱ ተቃጠለ፡፡ አንድ በረት ከብቶቹ መብረቅ ወድቆባቸው አለቁ፡፡ አንድ ልጁ የአእምሮ በሽተኛ ሆነ፡፡ ሊቀመንበሩም የተጣላው ከእግዚአብሔር ጋር እንደሆነ ገብቶት ስልጣኑን ለቀቀ፡፡ ለተካው

ግለሰብም ከማስጠንቀቂያ ጋር ቢሮውን አስረከበው፡፡ "እነዚህን ጴንጤዎች እንኳንስ ሄዳችሁ መተናኮል ይቅርና ቢመጡ እንኳ እንዳትነኳቸው" በማለት፡፡ በመጨረሻም እግዚአብሔር ረድቶት ንስሀ ገብቶ ጌታን ማምለክ ጀመረ ይህንንም ያደረገው ለቤተክርስቲያን ደብዳቤ በመፃፍና ይቅርታ በመጠየቅ ነው፡፡" ወንጌላዊ አምሩ ሁንዴሣ ከዋንኪ፡፡

"በጥቅምት ወር 1987 ዓ.ም ጉሊሶ ላይ በተዘጋጀው ኮንፍረንስ አስደናቂ የእግዚአብሔር ጉብኝት የሆነ ሲሆን ከሁሉ በላይ አማኙንና ከተማውን ያስደነቀው የኤች አይ ቪ ታማሚ የነበረችው ደሴ ማሞ የተባለች ሴት አህልና ውኃ የማትቀምስ በሰዎች ርዳታ በቃሬዛ መጥታ ከጉባኤው ርቃ ተኝታ ሳለ ነቢዩ ወደርሷ በመሄድ "በጌታ በኢየሱስ ስም ተነሺና የተኛሽበትን ተሸከመሽ ሂጂ" ሲላት ወዲያው ተፈውሳ ተነሳች ፍፁም ጤነኛ ሆና የተኛችበትን ጠቅልላ በመድረኩም ላይ ወጥታ እግዚአብሔር እንደነካት መሰከረች፡፡

ወደመጣችበት ቤቷ ሀያ አምስት ደቂቃ ያህል ተጉዛ ገባች፡፡ ያችም ሴት ከዚያ በኋላ የሞቷን ደቂቃ ከመጠባበቅ ወጥታ በሰላምና በጤና ኖረች፡፡ በዚያው ኮንፈረንስ ነብዩ አገልግሎ ወደ ማረፊያው ሲመለስ አንድ የወንጌል ተቃዋሚ በእርሱ ለማሾፍ ፈልጎ ድምፁን ለውጦ የሴት ድምፅ በማስመሰል "ገርባሴ" ብሎ ሁለት ጊዜ በቀጭን ድምፅ ተጣራ፡፡ ገርባሴም እውነት የተጠራ መስሎት ዞር ቢል የጠራው ወንድና ለዚያውም ለማሾፍ ነው፡፡ የሰውየው ድምፅ እንደዛው የሴት ድምፅ ሆኖ ሲቀር ሚስቱ ከወር በኋላ ስትሞት





እሱም አብዶ ራቁቱን በዚያ ከተማ ለብዙ ጊዜ ኖረ፡፡" ወ/ዊ ጅሬኛ አያና ከጉሊሶ

"በታህሳስ ወር በ1985 ዓ.ም እኔና አንድ ባልደረባዬ ኪረሙ እያገለገልን እያለ ሰይጣንና ክፉ ሰዎች ያዘጋጁልን ወጥመድ ስለነበር ከፍተኛ ችግር ውስጥ ገብተን ሳለ ነብይ ገርባሴን ጌታ ላከልን፡፡ ከጊዳ ተነስቶ በቀጥታ ወዳለንበት ቦታ በጌታ ምሪት በመምጣት ለኛ የተዘጋጀውን ክፉ ዕዋ እሱ ተቀብሎ እኛን አተረፈን፡፡ እንዲሁም ሌላ ጊዜ ከሐረቶ ተነስተን ረግረጋማውን ቦታና ውሃማውን አገር በእግርና በጀልባ ተጉዘን ዓባይ ጮመን ደረስን በዚህ የአገልግሎት ወቅት የገረመኝ ነገር ቢኖር አጋንንት የነበረባቸው የሚጮኹ ሰዎችን "አሁን ጊዜው የእግዚአብሔርን ቃል የምንሰማበት ነው እስከዚያው እዚያ ዝግባ ስር ተሰብሰባችሁ ቆዩ ለናንተ የተያዘው ጊዜ ሲደርስ እንገናኛለን" በማለት ሲናገራቸው በክፉ መንፈስ የተያዙ በሙሉ ማንም እንደተለመደው ሳይጎትታቸውና ሳይሸከማቸው ቀጥ ብለው በመሄድ በዛፍ ሥር ተሰበሰቡ፡፡ ሌላውን አገልግሎት ሲያበቃ አሁን ሰዓታችሁ ደርሷል ውጡ ሲባሉ እየጮሁ ወጡ፡፡" ፓ/ር ንጉሣ ደሳለኝ፡፡

"ኪረሙ ላይ ስናገለግል ግማሽ ቀን ያህል ምንም የሚጥም ነገር አልታየም፡፡ ሰማዩ ተዘጋ የሚቋቋም የጠላት ጉልበትና ተግዳሮት እንዳለ ተረዳን፡፡ ነብይ ገርባሴ ከመድረኩ በስተጀርባ ባለው የበሀርዛፍ ጫካ ውስጥ ተደብቆ የሚሟርት ሰው እንዳለ ተረድቷል ይህ ሰው እንዲመለስ በተደጋጋሚ ፀለየ፡፡ ለህዝቡ ሲናገር

የሥጋም የሃይማኖትም ግጭት ተነስቶ ነገሩ መንፈሳዊ ድል ያሳጣናል በማለት ዝም አለና የክፉን ሥራ በፀሎት ማፍረስ ጀመረ፡፡ ሁኔታው ሁሉ ተለወጠ፡፡ በመጨረሻም "ይህንን ጉባኤ ለመቋቋም ጠላት የተጠቀመበትን ሰው ሬሳ በቅርብ ቀን ከዛፍ ሥር ያነሳሉ" በማለት በጥቅሉ ተናገረ፡፡ በዚያው ሰሞን ያ ሰው ሆዱ ተነፍቶ ዛፍ ሥር ሞቶ ተገኘ፡፡ ለጨለማው አለም እውቅ ሠራተኛ ነበር በዚህ ዘመቻ ግን እንደወጣ ቀረ በዛፍ ሥር ሲሟርት በዛፍ ሥር ወድቆ ቀረ፡፡ ማድረግ የነበረበት ሆዱ መነፋት ሲጀምር ፈጥኖ ንስሀ መግባትና የመሲሁን ጌትነት መቀበል ነበረ መሸነፉን እያወቀ በጨለማ ኖሮ ወደዘላለም ጨለማ እየተ እያየ ሄደ፡፡





## የቡራዩ ቆይታ

የአገልግሎቱን ስፋት እየተከተለ የቤተሰቡም መኖሪያ በየጊዜው ከቦታ ወደ ቦታ ተዘዋውሯል፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ባገለገለበት ዘመን ረጃጅምና ታላላቅ የወንጌል ጉዞዎችን አድርጓል፡፡ የጻፉትን ለጌታ አደራ እየሰጠ ኋላም እያደራጀ፡፡ አብያተክርስቲያናትን ካደራጀ በኋላ ሮም በነበረባቸው አመታት በመልዕክቶቹ አብያተክርስቲያናትን ያንፅ ነበር፡፡ የነብይ ገርባሲም አገልግሎት እንዲሁ ከረጅም ጉዞዎች እየቀነሰ እየቀነሰ መጥቶ በተለይ ቡራዩ ከገባበት ከ2002 ዓ.ም ወዲህ የስልክ አገልግሎት በመስጠት በመላው አለም ያሉ ቅዱሳንን ይመክራቸዋል ይፀልይላቸዋል፡፡ ከአሜሪካ፣ ከካናዳ፣ ከአውሮፓ፣ ከአውስትራሊያ በመደወል ሸክማቸውን ያጋሩታል፡፡ ቀንም ሌሊትም ስልኩ አያቋርጥም ሞባይሉ ቻርጅ ላይ ካልሆነ በስተቀር፡፡

"አንድ ቀን ከጧት ጀምሬ እስከ ማታ በስልክ በማገልገሌ ደክመኝ ለማረፍ ብዬ ስልኩን ዘጋሁና ጋደም አልኩ፡፡ ሸለብ እንዳደረገኝ አንድ ሰው መጥቶ "ተነስ ተነስ" በማለት ቀሰቀሰኝ ቀና ብዬ ቤቱ ውስጥ ሰው ብፈልግ ማንም አልነበረም በህልም ሳይሆን በትክክል ትከሻዬን እየነቀነቀ ስለቀሰቀሰኝ ቤተሰብ መስሎኝ ነበር፡፡ ነገር ግን "ተነስ ሰው ይጠብቅሀል" ብሎኝ የቀሰቀሰኝ እጅ ተሰበሰበ፡፡ ተነስቼ ቁጭ በማለት የሚፈልገኝን ሰው መጠበቅ ጀመርኩ፡፡ ትዝ ሲለኝ እየሰጠሁ ያለሁት የስልክ አገልግሎት በመሆኑ ስልኩን ከፈትኩ ሁለት ደቂቃ ሳይቆይ ተደወለ፡፡ አሜሪካን ልጃቸው በጠና የታመመባቸው ወላጆች ነበሩ የደወሉት፡፡ "ልጃችን ታሞ አሁን ወደ

ሆስፒታል ልንወስደው እየተጣደፍን ነው የደወልንልህ እባክህ እግዚአብሔር ጣልቃ እንዲገባ ጸልይልን" አሉኝና እነሱም ባሉበት በእምነት በልጁ ላይ እጃቸውን ጭነው ከኔ ጋር በስልክ ጥቂት ጸለይን፡፡ ልጁ ወዲያው አይኑን ገለጠ ሕመሙ በረደ መነጋገር ጀመረ፡፡ ሆስፒታሉም ቀረ፡፡ እኔም ጌታ ሆይ ይቅር በለኝ እንዲህ የተጨነቁ ሰዎች እያሉ ነው የተኛሁት በማለት ንስሀ ገባሁ፡፡ ጌታም "እኔ መቼ አረፍኩና ነው አንተ የምታርፈው እኔ ካንተ ጋር እሆናለሁ ሲደክምህ ኃይል እጨምርልሀለሁ ባንተ ብዙዎች ከጭንቀታቸው ይላቀቃሉ" አለኝ፡፡ ከዚያ ወዲያ ሞባይል ቻርጅ ለማድረግ ወይም የጸሎት ጊዜ ሲኖረኝ እንጂ በድካም ምክንያት ለማረፍ ብዬ ስልክ አልዘጋም፡፡ ብዘጋም ከጌታ የምፈለግበት ነገር ካለ ውስጤን እያደመጥኩ ነው፡፡

በነዚህ የሁለት አመት የስልክ አገልግሎት የብዙ ሰዎችን እንቆቅልሽ ጌታ ፈቷል፡፡ ወንድም ሆነ ሴት የውስጣቸውን ሳይደብቁ ልክ ለእግዚአብሔር እንደሚናገሩ ሚስጥራቸውን ይነግሩኛል፡፡ እኔም በታማኝነት ሚስጥራቸውን እይዛለሁ፡፡ ጌታም በሚደንቅ ሁኔታ ይደርስላቸዋል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ በስልክ ከሚቀርቡልኝ የጸሎት ጥያቄዎች የጤና ችግር የትዳር ችግርና የመንፈሳዊ ሕይወት ችግሮች ናቸው፡፡ የጤና ችግርንና የህመምን በተመለከተ አድገዋል ሀኪም አላቸው ከሚባሉት ምዕራባዊ ሀገሮች የሚመጣ ጥያቄ ይበልጣል፡፡ እንደ ሀኪሙ መብዛት እንደ መሳሪያው መራቀቅና እንደመድሀኒቱ ጥራት አይምሰላችሁ በሽታው አይገኝም፡፡ እንዲህ አይነቶቹ ሰዎች እግዚአብሔር የሚፈልጋቸውና አልያዝ አልጨበጥ





ያሉ ሊሆኑ ይችላሉ በአብዛኛው ጉዳዩ

"አሁንም ከእርሱ ጋር ተስማማ ሰላምም ይኑርህ በዚያም በጎነትን ታገኛለህ

ከአፍም ህጉን ተቀበል

በልብህም ቃሉን አኑር

ሁሉን ወደ ሚችል አምላክ ብትመለስ ብትዋረድና

ኃጢአትን ከድንኳንህ ብታርቅ

የወርቅን ዕቃ በአፈር ውስጥ

የኦፊርንም ወርቅ በጅረት ድንጋይ መካከል ብትጥል

ሁሉን የሚችል አምላክ ወርቅና የሚብለጨለጭ ብር ይሆንልሀል

የዚያን ጊዜ ሁሉን በሚችል አምላክ ደስ ይልሃል

ፊትህንም ወደ እግዚአብሔር ታነሳለህ

ወደ እርሱም ትጸልያለህ እርሱም ይሰማሀል

ስዕለትህንም ትሰጣለህ

ነገርንም ትመክራለህ እርሱም ይሳካልሀል

ብርሀንም በመንገድህ ላይ ይበራል"

(ኢዮብ 22፡22-28)

የትዳርን ጉዳይ በተመለከተ ያገቡም ያላገቡም ጥያቄ አላቸው፡፡ በባልና ሚስት መሀል በብዛት የሚስተዋለው መከዳዳት "ጥሎኝ ወጣ" "ጥላኝ ሄደች" ጭቅጭቅ አለመግባባትና ጠብ የተለመዱ ናቸው፡፡ ብዙውን ጊዜ እኔ ተጎጂውን ወገን ነውና የማገኘው ባለበት ሁኔታ ውስጥ ወደ እግዚአብሔር እንዲቀርብ

እመክራለሁ። ምክንያቱም ሁለት ነው። የመጀመሪያው እግዚአብሔር ባልቃ ገብቶ ቤታቸውን ሊያስተካክል ስለሚችል ፤ ሁለተኛው ከትዳር የሚያልፍ ዘላለማዊው ነገር እንዳይጎዳ። የሳያል አጎት ስለጠፉት አህዮች ማሰብ ትቶ ሰላንተ እየተጨነቀ ነው እንደተባለ አህያው ወይም አህያዋ ብትጠፋ እንኳ አንድ አይንህ ጠፍቶ መንግስተሰማያት ብትገባ ይሻልሀል እንደተባለው ለመንፈሳዊው ሕይወት ጥበቃ ለማድረግ ነው።

በትዳር አብረው የቆዩ ሰዎች ቀስ በቀስ ብዙ የህይወት ውጣ ውረድ ባሳለፉ መጠን ፍቅራቸው መጨመር ሲገባው ሆድና ጀርባ እየሆኑ ወደ መለያየት የሚደርሱበት ሁኔታዎችም ይገጥማሉ። በድህነት ጀምረው እግዚአብሔር ባርኳቸው ሀብት ካገኙ በኋላ መናናቅና "አይመጥነኝም" "አትመጥኝም" የማለት አለቦታው የሆነ ምርጫ ውስጥ የሚገቡም አሉ። ልጅ ማጣት ሌላው የትዳር ችግር ነው። ባልና ሚስት ምንም ሆነ ምንም የገቡትን ቃል ኪዳን መርሳት የለባቸውም የብዙ ክርስቲያን ባልና ሚስት ችግር ቃል ኪዳንን መርሳት ነው። "በመከራና በችግር ጊዜ በማጣት ጊዜ" ተብለው የተገቡ ቃል ኪዳኖች ገንዘብ ሲታጣ ብቻ የሚሰሩ ሳይሆኑ ልጅም ሲታጣ ሊታሰቡ ይገባል። ቃልኪዳን ቢወለድም ባይወለድም ለድርድር መቅረብ የለበትም። "መካኑ አንተ ነህ አንቺ ነሽ" በመባባል ለማምለጥ የቃል ኪዳንን ማሰሪያ ከመገዝገዝ ይልቅ ወደ እግዚአብሔር ተስማምተው ቢቀርቡ ቁጥር ስፍር የሌላቸው መካን ባለትዳሮች ተጸልዩላቸው ሲወልዱ አይተናል።





ያላገቡትም ችግር ቀላል አይደለም። የመጀመሪያው ችግር የምርጫ ብዥታ ነው "ማንን ላግባ" ተወዳዳሪዎቹ ሊበዙ ይችላሉ። በዚያን ጊዜ ሙሉ ለሙሉ በጌታ ላይ በመደገፍ ምሪት መጠየቅ ነው። ምኞትን ተከትሎ መወሰን በአይን እምሮት ላይ መንጠልጠል ውጫዊ ነገሮች ላይ ለምሳሌ ሀብት፣ ውበት ላይ በመመርኮዝ መወሰን ዘለቄታ ያለው ትዳር አይመሰርትም ውጤቱ ፀፀትና ኪሳራ ከመሆኑም በላይ ርቆ የማይሄድ ትዳር ይሆናል።

"ልባም ሴት ማን ሊያገኛት ይችላል" /ምሳሌ 31፥10/

እግዚአብሔር ሊያገኝልህ የታመነ ነውና ፊቱን ፈልግ። ለትዳር ጓደኛ የሚሆንን ሰው እግዚአብሔር ከሰጠም በኋላ ስጦታውን ባለመቀበል ወይም በአግባቡ ባለመያዝ ጋብቻ የሚዘላቸው በተለይ በርካታ እህቶች ገጥመውኛል። አይናቸውን ጨፍነው ጌታን ከመጠበቅ ይልቅ አይናቸውን ከፍተው የሚፈልጉትን ባል ያስሳሉ። በሌላ በኩል "ለአንቺ የሚሆነው ይኼ ነው ቢሏቸውም በራሳቸው የሞቀ አደን ላይ ስለሆኑ አይሰሙም። ያኛውም ከእግዚአብሔር አይደለምና ሳያገኙት እግዚአብሔር ለነሱ ያዘጋጀውም ጊዜው በማለፉ የትዳር ማዕድ መሰባቸው ተነስቶ እድሜያቸው ሲያቆለቁል ይባንናሉ። ከሁለት የወደቀ ሆነው የባል ያለህ አገሩን በሚፈልጉት ያስሳሉ። ያላገባችሁ እግዚአብሔር ይምረጥላችሁ እሱ አይሳሳትም።

ለናንተ የማስባት አሳብ መልካም ተስፋና ፍጻሜ ያላት ናት ተብሏልና። ጌታ ነፍሳችንን ያድናል ብለን ካመነው ሌላውንም ሁሉ ሊያደርግ የታመነ ነው።

የእረኝነት ወቅት የሚወልደውም ችግር አለ፡፡ ሁለቱ ተጋቢዎች በትክክል እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ተገናኝተው ሳለ ረጅም የእረኝነት ጊዜ በሚፈጥረው መጠጋገብና መሰላቸት ወይም በሌሎች ጣልቃ ገብነት ነገሩ ለፍሬ ሳይበቃ ሊጨናገፍ ይችላል፡፡ ይህም የህይወት ዘመን ኪሳራና ጠባሳን ትቶ ያልፋል፡፡

ሌላው በሰልክ አገልግሎት ውስጥ በብዛት የሚገጥመኝ የመንፈሳዊ ሕይወት ድካም ነው፡፡ ይህም ጊዜ ከማጣትና ከእግዚአብሔር ቃልና መንፈሳዊ ተሳትፎዎች በመራቅ የሚከተል መንፈሳዊ ዝለትና የህይወት መላሸቅ ነው፡፡ በተለይ ከውጭ አገር በብዛት ስለመንፈሳዊ ሕይወት ድካማቸው ይደውሉልኛል፡፡

የትም እንሁን የት ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ኅብረት ሥፍራውን መልቀቅ የለበትም፡፡ ለጸሎት ለቃሉና ለቅዱሳን ህብረት ጊዜ ከሌለን በውስጣችን የነበረው ግለት እየቀዘቀዘ ሄዶ የሚጠፋበት ቀን ላይ እንደርሳለን፡፡ ሳይጠፋ እሳቱን መቆስቆስ አለብን፡፡

"እሳት እንደሚያቀጣጥል ሰው እጆቼን በመጫኔ በአንተ ያለውን የእግዚአብሔርን ስጦታ እንድታነሳሳ አሳስባለሁ" (2ኛ ጢሞቴዎስ 1፡6)

ይህ ለሁሉም አማኝ ይሠራል፡፡ በውስጣችን ያለው መንፈስ ሁልጊዜ መነሳሳት መቀጣጠልና እየበዛ መሄድ አለበት፡፡ መንፈሳዊ ህይወት ያለመንፈስ መነሳሳትና መቀጣጠል ባዶና ሥርዓታዊ ሃይማኖት ብቻ ሆኖ ይቀራል፡፡ በመንፈስ እንድንፀልይ በመንፈስ እንድንዘምር ቃሉን በመንፈስ እንድንረዳ የእግዚአብሔር ቃል





ይመክረናል፡፡ ጌታም ሕይወት እንዲሆንላችሁ እንዲበዛላችሁም መጣሁ ማለቱ የተገኘው የእምነት ሕይወት ዘወትር እየጨመረ እየበዛ የሚሄድ መሆኑን ያሳያል፡፡ ሕይወት በመንፈስ እሳት እየተቀጣጠለ ካልሄደ እንደሚጠፋ እንለወጣለን፡፡ እግዚአብሔር የሚጠብቅብን እኮ የመንግስቱ ወራሾች ብቻ መሆንን አይደለም እየተለወጡ የልጁን መልክ መያዝ ጭምር ነው እንጂ፡፡ ከዛም ባለፈ፡፡

"ነገር ግን እላለሁ በመንፈስ ተመላለሱ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈፅሙ፡፡ ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና እነዚህ እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ፡፡ (ገላትያ 5፡16-17)

በመንፈስ ካልበረታን ሥጋ በክርስትናችን ላይ አዛዡ እሱ ይሆናል፡፡ በሥጋ ቁጥጥር ሥር ያለ መንፈሳዊ ሕይወት ከክፉ ፍሬ በስተቀር አያፈራም፡፡ ሕይወት በፍሬ ስለሚገለጥ መንፈሳዊ ፍሬ ለማፍራት መንፈሳዊ ሕይወት መኖርን ግድ ይላል፡፡ ሌላው ወደፊት ጌታ የሚያሳየኝ አገልግሎት በመደበኛ የቤተክርስቲያን አገልግሎት መስጠት ነው፡፡ በስልክ ለተቸገሩ የምጸልየውና የማማክረው ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ነው በሩቅ ላሉ ብቻ ካልሆነ በስተቀር፡፡ በቅርብ ጊዜ ከአዲስ አበባ በስተምዕራብ የኮልፌ ቀራኒዮ አዋሳኝ በሆነው አሸዋ ሜዳ በሚባለው የቡራዩ ዞን ውስጥ በተሰጠን መሬት ላይ አዳራሽ በመስራት መደበኛ የቤተክርስቲያን አገልግሎት ለመስጠት በጸሎትና በአስፈላጊው ነገር ሁሉ እየተዘጋጀን ስለሆነ በዚያ ሰዎች የእግዚአብሔርን በረከት እንደሚያገኙ እምነቴ ነው"፡፡

# ማጠቃለያ

ወደማጠቃለሉ ስንቃረብ እስከዚህ መፅሐፍ ዝግጅት ድረስ በጌታ ቤትና በአገልግሎት ከቆየህባቸው ሠላሳ ሰባት አመታት ልምድህ ለዘመናችን አገልጋዮች መሪዎችና በአጠቃላይ ለቤተክርስቲያን የምትሰጠው ምክር ካለ ብለን ስንጠይቀው የሚከተለውን ሲመልስልን የተነሳው ለሱ ምሳሌ ከሆኑት ያካበቢው ቀደምቶች ከዕብራውያን አሥራ አንድ ከቁጥር ሠላሳ ሦስት እስከ ሠላሳ ስምንት ባሉት ክፍል ነው፡፡

"እነሱ በእምነት መንግስታትን ድል ነሱ ፅድቅን አደረጉ የተሰጠውን የተስፋ ቃል አገኙ፡፡ የአንበሶችን አፍ ዘጉ የእሳትን ኃይል አጠፉ፡፡ ከሰይፍ ስለት አመለጡ ከድካማቸው በረቱ በጦርነት ኃይለኞች ሆኑ የባዕድ ጭፍሮችን አባረሩ ሴቶች ሙታናቸውን በትንሳኤ ተቀበሉ ሌሎችም መዳንን ሳይቀበሉ የሚበልጠውን ትንሳኤ እንዲያገኙ እስከ ሞት ድረስ ተደበደቡ ሌሎችም መዘበቻ በመሆንና በመገረፍ ከዚህም በላይ በእስራትና በወህኒ ተፈትኑ በድንጋይ ተወግረው ሞቱ ተፈትኑ በመጋዝ ተሰነጠቁ በሰይፍ ተገድለው ሞቱ፡፡ ሁሉን እያጡ መከራን እየተቀበሉ እየተጨነቁ የበግና የፍየል ሌጦ ለብሰው ዞሩ ዓለም አልተገባቸውምና በምድረበዳና በተራራ በዋሻና በምድር ጉድጓድ ተቅበዘበዙ"

"ከእኛ በፊት ብዙ ዋጋ የከፈሉ ወገኖች የእንባ ፍሬና የድካም ውጤት ነን፡፡ በ1960ዎቹና በ1970ዎቹ ብዙ ዋጋ የከፈሉ አባቶችና እናቶች ወንጌላውያንና የቤተክርስቲያን መሪዎች በሀገራችን





ለጀመረው የወንጌል ሕይወትና አገልግሎት ታላቅና የማይረሳ ሥራ ሠርተዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ ጥቂቶቹን ለማስታወስ፦

- ፓ/ር ተፈራ ጎንፋ
- ፓ/ር ደረሰ ገለታ
- ወ/ዊ ዱሬሳ ዲንሳ
- ወ/ዊ ሲቀታ ገለታ
- አቶ ንጉሜ ኮማ
- ወ/ሮ መገርሴ ሻንቆ
- አቶ ቶሌራ እሬሳ
- አቶ ኢጋ ሂርጳ
- አቶ ዲንሳ ገለታ
- አቶ ደበሎ ገለታ
- አቶ ጌታቸው ሙለታ
- አቶ ገቡላ አመንቴ
- አቶ በቀለ ጉዮ
- አቶ አበበ አያና
- አቶ አቤቱ ከትል
- አቶ ወሳኔ ኪትል
- አቶ ቂጣታ ገርቢ
- አቶ ገርባ ቴሶ

• ፓ/ር ተስፋዬ ሀይሌና ባለቤታቸው ወ/ሮ መሠረት ነቀምት ወ/ሮ ሸጌና፣ ወ/ሮ ሎሚ ዲንሳ ስበም ጊዳ አገልጋዮችን የሚያሳርፉና የሚያገለግሉ ደከመን ሰለቸን የማይሉ ራሳቸውንና

ኑሯቸውን ለጌታና ለቅዱሳን መስዋዕት አድርገው የሰጡ እናቶች ሲሆኑ የተራበውን አብልተው የደከመውን አሳርፈው ከሌላ ቦታ ተሰዶ የመጣውን ሸሽገውና አፅናንተው ሲሄዱም ሸኝተው በተመሳሳይ ሁኔታ ለአመታት አገልግሎታቸውን የፈፀሙ ወገኖች ናቸው፡፡ ሌሎቹም ቢሆኑ ለወርና ከዚያም በላይ እየዞሩ ወገኖችን ይጎበኛሉ ያፅናናሉ፡፡ በስደት ሲባረሩ እርሻና ከብታቸውን በበረት ጥለው ይሸሻሉ፡፡ የቀበሌ ታጣቂዎችም ለማስካድ ከማሰር ከአካባቢ ከማባረር ባለፈ አፋቸውን በእንጨት እየፈለቀቁ አረቂ በማንቆርቆር እንዲክዱ የማድረግ ሙከራ ያደርጉ ነበር፡፡

አፋቸው በእንጨት ተፈልቅቆ አረቂ ከተጋቱት ውስጥ እስከዛሬም በጌታ ፀንተው እያገለገሉ ያሉት ወ/ሮ ሴቀታ ገለታ አንዱ ናቸው፡፡ ወ/ሮ ገላኔና ወ/ሮ ጋሌ ኢንዶ ከተማ ሕዝብ በተሰበሰበበት በገበያ ላይ ራቁታቸውን እንዲዞሩ ተደርገዋል፡፡ "ትክዳላችሁ ወይስ ራቁታችሁን ገበያ ትዞራላችሁ" ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ "ጌታን አንክድም ራቁቱን ለተገረፈልን ጌታ ራቁታችንን መዞር ለኛ ክብር ነው ራቁታችንን ላዞራችሁን ለናንተ ግን ወዮላችሁ" ነበር መልሳቸውና ራቁታቸውን በቅዳሜ ገበያ እንዲዞሩ ተደረገ፡፡ እርቃናቸውን ያዞሯቸው ግለሰቦችም ስርዓቱም ዛሬ የሉም እነዚህ እህቶች ግን ትዳር መስርተው ወልደው ከብደው ዛሬም የብዙዎች በረከት ሆነው በህይወት አሉ፡፡

እንግዲህ ከላይ ከብዙዎቹ ውስጥ በጥቂቱ ለምሳሌ ያህል የጠቀስናቸውና የሌሎችም የብዙዎች ድካም ውጤት ነን፡፡





የእግዚአብሔር ሥራ የአንድ ሰው ሥራ አይደለም የብዙዎች እስተዋፅዖ ውጤት ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቤት የአስተዋፅዖ ቤት ነው፡፡ የእኔ በጌታ መቆምና ማገልገልየነሱ ድካም ውጤት ነው፡፡ ደግሞም የኔም ብቻ አይደለም ከዚያ በኋላ ለተገለጠው ታላቅ የእግዚአብሔር ሥራና የአብያተክርስቲያናት ማደግ የዚያን ዘመን ወገኖች እንባ ውጤት ነው፡፡ ያንጊዜ ዋንኛው የፀሎት ርዕስ የሰዎች መዳን የጌታ መንፈስ መፍሰስና ዳግም ምፅዓት ነበሩ፡፡ የጌታ መመለስ ትልቅ ናፍቆታችን ነበር፡፡ ሰው ሲገናኝ ሰላምታ ከተለዋወጠ በኋላ "አይዞህ ጌታ ይመጣል" በመባባል እርስ በርሱ ይፅናና ነበር፡፡

የዚያን ጊዜውን መንፈሳዊ ሕይወት ከዛሬው ጋር ስናስተያይ ያን ጊዜ መታዘዝና መስማማት ተነጋግሮ መግባባት እግዚአብሔርን መፍራት ነበር፡፡ ዛሬ እግዚአብሔርን መፍራት የለም፡፡ ያኔ ቅርብ የነበረው እግዚአብሔር ዛሬ ርቋል፡፡ ክብሩም በመካከላችን የለም፡፡ ሰው ቢበዳደል እንኳ ጥፋቱ የኔ ነው በማለት ሰላም ፈላጊው በራሱ ላይ ፈርዶ ይቅርታ ይጠየቁ ነበር፡፡ ዛሬ ድፍረት አለ፡፡ እኔ ጥፋተኛ ነኝ የሚል የለም፡፡ ቢያጠፋ እንኳ ንስሀ ገብቶ የተበደለውን ይቅርታ ለመጠየቅ ይከራከራል፡፡ በደልን ይቆጥራል፡፡ ያኔ ሰው በወንድሙ ውድቀት ያዝናል ጌታ ሆይ አስበው ይቅር በለው ወደልቡ መልሰው እያለ ይማልዳል ያለቅሳል ዛሬ ግን ሰው በወንድሙ ውድቀት ይስቃል ወሬውንም በከፍተኛ ፍጥነት ያዳርሳል፡፡ ስለ ወንድሙ አይገደውም፡፡ እግዚአብሔር ስለደከመው

እንደሚገደው ሊገደን ይገባል፡፡ ጥንት እርስ በርስ መፈላለግ ነበር፡፡ ዛሬ ግን ሰው አንዱ ካንዱ ይሻሻል ፊቱን አዙሮ ያልፋል፡፡ አገልግሎትም በምሪት ነበር፡፡ አሁን ግን በሥጋ ምርጫ በመሆኑ ኃይል ጠፋ ቃሉና ፀሎት ቁልፍ ስልጣን ሆነው ሳሉ ወደ ጎን ተትተዋል፡፡ ንስሀ የማይገባው እርኩታ የሌለው ከአለም ጋር የተደባለው ብድራቱን የረሳው የጌታን አደራ የናቀው በሀጢአት የተዋጠው የዚህ ዘመን ክርስቲያን ሊመለስ ይገባዋል አለበለዚያ ግን በፍፃሜው ይጎዳል፡፡

ጌታ ይባርካችሁ

እምነትንም ይስጣችሁ!



ደረጀ በቀለ

ወንድም ሮሮን እና ወንድም ገርቦሌን በስም ካወቅኋቸው 30 ዓመታት አልፈውኛል። በአሙሩ ከነደደው ከዚያ አስደናቂ ሪቫይቫል ጋር በተያያዘ ነበር የእነዚህን ወንድሞች ስም ለመስማት የበቃሁት። አሁን ደግሞ በነብይ ገርቦሌ አዳዳን፣ አስተዳደግና አገልግሎት ዙሪያ የምታጠነጥነውን የዚህችን መጽሐፍ ረቂቅ ለማንበብ እና አስተያየት ለመጻፍ በመብቃቴ እራሴን እንደ ትልቅ ባለ ዕድል እቆጥረዋለሁ።

በዚህች መጽሐፍ ውስጥ የምናነባቸው ምስክርነቶች ከማስደነቅ ያልፋሉ። ያስደምማሉ ብል ይሻላል። መስካሪዎቹ ብዙ ሰዎች መሆናቸው ደግሞ ታሪኩን እጅግ ተአማኒ ያደርገዋል። አ! መንፈስ ቅዱስ ሆይ! የዛሬ 44 ዓመት ምዕራባዊውን የአገራችንን ክፍል በጎበኘህበት ዓይነት ጉብኝት እባክህን እንደገና ምድራችንን ጎብኝ። እነ ወንድም ገርቦሌን በነካህበትም ዓይነት መንካት እባክህን ብዙዎችን እንደገና ንካ።

በቀለ ወ/ኪዳን (መጋቢ)

“በቋጥኝ ላይ የበቀለች ዋርካ” መጽሀፍ እግዚአብሔር በየዘመናቱ ቦታና ሰውን ሳይለይ የሚሠራቸውን ድንቅ ሥራዎች የምታሳይ ከመሆኑም በላይ እግዚአብሔርን ታምነው የሚሠማሩ እንዴት መለኮታዊ ኃይሉን መለማመድ እንደሚችሉና ለእግዚአብሔር መንግስት መስፋፋት ምክንያት እንደሚሆኑ በግልጽ ታስረዳለች። የነብይ ገርቦሌ የሕይወት ጉዞ ብዙዎች ሊማሩበትና ሊነቃቁበት የሚያስችል አስደናቂ ታሪክ ነው። አንብቡት ትጠቀማላችሁ።

ንጉሴ ተፈራ (ዶ/ር)

በነብይ ገርቦሌ አገልግሎት ላይ ያተኮረውን መጽሐፍ ያነበብኩት በትልቅ ተመስጦ ነው። ቀደም ሲል የሰማኋቸው አንዳንድ ታሪኮቹ ጭምር በዚህ መስክ ተፅፈው ሲቀርቡ የአገልጋዩን ታሪክ በጥልቅ ለመገንዘብ አስችሎኛል። የአገልጋዩን ታሪክ ስናስብ እግዚአብሔር አንድን ሰው ለመጥራትና ለመጠቀም ከፈለገ የግለሰቡ ማንነት እንደማያግደው ነቢዩ የተጠራበትን ዕድሜ የኖረበትን የገጠር አካባቢና የዕውቀት ደረጃውን ስንመለከት የበለጠ እንገነዘባለን። ስለሆነም መፅሀፉ ለአንባቢዎች የእግዚአብሔርን ፈቃድ አሸናፊነት አጉልቶ የሚያሳይ ስለሆነ መነበብ ያለበት መጽሐፍ ነው።

ፓ/ር ፃድቁ አብዶ
የኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤ/ክ ዋና ፀሀፊ

**ዋጋው 35 ብር**